# የህብረተሰብ ትምህርት

## የተማሪ መጽሐፍ

## 7ኛ ክፍል


በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ
ISBN ቁጥር -
ዋጋ ብር -


የህብረተሰብ ትምህርት የተማሪ መጽሐፍ 7ኛ ክፍል

# የህብረተሰብ ትምህርት

## የተማሪ መጽሐፍ

## 7ኛ ክፍል







በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ

## የጥንቃቄ መልዕክት

**ተማሪዎች!**

**ይህን የተማሪ መጽሐፍ በጥንቃቄ ያዙ!**

ይህ መማሪያ መጽሐፍ በቀጣይ ዓመት የናንተ ወንድሞችና እህቶች የሚማሩበት የትምህርትቤታችሁ ንብረት ነው! መጽሐፉ እንዳይበላሽ ወይም እንዳይጠፋ በጣም መጠንቀቅ አለባችሁ። መጽሐፉን በጥንቃቄ ለመያዝ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መመሪያዎች ተግባራዊ አድርጉ፤

1. መጽሐፉን ከጉዳት ለመከላከል በላስቲክና በአሮጌ ጋዜጣ ወይም በካኪ ወረቀት ሸፍኑ፤
2. መጽሐፉን ሁልጊዜ ደረቅና ንጹህ በሆነ ቦታ አስቀምጡት፤
3. መጽሐፉን ለመጠቀም ስትዘጋጁ በቅድሚያ እጃችሁ እርጥበት የሌለውና ንጹህ መሆኑን አረጋግጡ፤
4. በመጽሐፉ ሽፋን ወይም የውስጥ ገጾች ላይ አትጻፉ፤
5. መጽሐፉን እያነበባችሁ እያላችሁ ንባባችሁን አቋርጣችሁ እንደገና ለማንበብ ስትፈልጉ ምልክት ማድረጊያ ብጣሽ ወረቀት ወይም ካርድ ተጠቀሙ፤
6. በመጽሐፉ ውስጥ ያሉ ስእሎችን ወይም ገጾችን አትቅደዱ፤
7. በመጽሐፉ ውስጥ የተቀደደ ወይም የተገነጠለ ገጽ ሲኖር በሙጫ ወይም በሌላ ንጹህ ማጣበቂያ ጠግኑት፤
8. መጽሐፉን ከቦርሳችሁ ስታስገቡ ወይም ስታወጡ ጥንቃቄ አድርጉ፤
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው ስታቀብሉም ሆነ ከሌላ ሰው ስትቀበሉ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጉ። ደህንነቱን አረጋግጣችሁ ተቀበሉ።
10. መጽሐፉን ለመጀመሪያ ጊዜ ስትቀበሉ ሽፋኖቹና ገጾቹ እንዳይገነጣጠሉ መጽሐፉን በጀርባው ጋደም አድርጋችሁ አስቀምጡት፤ ከዚያም ጥቂት ገጾችን ቀስ እያላችሁ በየተራ ግለጡ፤ በግራና በቀኝ እጃችሁ የያዛችሁትን የመጽሐፉን ክፍል በኃይል አትጫኑት (አትመንጭቁት)።

**ማሳሰቢያ፤** እነዚህ መመሪያዎች ሳይተገበሩ ቀርተው በመጽሐፉ ላይ አንዳች ጉዳት ከደረሰ በወጣው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ያደርጋል።

# የህብረተሰብ ትምህርት

## የተማሪ መጽሐፍ

## 7ኛ ክፍል


አዘጋጆች

ሸዋነሰህ ፍስሐ (ኤም. ኤ በጂኦግራፊ)
ሠይድ ሁሴን (ኤም. ኤ በታሪክ)

አርታኢዎች:

አበበ ጠየቀ (ኤም. ኤ በጂኦግራፊ)
ሽመልስ አየለ (ኤም. ኤ በታሪክ)

የቡድን መሪ

ሙሉጌታ ነቅዓ (ረዳት ፕሮፌሰር)

ሰዓሊ

ከበደ አለሙ እና ቀለመወርቅ ተገኘ

ዲዛይነር

አትርሳው ጥግይሁን



በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በተመደበ በጀት በአብክመ ትምህርት ቢሮና በምሁራን መማክርት ጉባዔ ትብብር ነው፡፡

የመጽሐፉ ሕጋዊ የቅጂ ባለቤት © 2015 ዓ.ም. አብክመ ትምህርት ቢሮ ነው፡፡

ምሁራን መማክርት ጉባዔ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

## ማውጫ


መግቢያ ................................................................................................ vi

### ምዕራፍ-1

### የህብረተሰብ ትምህርት፣ ሁለንታ እና ስርዓተ ፀሀይ

1.1. የህብረተሰብ ትምህርት ጽንሰ ሐሳብ........................................................ 2
1.2 የሁለንታ (Universe) ምንነትና ጥንቅር (Composition) ............................ 4
1.3. የስርዓተ ፀሀይ (Solar System) ምንነትና ጥንቅር (Composition)........... 7
1.4. የመሬት አፈጣጠር እና ዝግመተ ለውጥ (Evolution) ................................ 13
1.5. የመሬት መገኛ (Position) እና ቅርጽ (Shape)......................................... 15
1.6. የመሬት እንቅስቃሴዎችና የሚያስከትሏቸው ውጤቶች ................................ 17
1.7. የጊዜ ስሌት ........................................................................................ 23
1.8. የመሬት ገፅታዎች ................................................................................ 26
1.9. የመሬት ውስጣዊ አወቃቀር (Internal Structure of the Earth)............... 28

### ምዕራፍ-2

### የዓለም ሕዝብ፣ መጓጓዣ እና የካርታ ጽንሰ ሐሳብ

2.1. የዓለም ህዝብ ቁጥር ታሪካዊ እድገትና ስርጭት ........................................ 35
2.2. የመጓጓዣ (Transport) ጽንሰ ሐሳብ፣ ዓይነቶች እና ለማህበረ- ምጣኔ ሀብታዊ እድገት ያለው ጠቀሜታ ................................................................ 39
2.3. የመንገድ ደህንነት፣ የትራፊክ አደጋ እና ማህበረ-ምጣኔ ሀብታዊ ችግሮቹ .... 41
2.4. የካርታ እና ሉል ጽንሰ ሐሳቦች፣ ጠቀሜታዎችና ዓይነቶች ........................ 45
2.5. የካርታ ሕዳግ መረጃዎች እና የካርታ ንባብ መርሆዎች ............................ 50
2.6 ዓለም ዓቀፋዊ መገኛ ስርዓት (Global Positioning System/GPS/) ........... 52

### ምዕራፍ-3

### የሰው እና የተፈጥሮ ሀብቶች መስተጋብር

3.1. የሰው እና የአካባቢ ግንኙነት ................................................................ 59
3.2. የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶች....................................................................... 61
3.3. የሕዝብ አሰፋፈር እና የተፈጥሮ ሀብቶች ግንኙነት ................................ 63
3.4. የሕዝብ ጥግግት መለኪያዎች................................................................... 65
3.5. በኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን ............................................... 67

### ምዕራፍ-4

### ጥንታዊ እና የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ

4.1 የጥንታዊ ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ ......................................................... 74
4.1.1.ቅድመ አክሱም መንግስታት ................................................................ 74
4.1.2. የአክሱም ስልጣኔ ............................................................................... 76
4.1.3. የዛግዌ ስርወ መንግስት አነሳስና መጠናከር............................................ 81
4.2 የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ...................................................... 83
4.2.1. የሰለሞናዊ ስርወ መንግስት ዳግም መመስረት ........................................ 83

4.2.2. የሙስሊም ሱልጣኔቶች ........................................................ 84
4.2.3. የአዳል ሱልጣኔት እና የደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት ጦርነት................ 88
4.2.4. የኦሮሞ ህዝብ መስፋፋት .................................................... 89
4.2.5 የመካከለኛው ዘመን ምጣኔ ሀብታዊ መሰረቶች እና ዋና ዋና የረጅም ርቀት ንግድ መስመሮች ............................................................ 91
4.2.6. የጎንደር ዘመን ................................................................ 93
4.2.7. ዘመነ መሳፍንት (1769-1855) ............................................ 95

## ምዕራፍ-5

## የአፍሪካ ታሪክ እስከ 1500

5.1. የአፍሪካ ቋንቋዎች.............................................................. 102
5.2. ጥንታዊ የሰሜን አፍሪካ ስልጣኔዎች ........................................ 104
5.3. ጥንታዊ የምዕራብ አፍሪካ መንግስት ምስረታ ............................ 109
5.4. የመካከለኛውና ደቡብ ምስራቅ አፍሪካ መንግስታት....................... 113
5.5. የምስራቅ አፍሪካ ጠረፍ ንግድ ማህበረሰቦች ............................ 116

## ምዕራፍ-6

## የዓለም ጥንታዊ ስልጣኔዎችና የመካከለኛው ዘመን ታሪክ

6.1. የጥንታዊ ዓለም ስልጣኔዎች ................................................ 122
6.1.1. የጥንታዊ ሜሶፖታሚያ ስልጣኔ ............................................ 122
6.1.2. የህንድ ጥንታዊ ስልጣኔ.................................................... 124
6.1.3. የጥንታዊ ቻይና ስልጣኔ .................................................. 127
6.1.4. የጥንታዊት ግሪክ ስልጣኔ ................................................ 129
6.1.5. የሮማ ሥልጣኔ................................................................ 132
6.2. የመካከለኛው ዘመን የዓለም ታሪክ ......................................... 134
6.2.1. የጨለማው ዘመን ታሪክ በአውሮፓ ....................................... 134
6.2.2. የባይዛንታይን ግዛተ አፄ ................................................... 135
6.2.3. የኦቶማን ግዛተ አፄ ......................................................... 137
6.3. በአለም ላይ ያሉ ዋና ዋና ሃይማኖቶች .................................... 139

## ምዕራፍ-7

## ወቅታዊ ዓለም ዓቀፋዊ ሁኔታዎች

7.1. ወቅታዊ አካባቢያዊ ጉዳዮች.................................................... 145
7.2. ፈጣን የህዝብ ቁጥር እድገት ................................................ 152
7.3. ሽብርተኝነት (Terrorism) ................................................... 154
7.4. ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር (Human Trafficking) ........................ 156
7.5. ኤች አይ ቪ ኤድስ (Human Immunodeficiency Virus/HIV) .............. 160
ማጣቀሻዎች (References)........................................................ 165

## የመጻሕፍት አተገባበር

መጽሐፉ ተማሪዎች ከዚህ ቀደም ከሚያውቁትና ከአካባቢያቸው ይዘውት ከሚመጡት ተሞክሮና እውቀት በመነሳት ተግባር ተኮር እና አሳታፊ በሆነ መልኩ እንዲማሩ ሆኖ ስለተዘጋጀ ተማሪዎች ትምህርቱን በጥልቀት ይገነዘቡታል ወይም ይረዱታል ተብሎ ይታመናል። ተማሪዎችና መምህራን አካባቢያቸውን እና ያካበቱትን ዕውቀትና ተሞክሮ መሰረት በማድረግ በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የተለያዩ ተግባራትን በአግባቡ በመተግበር ተማሪዎቻችን ይዘቶችን መማር ብቻ ሳይሆን የመማር ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ ይጠበቃል። በመሆኑም መምህራን ለይዘቱ ተስማሚ ተብለው የተጠቆሙ የማስተማሪያ እና መማሪያ ዘዴዎችን በአግባቡ በመተግበርና ሌሎች ተገቢ ዘዴዎችን ተጨባጭ ሁኔታንና የተማሪዎችን አቅምና ፍላጎት መሰረት አድርጎ በመምረጥ ተማሪተኮር /አሳታፊ አድርገው የመማር ማስተማሩን ተግባር መፈጸም የሚጠበቅባቸው ሲሆን ተማሪዎች ደግሞ በትምህርቱ ክፍለ ጊዜ መጽሐፍቱን ከእጃቸው ሳይለዩ ትምህርቱን መከታተል ይኖርባቸዋል።

## ውድ ተማሪዎቻችን!

መጽሐፉን በጥንቃቄ በመያዝ በአግባቡ መጠቀም አለባችሁ። በማንኛውም አገርና ሁኔታ መማር የትውልድን የወደፊት ሁኔታ ይወስናል። መማር ለማንኛውም ማህበራዊ፣ ሰብዓዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መሰረት ነው። በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ተግባራት፣ ይዘቶችና ጥያቄዎች በአግባቡ በመስራትና በማጥናት ጥልቀት ያለው ክህሎትን እና ግንዛቤን ማዳበር ይገባችኋል።

## ውድ ወላጆች /አሳዳጊዎች!

የተማሪዎችን መማር የተሳለጠ ለማድረግ የመማሪያ መጻሕፍት ያላቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። ስለሆነም ተማሪዎች መጽሐፉን በጥንቃቄ ይዘው እንዲጠቀሙ ማድረግ ይኖርባችኋል። ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች መጽሐፉን ት/ቤት ይዘው እንዲሄዱ ማበረታታት፣ ከመምህሮቻቸው የሚሰጡ ተግባራትን በትክክል እንዲፈጽሙና እንዲያጠኑ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ ትምህርት ቤት በመሄድ ከመምህራን ጋር በመገናኘት ስለ ልጅዎ የመማር ዕውቀትና የባህሪ ለውጥ በመጠየቅ ክፍተቱን በመለየት ምክር በመሥጠት ማስተካከል ይጠበቅባችኋል። በመሆኑም ትምህርት የሁሉም ነገር መሰረት መሆኑን በመገንዘብ መማርን ከመንግስት ስራ መያዝ ጋር ብቻ ሳታቆራኙት/ሳያያይዙት ልጆችን ሁልጊዜ ወደትምህርት ቤት መላክ አለባችሁ።

# መግቢያ

በዚህ የሰባተኛ ክፍል የሕብረተሰብ ትምህርት መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ሰባት ምዕራፎች ይገኛሉ፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሶስት ምዕራፎች የጂኦግራፊ ይዘቶችን ያካተቱ ሲሆን ከምእራፍ አራት እስከ ስድስት የሚገኙት ደግሞ በታሪክ ይዘቶች የተዋቀሩ ናቸው፡፡ በምዕራፍ ሰባት ወቅታዊ ዓለም ዓቀፋዊ ጉዳዮች ቀርበዋል፡፡

የጂኦግራፊ ትምህርት ይዘቶችን በተመለከተ ምዕራፍ አንድ የህብረተሰብ ትምህርት፣ ሁለንታ እና ስርአተ ፀሐይ የተዳሰሱበት ሲሆን ምዕራፍ ሁለት ደግሞ የዓለም ሕዝብ፣ መጓጓዣ እና የካርታ ጽንሰ ሐሳብ የሚቀርቡበት ነው፡፡ በምዕራፍ ሶስት የሰው እና የተፈጥሮ ሀብቶች መስተጋብር ቀርቧል፡፡

የታሪክ ትምህርትን በተመለከተ ምዕራፍ አራት ጥንታዊ እና የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ ማለትም ከቅድመ አክሱም እስከ አፄ ቴዎድሮስ ዘመን ያለውን ታሪክ አካትቷል፡፡ አምስተኛው ምዕራፍ የአፍሪካን ጥንታዊ ታሪክ እስከ 1500 ዓ.ም ያለው ተዳስሶበታል፡፡ ስድስተኛው ምዕራፍ ደግሞ የዓለም ጥንታዊ ስልጣኔዎች እና የመካከለኛው ዘመን የዓለም ታሪክን ይሸፍናል፡፡

በዚህ መፅሀፍ ዓመተ ዓለም(ዓ.ዓ) ማለት የጊዜ አቆጣጠሩ ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለውን ጊዜ ሲያመለክት ዓመተ ምህረት(ዓ.ም) ደግሞ ከክርስቶስ ልደት ኋላ ያለውን የጊዜ አቆጣጠር ያሳያል፡፡ በመፅሀፉ የተጠቀሱት አመታት የተቀመጡት እንደ አውሮፓዊያን የዘመን ቀመር ነው፡፡ ሰባተኛው ምዕራፍ በአሁኑ ጊዜ የዓለምን ሕብረተሰብ ፈታኝ የሆኑ አሳሳቢ ጉዳዮች ተዳሰውበታል፡፡

# ምዕራፍ-1

# የህብረተሰብ ትምህርት፣ ሁለንታ እና ስርዓተ ፀሀይ

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ስር የህብረተሰብ ትምህርት ምንነትና ዓላማዎች፣ የሁለንታ (Universe) እና የስርዓተ ፀሀይ ጥንቅሮች (Composition) እንዲሁም የመሬት አፈጣጠር፣ መሬት በስርዓተ ፀሀይ ውስጥ የምትገኝበት አቀማመጥና የምታደርጋቸው እንቅስቃሴዎች የሚያስከትሏቸው መሰረታዊ ክስተቶች ይቀርባሉ:: ከዚህ በተጨማሪ በምዕራፉ ውስጥ ዓለም ዓቀፍ የጊዜ ክልሎች (International Time Zones) ጽንሰ ሀሳብ እና የጊዜ ስሌት ክህሎት የሚያስጨብጡ ተግባራት ተካተዋል:: በመጨረሻም የመሬት መልክዓ ምድራዊ ገፅታዎች እና ውስጣዊ አወቃቀር የሚዳስሱበት ይዘቶች ተደራጅተው ቀርበዋል::

**ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት፡**

*ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦*

- *የህብረተሰብ ትምህርትን ምንነት ታብራራላችሁ::*
- *የሁለንታንና የስርዓተ ፀሀይን ጥንቅር (Composition) የሚያሳይ ንድፈ ካርታ (Sketch Map) ትሰራላችሁ::*
- *የመሬት አፈጣጠርን ታሪክ ትገልጻላችሁ::*
- *የመሬትን ቅርጽ የሚወክል ሞዴል ትሰራላችሁ::*
- *የመሬት ሽክርክሪትንና ዙሪትን ምንነት ትገልጻላችሁ፣ የሚያስከትሏቸውን ውጤቶች ታደንቃላችሁ::*
- *ጊዜን ታሰላላችሁ::*
- *የመሬትን መልክዓ ምድራዊ ገጽታ የሚያሳይ ንድፍ ታዘጋጃላችሁ::*
- *የመሬትን ውስጣዊ ንብርብሮች እና በመካካላቸው ያለውን ግንኙነት ትመረምራላችሁ::*

## ቁልፍ ቃላት:

- ሁለንታ (Universe)
- ቅርፊተ መሬት (Crust)
- ሽክርክሪት (Rotation)
- ስርዓተ ፀሀይ (Solar System)
- ማእከለ መሬት (Mantle)
- ዙሪት (Revolution)
- እምብርተ መሬት (Core)
- ሜዳማ ስፍራ (Plain)
- ገበቶ (Plateau)

## 1.1. የህብረተሰብ ትምህርት ጽንሰ ሐሳብ

ውድ ተማሪዎች! የህብረተሰብ ትምህርት ምንድን ነው?

ለዚህ ጥያቄ ምላሽ መስጠት ትችሉ ዘንድ የሚከተለውን ተግባር ለማከናወን ሞክሩ:: ተግባሩን የምታከናውኑት በቅድሚያ ሠንጠረዡንና በሠንጠረዡ ውስጥ የተዘረዘሩትን ሀሳቦች በደብተራችሁ ላይ አስፍራችሁ ነው::

### ተግባር-1

1. በመጀመሪያ በየግላችሁ የ7ኛ ክፍል የህብረተሰብ ትምህርት መማሪያ መጽሀፍን ይዘቶች ለመዳሰስ ሞክሩ::
2. ቀጥሎ በጥንድ በጥንድ በመሆን በሰንጠረዡ ውስጥ የተቀመጠው እያንዳንዱ ይዘት ከህብረተሰብ ትምህርት ጋር ያለውን ዝምድና እየገመገማችሁ ውሳኔያችሁን (ምርጫችሁን) እስማማለሁ ወይም አልስማማም በማለት ከፊት ለፊቱ የ'✓' ምልክት በማድረግ አመላክቱና ለምን በሚለው አምድ ስር ደግሞ ምክንያታችሁን ግለጹ::

| ይዘት | እስማማለሁ | አልስማማም | ለምን? |
|---|---|---|---|
| የሰው ልጅ የሚኖርበት ዓለም | | | |
| ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ክስተቶች | | | |
| የሰው ልጅ የእርስ በርስ ግንኙነት | | | |
| የሰው ልጅና አካባቢ ግንኙነት | | | |
| የህንጻና የመንገድ አሰራር | | | |
| ስርአተ ምግብ (Nutrition) | | | |
| የመድሀኒት ምርምር | | | |
| አካባቢያዊ፣ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ክስተቶች/ጉዳዮች | | | |
| ህዝባዊ ጉዳዮች | | | |

## ተግባር-2

1. እስማማለሁ' በሚል ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ሀሳቦች አሰባስባችሁ በራሳችሁ አገላለጽ የህብረተሰብ ትምህርትን ምንነት እና ጠቀሜታዎች የሚገልጽ አንድ የማጠቃለያ አንቀጽ ጻፉ::
2. ያዘጋጃችሁትን የማጠቃለያ አንቀጽ ለክፍል ተማሪዎች በገለጻ ካቀረባችሁ በኋላ ለሚቀርቡላችሁ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ምላሽና ግብረ መልስ ስጡ::


ተማሪዎች! ከላይ የተሰጡትን ተግባራት በሚገባ እንዳከናወናችሁ ይታመናል:: የህብረተሰብ ትምህርት (Social Studies) ከተለያዩ የማህበራዊ ሳይንስ (Social Science) የትምህርት ዘርፎች (ለምሳሌ፦ ጂኦግራፊ፣ ታሪክ፣ ምጣኔ ሀብት፣ ፍልስፍና፣ ህግ፣ ወዘተ) የተመረጡ ቀለል ያሉ ይዘቶች ለተማሪዎች የእድሜ ደረጃ በሚመጥን መልኩ ተደራጅተው የሚቀርቡበት የትምህርት ዓይነት ነው:: የህብረተሰብ ትምህርት የሰው ልጅ እርስ በርሱና በአካባቢው ከሚገኙ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ክስተቶች ጋር የሚያደርገውን መስተጋብር (ግንኙነት) የሚያጠና የትምህርት ዓይነት ነው:: ይህ ትምህርት ከተለያዩ የማህበራዊ ሳይንስ የትምህርት መስኮች የተውጣጡ ይዘቶችን ያካተተ በመሆኑ ተማሪዎች በአካባቢያዊ፣ በማህበራዊ እና በተፈጥሯዊ ክስተቶች ላይ እንዲሁም በአገራዊና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ላይ አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያደርግ ነው::

## 1.2 የሁለንታ (Universe) ምንነትና ጥንቅር (Composition)

### ተግባር-3 - የቤት ስራ

1. የደመና ሽፋን በሌለበት ምሽት ወደ ሰማይ አንጋጣችሁ ተመልከቱ:: የምታዩአቸውን ቁስ አካላት ከዘረዘራችሁ በኋላ የእያንዳንዱን አካል ምንነት ግለጹ::
2. እነዚህን አካላት እና ሰፊውን ሰማይ ስትመለከቷቸው ምን ዓይነት ስሜት ፈጠሩባችሁ?

ሁለንታ ማለት ሁሉንም ቁስ አካላት (ጠጣር፣ ፈሳሽና ጋዝማ ቁሶች) አጠቃልሎ የያዘ እጅግ በጣም ሰፊና ወሰን የለሽ ወይም ድንበር የለሽ ስፍራ ነው:: ሁለንታን ሙሉ በሙሉ ማየት አይቻልም:: ለምሳሌ ከታች በምስል 1 ላይ የምትመለከቷቸው ሁለት ፎቶግራፎች የተወሰኑ የሁለንታ ክፍሎች ናሙናዎች ናቸው::




ምስል 1 - የሁለንታ ናሙናዎች

ከታች በምስል 2 ላይ የቀረበላችሁ የሁለንታ መዋቅር ነው:: ምስሉ ስለ ሁለንታ አጠቃላይ አወቃቀር መሰረታዊ ግንዛቤ የሚያስጨብጣችሁ ስለሆነ መዋቅሩን ከመረመራችሁ በኋላ ቀጣዩን ተግባር ለማከናወን ሞክሩ::

## ተግባር-4

1. የሚከተለውን የሁለንታ መዋቅር በጥንድ በጥንድ በመሆን በጥልቀት ከፈተሻችሁ በኂላ ትንታኔ ስጡበት፤ በመቀጠል የማጠቃለያ ሀሳብ የያዘ ጽሁፍ አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በየተራ እየወጣችሁ አቅርቡ፡፡




ምስል 2 - የሁለንታ መዋቅር

ሁለንታ እጅግ መጠነ ሰፊ የሆነ ሁሉንም ቁስ አካላት አካትቶ የያዘ ወሰን የለሽ ስፍራ ነው ብለናል፡፡ ጠፈር ደግሞ በሁለንታ ውስጥ ወሰን የለሽ የሆነና ቁስ አካል የሌለበት ባዶ (Vaccume) ስፍራ ነው፡፡ ስለዚህ በመሬት ላይ ርቀቶችን ለመለካት የምንገለገልባቸውን አሀዶች ማለትም ኪሎ ሜትርንና ማይልን በመጠቀም የጠፈር/የህዋ ውስጥ ርቀትን ለመግለጽ ፈጽሞ አይቻለንም፡፡ ምክንያቱም በእነዚህ አሃዶች የሚለኩ ርቀቶች በጣም አነስተኛ የሆኑ ብቻ ናቸው፡፡

ውድ ተማሪዎች! በጠፈር ውስጥ ያለ ርቀትን በኪሎ ሜትርና በማይል ለመግለጽ ብንሞክር እንኳን የምናስቀምጣቸው ቁጥሮች (Digits) እጅግ በጣም ስለሚበዙ ለመጻፍና ለማንበብ እንቸገራለን፡፡ ስለዚህ የጠፈር አካላትን ርቀት ለመለካት የምንጠቀመው አሀድ የብርሃን ዓመት ነው፡፡ የብርሃን ዓመት ማለት ብርሃን በአንድ ዓመት ውስጥ የሚጓዘው ርቀት ነው፡፡ ብርሃን በሰከንድ 300,000 ኪ.ሜ ይጓዛል፡፡ በዚህ መሰረት 1 የብርሀን ዓመት ስንት ኪ.ሜ ይሆናል? (’ = ደቂቃ፣ ” = ሰከንድ)


መልሱ፦

300,000 ኪ.ሜ X 60” X 60’ X 24ሰ X 365.25 ቀናት = 9,467,280,000,000 ኪ.ሜ (ዘጠኝ ትሪሊየን አራት መቶ ስልሳ ሰባት ቢሊየን ሁለት መቶ ሰማንያ ሚሊየን) ነው፡፡

ከዋክብት የራሳቸውን ብርሃንና ሙቀት የሚያመነጩ በቁጥር እጅግ በጣም ብዙ የሆኑ የሁለንታ አካላት ናቸው፡፡ ከዋክብት ከመሬት ላይ ሆነን እንደምንመለከታቸው በመጠናቸው ትንንሽ አይደሉም፡፡ በአቀማመጣቸውም የተዘበራረቁ ሳይሆን በስርዓት ተሰባስበውና ተዋቅረው የሚገኙ ናቸው፡፡ ይህ ስብስብ ወይም ውቅር ረጨት (Galaxy) ይባላል፡፡ ረጨቶች የከዋክብት፣ የጋዞችና የአቧራ ብናኞች ስብስብ ወይም ክምችቶች ናቸው፡፡ ፀሀይ እና እኛ የምንኖርባት መሬት የሚገኙበት ረጨት ፍኖተ ሃሊብ ረጨት (Milky-Way Galaxy) ይባላል (ምስል 3ን ተመልከቱ)፡፡



ሀ



ለ

ምስል 3 - ፍኖተ ሃሊብ ረጨት ከሰሜን ዋልታ ሲታይ (ሀ) እና ከደቡብ ዋልታ ሲታይ (ለ)

*ተግባር-5*

1. ከፀሀይ ቀጥሎ ለመሬት ቅርብ የሆነችው ኮከብ አልፋ/ፕሮክሲማ/ ሴንቹዋሪ ናት:: ይህች ኮከብ ከመሬት ያላት ርቀት 4.3 የብርሃን ዓመት ነው:: ተማሪዎች! ይህችን ኮኮብ ዛሬ ማታ ላይ ብትመለከቷት ዓይናችሁ የሚያየው ክሰተት ኮከቧ አሁን የምትገኝበትን ሁኔታ ነውን? ማብራሪያ ስጡበት::

የጠፈር ወይም የህዋ ሳይንስ ጥናት አስትሮኖሚ ሲባል በዚህ ዘርፍ ላይ ምርምርና ጥናት የሚያደርጉ ባለሙያዎች ደግሞ አስትሮኖመር ይባላሉ:: በጠፈር ውስጥ የሚገኙ አካላትን አቅርቦ የሚያሳይ መሳሪያ ደግሞ የህዋ ቴሌስኮፕ ይባላል::

## 1.3. የስርዓተ ፀሀይ (Solar System) ምንነትና ጥንቅር (Composition)

ስርዓተ ፀሀይ ማለት ፀሀይ እና በዙሪያዋ የሚገኙትን አካላት ማለትም ፈለኮችን (Planets)፣ አስቴሮይዶችን፣ ኮሜቶችን፣ ተወርዋሪ ኮከቦችን (ሚቲዮሮችን)፣ ጅራታም ኮከቦችንና ጨረቃዎችን የያዘ ስብስብ ነው::

### ሀ) ፀሀይ

ፀሀይ በፍኖተ ሐሊብ ውስጥ ከሚገኙት በብዙ መቶ ቢሊዮን ከሚቆጠሩ ከዋክብት መካከል አንዷ ናት:: ፀሀይ የተፈጠረችው 75% ከሐይድሮጅንና 25% ከሒሊየም ጋዞች ክምችት መኮማተር (Contraction) ነው ተብሎ ይገመታል:: ፀሀይ የስርዓተ ፀሀይ ማዕከል ስትሆን ከፈለኮች (ፕላኔቶች) ጋር ተቀራራቢ እድሜ እንዳላትም ይታመናል:: የፀሀይ ሰቅ (ወገብ) ርዝመት ወይም መጠነ ዙሪያ (Circumference) 1,390,176 ኪ.ሜ ነው:: ስለዚህ ፀሀይ በመጠንዋ ከሌሎቹ የስርዓተ ፀሀይ አባላት ጋር ስትነጻጸር እጅግ በጣም ግዙፍ ናት:: የውጫዊ አካሏ የሙቀት መጠን 6000 ዲግሪ ሴልሽየስ ሲሆን የውስጠኛው አካሏ የሙቀት መጠን ደግሞ 15,000,000 ዲግሪ ሴልሽየስ ነው::



ምስል 4 - የስርዓተ ፀሀይ አባላት

## ተግባር-6

በትምህርት ቤታችሁ ከሚገኘው ቤተ መጻህፍት በመሄድ የተለያዩ ዋቢ መፅሀፍትን አገናዝባችሁ ወይም ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸውን ባለሙያዎች በማነጋገር ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ሞክሩ::

1. ፀሀይ ከሌሎች የስርዓተ ፀሀይ አባላት የምትለየው በምንድን ነው?
2. የምድር ሰቅ (ወገብ) ርዝመት ወይም መጠነ ዙሪያ 40,075 ኪ.ሜ ሲሆን የፀሀይ ሰቅ ርዝመት ወይም መጠነ ዙሪያ ደግሞ 1,390,176 ኪ.ሜ ነው:: ይህን መረጃ መሰረት በማድረግ የሁለቱን አካላት ግዝፈት አወዳድሩ::
3. ፀሀይ በየትኛው የቁስ አካል ምድብ ውስጥ ትፈረጃለች - ከጠጣር፣ ከፈሳሽ ወይስ ከጋዝ?

### ለ) ፈለኮች (ፕላኔቶች)

ምስል 4 ፈለኮች በፀሀይ ዙሪያ የሚገኙበትን አቀማመጥ ያሳያል:: ፈለኮች የስርዓተ ፀሀይ አባላት ሲሆኑ የራሳቸው የሆነ ብርሃንና ሙቀት የላቸውም ነገር ግን የፀሀይን ብርሃን በማንፀባረቅ ብርሃን ያላቸው ይመስላሉ:: ሁሉም ፈለኮች ፀሀይን ማእከላቸው በማድረግ በዙሪያዋ ይንቀሳቀሳሉ (ይዞራሉ):: ፈለኮች በፀሀይ ዙሪያ ለመዞር የሚከተሉት የራሳቸው መንገድ (path) አላቸው:: ይህ መንገድ ምህዋር (Orbit) በመባል ይታወቃል:: ከፈለኮች ውስጥ ለፀሀይ ቀረብ ብለው የሚገኙት የመጀመሪያዎቹ አራቱ ድንጋያማና ጠጣር ውጫዊ አካል አላቸው:: እነማን

ናቸው? ቀሪዎቹ አራቱ ፈለኮች ደግሞ ከፀሀይ የሚርቁ ሲሆን አካላቸው የተገነባው በሃይል ከታመቀ የሐይድሮጅንና የሄሊየም ጋዝ ነው:: እነዚህ ጋዝማ (gaseous) ፈለኮችስ እነማን ናቸው?

## ተግባር-7

በሠንጠረዥ 1 ውስጥ የተካተቱትን መረጃዎች መሠረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ::

1. እያንዳንዱ ፈለክ ከሌሎቹ የሚለይበትን ባህሪ ግለፁ::
2. ፈለኮችን እንደመጠናቸው ከትልቅ ወደ ትንሽ ዘርዝሩ::
3. ጨረቃ ያላቸውንና ጨረቃ አልባዎቹን ፈለኮች ለይታችሁ ዘርዝሯቸው:: ከፍተኛ የጨረቃ ብዛት ያላቸው ፈለኮች የትኞቹ ናቸው? አነስተኛ ቁጥር ያላቸውስ?

**ሠንጠረዥ 1 - ፈለኮችና ዋና ዋና ባህርያቸው**

| ተ.ቁ | ፈለክ | ከፀሀይ ያለው አማካይ ርቀት (በሚሊዮን ኪ.ሜ.) | የሰቅ ዳያሜትር (በኪ.ሜ.) | የውጫዊው አካል ልከ ሙቀት (በዲግሪ ሴ.ግሬድ) | የሽክርክሪት ጊዜ | የዙሪት ጊዜ | የጨረቃ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሜርኩሪ | 58 | 4854 | 400 | 59 ቀናት | 88 ቀናት | 0 |
| 2 | ቬነስ | 108 | 12112 | 475 | 243 ቀናት | 225 ቀናት | 0 |
| 3 | መሬት | 150 | 12756 | 13-15 | 23 ሰዓት ከ56 ደቂቃ | 365¼ ቀናት | 1 |
| 4 | ማርስ | 228 | 6788 | -20 | 24 ሰዓት ከ37 ደቂቃ | 687ቀናት | 2 |
| 5 | ጁፒተር | 778 | 143000 | -150 | 9 ሰዓት ከ45 ደቂቃ | 12ዓመት | 16 |
| 6 | ሳተርን | 1,427 | 121000 | -170 | 10 ሰዓት ከ15 ደቂቃ | 29½ዓመት | 21 |
| 7 | ኡራኑስ | 2,866 | 47000 | -210 | 16 ሰዓት | 84 ዓመት | 15 |
| 8 | ኔፕቱን | 4,492 | 46529 | -230 | 18 ሰዓት | 165 ዓመት | 2 |

ማስታወሻ፦ ከላይ በሠንጠረዡ ውስጥ እንደሚታየው ለፀሀይ የምትቀርበው ፕላኔት ሜርኩሪ ሆና ሳለች ነገር ግን የቬነስ ልክ ሙቀት ከሜርኩሪ የበለጠ ነው። ለዚህም ምክንያቱ የቬነስ ከባቢ አየር ሙቀትን አምቆ መያዝ የሚያስችል ከፍተኛ እፍግታ (Density) ያለው በመሆኑ ነው።

ተማሪዎች! ቀደም ሲል የተጻፉ መጻህፍት ፕሉቶን ጨምሮ የፈለኮች ብዛት ዘጠኝ እንደሆነ የሚገልጹ ናቸው። ነገር ግን የዓለም ዓቀፍ የጠፈር ሳይንቲስቶች ሕብረት እ.አ.አ በ2006 ዓ.ም ፕሉቶ የፈለኮችን መስፈርት ስለማታሟላ ከፈለኮች ዝርዝር ውስጥ እንድትሰረዝ ወስኗል። ለዚህም ዋናው ምክንያት ፕሉቶ እንደሌሎቹ ፈለኮች በፀሀይ ዙሪያ የራሷ ምህዋር የሌላትና ከሌሎች በርካታ አካላት ስብስብ ውስጥ የምትገኝ መሆኗ በመረጋገጡ ነው። በስርዓተ ፀሀይ ውስጥ ከፀሀይ እና ከፈለኮች በተጨማሪ ሌሎች አካላት ይገኛሉ። እነዚህ የስርዓተ ፀሀይ አባላት እንግዳ ሊሆኑባችሁ እንደሚችሉ በመገመት ተገቢውን ግንዛቤ ትጨብጡ ዘንድ ቀጣዮቹ ምስሎችና ማብራሪያዎች ቀርበውላችኋል።

ሀ) ኮሜቶች (Comets) - ኮሜቶች በጠፈር ውስጥ የሚገኙ ጠጣር አካላት ናቸው። በመጠን የተለያዩና የራሳቸው ምህዋር ያላቸው ናቸው። የሚያንጸባርቅ ከጋዝ የተሰራ ጅራት ሲኖራቸው አንዳንዶቹ በረጅም ዓመታት ውስጥ ለመሬት ቀርበው ይታያሉ (ለምሳሌ፦ የሀሌ ኮሜት በየ76 ዓመት ልዩነት ለመሬት ቀርባ ትታያለች)።

ለ) ሚቲዮሮች/ተወርዋሪ ኮከቦች (Meteors) - እነዚህም ጠጣር አካላት ሲሆኑ በልማድ ተወርዋሪ ኮከብ በመባል ይታወቃሉ። እነዚህ አካላት በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ሲሆኑ አንዳንዶቹ በየራሳቸው ምህዋር ላይ ፀሀይን ሲዞሩ የተቀሩት ደግሞ እጅብ ብለው ፀሀይን ይዞራሉ። ሚቲዮሮች በመሬት ከባቢ አየር ውስጥ ሲገቡ ተቃጥለው አመድ ይሆናሉ። በጣም ትልልቅ የሆኑ ሚቲዮሮች ግን መሬት ላይ ሊወድቁ ይችላሉ። መሬት ላይ የሚያርፉት ሚቲዮሮች ሚቲዮራይት (Meteorite) ይባላሉ።

ሐ) ትንንሽ ፈለኮች - እነዚህ አካላት ፕላኔቶይድስ /Planetoides/ ወይም አስቴሮይድስ /Aesteroids/ በመባልም የሚታወቁ ሲሆን የሚገኙት በማርስና በጁፒተር ምህዋሮች መካከል ነው። ፕላኔቶይድስ የተፈጠሩት በተጠቀሱት ፕላኔቶች መካከል የነበረ አንድ ግዙፍ ፕላኔት በመሰባበሩ ምክንያት እንደሆነ ይገመታል። እያንዳንዱ ፕላኔቶይድ በፀሀይ ዙሪያ ሲጓዝ የራሱን ምህዋር ተከትሎ ነው።

ተማሪዎች! በምሽት ጊዜ ጨረቃ ታበራለች፤ እንዲሁም ጨረቃ ላይ ሆነን መሬትን ስንመለከታት ልክ እንደ ጨረቃ ብርሀን ትፈነጥቃለች። ይህ ጨረቃና መሬት

የሚለቁት ብርሀን ምንጩ ምን እንደሆነ አስባችሁት ታውቃላችሁ? እስኪ ለተወሰኑ ደቂቃዎች በየግላችሁ አስቡበት፣ ከዚያም ሀሳባችሁን ለመምህራችሁ ግለጹላቸውና በጉዳዩ ላይ ተወያዩበት::




ምስል 5 - ኮሜቶች፣ ሚቲዮሮች፣ ትንንሽ ፈለኮችና ስብርባሪ ኮከቦች



ምስል 6 - የሚቲዮራይቶች ናሙናዎች

### ውስን ጥናት (Case Study)

ኪሩቤል የሚባል የ13 ዓመት የ6ኛ ክፍል ተማሪ ከጎንደር ወደ አዲስ አበባ ከአባቱ ጋር ለመጓዝ ቲኬት ቆርጠው ስለነበር ሌሊቱ ሊነጋጋ ሲል ወደ መናኸሪያ ለመሄድ ከቤታቸው ወጡ። በጉዟቸው ወቅት ኪሩቤል ወደ ሰማይ ሲመለከት በሰማይ ላይ ከሚታዩት አካላት መካከል እጅግ ውብ የሆነች በጣም ብሩህና ቀላ ያለ ደማቅ ብርሀን የምትፈነጥቅ የጠፈር አካል እይታው ውስጥ ትገባለች። በመገረም ስሜት አንጋጦ እየተመለከታት አባቱን ‘ይህች ከሌሎቹ አካላት ሁሉ በጣም ብሩህ እና ማራኪ የሆነች የጠፈር አካል ምንድን ናት’? ሲል ይጠይቀዋል። አባቱም ይህች ሊነጋጋ ሲል ለእኛ ብሩህ ሆናና ደምቃ በሰማይ ላይ የምትታየን አካል አጥቢያ ኮከብ (የንጋት ኮከብ) ነው የምትባለው ሲል መለሰለት። በአጋጣሚ በተሳፈሩበት ባጃጅ ላይ አብራቸው የምትጓዝ አንዲት መንገደኛ መምህርት ነበረችና ጭውውታቸውን ካዳመጠች በኋላ ‘አይ! ይህች የምትነጋገሩባት የጠፈር አካል በልማድ እንደዚያ ተብላ ትጠራለች እንጂ እውነተኛ ኮከብ አይደለችም። እንዲያውም ባይገርማችሁ ለመሬት ቅርብ የሆነች ፕላኔት ናት’ አለቻቸው።

### ተግባር-8

1. እናንተስ ለእርሻ ስራ፣ ለጉዞ ወይም የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን ሌሊቱ ሊነጋጋ አካባቢ ስትንቀሳቀሱ ይህችን የጠፈር አካል አይታችኋት ይሆን? ካያችኋት ምን ትመስላለች? ከሌሎቹ አካላት ለየት ስለምትል ምን ዓይነት ስሜት ትፈጥርባችኋለች?
2. አባትየው በሰጠው ምላሽ መሰረት ይህች አካል ኮከብ ለመሆኗ ትስማማላችሁ ወይስ አትስማሙም? ለምን?

# 1.4. የመሬት አፈጣጠር እና ዝግመተ ለውጥ (Evolution)

የመሬትን ታሪካዊ አመጣጥ ሂደት ለመተንተን የምንጠቀምባቸው ዘመናት የተከፋፈሉት መሬት በፈለክነት ከተፈጠረችበት ጊዜ ጀምሮ ያሉትን የእንስሳትንና የእጽዋትን ቅሪተ-አካሎች (Fossils) በመመርመር ነው።

### ሀ)ቅድመ ዘመነ ህይወት /Pre-Cambrian Era/ (ከ4.6 ቢሊዮን - 600 ሚሊዮን ዓመት)


ይህ ክፍለ ዘመን 90% የሚሆነውን የመሬትን ዝግመታዊ ለውጥ ታሪክ (ጊዜ) የሚሸፍን ነው። በዚህ ዘመን የተከናወኑት ዋና ዋና ስነ ምድራዊ ክስተቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ስርዓተ ፀሐይ በዚህ ዘመን መጀመሪያ ላይ እንደተፈጠረ ይገመታል።
- የመሬት ጨረቃ በዚህ ዘመን ተፈጠረች።

### ለ)ዘመነ ጥንተ ህይወት /Paleozoic Era/ (ከ600 ሚሊዮን - 225 ሚሊዮን ዓመት)

በዚህ ክፍለ ዘመን የተከናወኑት ቀጥሎ የተዘረዘሩት ዋና ዋና ስነ ምድራዊ ክስተቶች ናቸው፡-

- የሰሜኖቹ አህጉራት ማለትም ሎሬሽያ፣ ባልቲክና ሳይቤሪያ ሲነጣጠሉ የደቡቦቹ አህጉራት (ተጠቃለው ጎንድዋናላንድ ይባላሉ) ወደ ደቡብ መንሸራተት ቀጠሉ። በመሬት ሰቅ አካባቢ ደግሞ ግዙፉ አህጉር ፓንጂያ (Pangaea) በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ መላተም ምክንያት ተፈጠረ።





ምስል 7 - ፓንጂያ

### ሐ)ዘመነ ማዕከላዊ ህይወት /Mesozoic Era/ (ከ225 ሚሊዮን - 70 ሚሊዮን ዓመት)

በዚህ ክፍለ ዘመን የሚከተሉት ስነ ምድራዊ ክስተቶች ተከስተዋል፦

- ፓንጂያ ሙሉ በሙሉ ወደ አሁኖቹ አህጉራት ተከፋፈለ:: ይሁን እንጂ አህጉራቱ የአሁኑን አቀማመጣቸውን አልያዙም ነበር::
- አትላንቲክና ህንድ ውቅያኖሶች ተፈጠሩ::
- በሰሜን አሜሪካና በአውሮፓ መካከል ባህር ተፈጠረ::





ምስል 8- የፓንጂያ መከፋፈል መጀመር

### መ)ሰብዓ ዘመን /Cenozoic Era/ (ከዛሬ 70 ሚሊዮን ዓመት እስከ አሁን)

በዚህ ዘመን የተከናወኑት አብይ ስነ ምድራዊ ክስተቶች የሚከተሉት ናቸው፦

- አህጉራት አሁን ወደሚገኙበት ቦታቸው መንሸራተታቸውን ቀጠሉ::
- ቀስ በቀስ ግሪንላንድና ሰሜን አሜሪካ መለያየት ጀመሩ::
- የሰሜኑ ግዙፍ አህጉር ሎሬሽያ መከፋፈል ጀመረ::
- አፍሪካ ከአንታርክቲካ ተለይቶ ወደ ሰሜን መንሸራተት ቀጠለ::
- ደቡብ አሜሪካና ሰሜን አሜሪካ በፓናማ ተፈጥሯዊ የመሬት ድልድይ ተገናኙ::




ምስል 9 - የጎንድዋናላንድና የሎሬሽያ መከፋፈል

## 1.5. የመሬት መገኛ (Position) እና ቅርጽ (Shape)

መሬት የምትገኝበት ረጨት ፍኖተ ሀሊብ ረጨት እንደሚባል ቀደም ሲል መገለጹ ይታወሳል:: መሬት አንድ መቶ ቢሊየን ከሚሆኑ የፍኖተ ሀሊብ ረጨት ከዋክብት መካከል በአንደኛዋ ዙሪያ የምትንቀሳቀስ ፕላኔት ናት:: ይህች ኮከብ ማን ትባላለች?

### ተግባር-9

1. መሬት ለፀሀይ በስንተኛ ደረጃ ቀርባ ትገኛለች?
2. መሬት የምትገኘው በየትኞቹ ፈለኮች መካከል ነው?
3. መሬት በፀሀይ ዙሪያ በራሷ ምህዋር ላይ ዙሪት ታከናውናለች:: የዚህ ምህዋር ቅርፅ ምን ዓይነት ነው? ክብ፣ ሞላላ ወይስ ሌላ?

ተማሪዎች! ከላይ የተሰጣችሁን ተግባር ባግባቡ ካከናወናችሁ መሬት በስርዓተ ፀሀይ ውስጥ የምትገኝበትን አቀማመጥ በተመለከተ ተገቢውን ግንዛቤ እንደጨበጣችሁ ይታመናል:: እስኪ ከታች የቀረበውን ምስል ደግሞ መርምራችሁ የመሬት ቅርጽ ምን ዓይነት ነው? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት ሞክሩ::



ምስል 10 - የመሬት ቅርፅ ከጠፈር ሲታይ

ሳይንስና ቴክኖሎጅ ባልተስፋፋበት በጥንት ዘመን መሬት ጠፍጣፋና የመጨረሻ ጠርዝ ያላት እንደሆነች ይታመን ነበር፡፡ የግሪኮች ስልጣኔ በመጠቀበት ዘመን ደግሞ መሬት እንደ ኳስ የተድበለበለች ናት የሚለው አስተያየት እያመዘነ መጣ፡፡ ይሁን እንጂ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ1519 - 1522 ዓ.ም ባሉት ዓመታት ማጅላን የተባለው አሳሽ (Explorer) ከስፔን ተነስቶ ዓለምን ለመዞር በጉዞ ላይ ሳለ ህይወቱ ሲያልፍ አብረውት የነበሩት ተጓዦች ጉዟቸውን አጠናቀው ተመልሰው ስፔን መግባት በመቻላቸው መሬት ጠፍጣፋና የመጨረሻ ጠርዝ ያላት አካል አለመሆኗን አረጋግጡ፡፡

## ተግባር-10

1. ከማጅላን ህልፈተ ህይወት በኂላ አብረውት የነበሩት አሳሾች ተመልሰው ስፔን ሊገቡ ችለዋል፡፡ እነዚህ አሳሾች ምን ዓይነት ቅርጽ ባለው አካል ላይ ቢጓዙ ነው ከተነሱበት ቦታ ተመልሰው ሊመጡ የቻሉት?
2. ከመሬት ወደ ላይ ከፍታችን ሲጨምር ከፊት ለፊታችን የምናየው የመሬት ክፍል ሽፋኑ ይጨምራል፡፡ ከፍታችን ሲቀንስ ደግሞ የእይታ አድማሳችን ይቀንሳል፡፡ ከከፍታ ጋር በተያያዘ የእይታ አድማሳችን የሚቀያየረው ለምንድን ነው?

ተማሪዎች! ከላይ ባከናወናችኋቸው ተግባራት የመሬት ቅርፅ ምን ዓይነት እንደሆነ ግንዛቤ እንደጨበጣችሁ ይታመናል። የዚህ ዓይነቱ ቅርፅ ኦብሌት ስፌር ወይም ኦብሌት ኢሊፕሶይድ (Oblate Sphere or Oblate ellipsoid) በመባል ይታወቃል። ከዚህ ቅርፅ የምንረዳው መሬት እንደ ኳስ ፍፁም የተድበለበለች ሳትሆን በዋልታዎች አካባቢ ጠፍጠፍ ያለችና በምድር ሰቁ አካባቢ ደግሞ የምትለጠጥ መሆኗን ነው።

የመሬት የክብ ዙሪያዋ ርዝማኔ መጠነ ዙሪያ (Circumference) ይባላል። የመሬት ጠቅላላ ስፋት 510.7 ሚሊዮን ስኩየር ኪሎ ሜትር ሲሆን ከዚህ ውስጥ 71%ቱ በውሃ የተሸፈነ፤ 29%ቱ ደግሞ በየብስ የተያዘ ነው። የመሬት ዲያሜትር በዋልታዎች መካከልና በምድር ወገብ ላይ መጠኑ ይለያያል። የመሬት ዋልታዊ ዲያሜትር (Polar Diameter) 12714 ኪሎ ሜትር ሲሆን የምድር ወገብ ዲያሜትር (Equatorial Diameter) ደግሞ 12756 ኪሎ ሜትር ነው። ዋልታዊ ዲያሜትር ከሰሜን ዋልታ እስከ ደቡብ ዋልታ መሬትን ውስጥ ለውስጥ የሚያቋርጠው መስመር ርዝመት ሲሆን የምድር ወገብ ዲያሜትር ደግሞ መሬትን ውስጥ ለውስጥ እኩል ለሁለት ከፍሎ ወደ ጎን የሚያቋርጠው መስመር ርዝመት ነው።

## 1.6. የመሬት እንቅስቃሴዎችና የሚያስከትሏቸው ውጤቶች

*መሬት፦*

1. ከፍኖተ ሐሊብ አባላት ጋር በመሆን በሁለንታ ውስጥ ትንቀሳቀሳለች።
2. ከስርዓተ ፀሀይ አባላት ጋር በመሆን በፍኖተ ሐሊብ ረጨት ማእከል ዙሪያ ዙሪት (Revolution) ታከናውናለች።
3. ከሌሎች ፈለኮችና ጨረቃዎች ጋር ፀሀይን ማእከል በማድረግ ዙሪት ታካሂዳለች።
4. በራሷ ዛቢያ (Axis) ላይ ሽክርክሪት (Rotation) ታከናውናለች።

ውድ ተማሪዎች! ከላይ ከተዘረዘሩት የእንቅስቃሴ አይነቶች መካከል ከመሬት ስፌራዊ ቅርፅ ጋር ተዳምረው ጉልህና ጠቃሚ ክስተቶች የሚፈጥሩት ሽክርክሪትና ዙሪት በመሆናቸው በቀጣይ እነዚህን እንቅስቃሴዎች እንመረምራለን።

### 1. የመሬት ሽክርክሪት (Rotation)

ተማሪዎች! እናቶች ጥጥ ሲፈትሉ እንዝርቱ እንዴት እንደሚሾር ልብ ብላችሁ አይታችሁ ከሆነ የመሬት ሽክርክሪትን ጽንሰ ሐሳብ በቀላሉ ልትጨብጡት ትችላላችሁ።





ምስል 11 - የመሬት ሽክርክሪት

## ተግባር-11

1. በምስል 11 ላይ በተቀመጠው መሰረት የመሬት ሽክርክሪት አቅጣጫ ከየት ወደ የት ነው?
2. እናንተ ጠዋት ከመኝታችሁ ስትነሱ አሜሪካን አገር የሚገኙ አቻዎቻችሁ በእንቅልፍ ላይ ሲገኙ ቻይናውያንና ጃፓናውያን ተማሪዎች ደግሞ በትምህርት ቤታቸው ቅጥር ግቢ ውስጥ ነው የሚገኙት። ይህ እለታዊ የውሎ ልዩነት በመካከላችሁ የተፈጠረው በምን ምክንያት ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?
2. በመኪና ተሳፍራችሁ በምትጓዙበት ጊዜ መኪናው ወደ ፊት በፍጥነት ሲሽከረከር በመሬት ላይ የምታዩአቸው ዛፎች እና የቆሙ ሰዎች ምን ዓይነት እንቅስቃሴ ያሳያሉ? የዚህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ ከመሬት ሽክርክሪትና ከፀሀይ አንጻራዊ እንቅስቃሴ ጋር (ለምሳሌ፦ ፀሀይ በምስራቅ ትወጣለች፣ በምእራብ ትጠልቃለች) ያለውን ዝምድና እንዴት ትገመግሙታላችሁ? እስኪ በጥንድ በጥንድ በመሆን ተወያዩበትና ምላሾቻችሁን ሌሎች ጓደኞቻችሁ ከደረሱበት ድምዳሜ ጋር ለማነጻጸር ሞክሩ።

ተማሪዎች! ቀጥሎ ከላይ ካከናወናችሁት ተግባር ጋር ዝምድና ያለው ምስል ቀርቦላችኋል። ምስሉን በጥሞና ከመረመራችሁ በኋላ ተከታዮቹን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሩ።




ምስል 12 - የመሬት ሽክርክሪት አቅጣጫ ከሰሜንና ደቡብ ዋልታዎች ሲታይ

## ተግባር-12

1. ሰሜን ዋልታ ላይ ሆነህ (ሽ) ወደ ደቡብ አቅጣጫ ስትመለከት (ቺ) የመሬት ሽክርክሪት በሰዓታዊ አዟዟር እንዴት ይገለፃል? ደቡብ ዋልታ ላይ ሆነህ(ሽ) ወደ ሰሜን አቅጣጫ ስትመለከት(ቺ)ስ?
2. መሬት በሰዓት ምን ያህል ዲግሪ ኬንትሮስ ትሽከረከራለች?


የመሬት ሽክርክሪት የሚያስከትላቸው ዋና ዋና ክስተቶች የቀንና ሌሊት መፈራረቅ፣

የፀሀይ ከምስራቅ ወደ ምእራብ አቅጣጫ የምትንቀሳቀስ መምሰል፣ የውቅያኖስ ፍሰትና የንፋስ አቅጣጫ መቀየር ናቸው።

## 2. የመሬት ዙሪት (Revolution)

ውድ ተማሪዎች! በቤታችሁ መስኮት ወይም በር የሚገባው የፀሀይ ጨረር በተለያየ ወቅት አቅጣጫውን እንደሚቀያይር ልብ ብላችሁ ታውቃላችሁ? በአንድ ወቅት የቀኑ ብርሀን ረዝሞ የሚጨልምበት ሰዓት ሲዘገይባችሁ በሌላ ወቅት ደግሞ ሌሊቱ ረዝሞባችሁ ቶሎ አልነጋ ብሏችሁ ያውቃል? ለምን ይመስላችኋል? ይህ ክስተት በቀጥታ ከመሬት ዙሪት ጋር የተያያዘ ነው።

መሬት በምህዋሯ ላይ በፀሀይ ዙሪያ የምታደርገው ጉዞ ዙሪት (Revolution) ይባላል። መሬት በፀሀይ ዙሪያ ስትዞር ከፀሀይ የሚኖራት ርቀት በተለያዩ ጊዜያት የተለያየ ነው። ለምሳሌ፦ በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ታህሳስ 25 ቀን አካባቢ መሬት ለፀሀይ በጣም ትቀርባለች (147,100,000 ኪ.ሜ)፤ ክስተቱም ቅርበ ፀሀይ (Perihelion) ይባላል። በተቃራኒው ሰኔ 28 ቀን አካባቢ መሬት ከፀሀይ በጣም ርቃ ትገኛለች (152,600,000 ኪ.ሜ)። ይህም ክስተት ሩቀ ፀሀይ (Aphelion) በመባል ይታወቃል።





ምስል 13 - መሬት በሰኔ እና በታህሳስ ላይ ከፀሀይ የሚኖራት ርቀት

## ተግባር-13

ምስል 13ን በሚገባ ከመረመራችሁ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ መልሱ::


1. የመሬት ምህዋር ቅርፅ ምን ዓይነት ሁኔታን ይፈጥራል?
2. መሬት ፀሀይን አንድ ጊዜ ለመዞር የሚወስድባት ጊዜ ምን ያህል ነው?
3. መሬት ከፀሐይ የሚኖራትን አማካይ ርቀት አስሉ::

የመሬት ዛቢያ ከምህዋሯ ፕሌን አንፃር በ66½$^0$ አንግል ወይም ከቀጥተኛው የመሬት አቀማመጥ በ23½$^0$ ያጋደለ ነው:: በተጨማሪ የመሬት ሰሜናዊ ጫፏ ሁል ጊዜ ወደ አንድ አቅጣጫ ማለትም ወደ ሰሜን ኮከብ ያመለክታል (ምስል 14ን ተመልከቱ):: የመሬት ዙሪት ከእነዚህ የመሬት ዛቢያ አቀማመጥ ጋር በመቀናጀት የተለያዩ ክስተቶችን ይፈጥራል:: ክስተቶቹ ምን ምን ይመስሏችኋል?




ምስል 14 - የመሬት ዛቢያ

መሬት በፀሀይ ዙሪያ በምህዋሯ ላይ ስትዞር ሶስት ሁኔታዎች ይከሰታሉ:: እነርሱም የፀሀይ ከሰሜን ወደ ደቡብ እና ከደቡብ ወደ ሰሜን አቅጣጫ የምትጓዝ መስሎ መታየት (መሬት ዙሪት ስታከናውን ፀሀይ ከምድር ወገብ በአንድ ወቅት ወደ ሰሜናዊ ንፍቀ ክበብ በሌላ ጊዜ ደግሞ ወደ ደቡባዊ ንፍቀ ክበብ የምትንቀሳቀስ ይመስለናል)፣ የቀኑ ርዝማኔ በዓለም ላይ በተለያዩ ጊዜያት መለያየት እና የወቅቶች መፈራረቅ ናቸው::




ምስል 15 - የወቅቶች መፈራረቅ

ተማሪዎች! በምስል 15 ላይ እንደሚታየው በመስከረም ወር መሬት ሙሉ በሙሉ ጨለማ እንደሆነች አድርጋችሁ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዳትጨብጡ ጥንቃቄ ልታደርጉ ይገባል:: ጨለማው የሚያመለክተው ከፀሀይ በተቃራኒ አቅጣጫ የሚገኘውን ግማሹን የመሬት ክፍል ብቻ ነው:: ለፀሀይ ትይዩ የሆነው በውስጥ በኩል ያለው ሌላኛው ግማሹ የመሬት ክፍል ግን ብርሀን የሚያገኝ ነው:: ቀጥሎ በመሬት ዙሪት ምክንያት በሚፈጠሩ ክስተቶች ላይ አጠቃላይ ግንዛቤ ለመጨበጥ የሚረዷችሁ የተግባር ጥያቄዎች ቀርበውላችኋል::

## ተግባር-14

1. ፀሀይ በካንሰርና በካፕሪኮርን መስመሮች እንዲሁም በምድር ሰቅ (ወገብ) በአናት ላይ ($90^0$) የምትሆነው መቼ ነው?
2. በአጠቃላይ ከዚህ ከሰሜን - ደቡብ እና ከደቡብ - ሰሜን መሰል የፀሀይ እንቅስቃሴ ምን እንደተገነዘባችሁ አብራሩ::
3. የሚከተለውን ሰንጠረዥ በየደብተራችሁ ላይ ካሰፈራችሁ በኋላ የተገለጹት ሶስት ሶስት ወራት በየንፍቀ ክበቡ የሚወክሉትን ወቅት አመልክቱ:: በመቀጠል በየወቅቶቹ የቀኑንና የሌሊቱን መርዘምና ማጠር በተመለከተ ንጽጽራዊ መግለጫ እየሰጣችሁ አንድ የማጠቃለያ ጽሁፍ አዘጋጁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ገለጻ አድርጉ::


| ተ.ቁ | ወሮች | ሰሜናዊ ንፍቀ ክበብ | ደቡባዊ ንፍቀ ክበብ |
|---|---|---|---|
| | | ወቅት | ወቅት |
| 1 | ሰኔ<br>ሐምሌ<br>ነሐሴ | | |
| 2 | መስከረም<br>ጥቅምት<br>ህዳር | | |
| 3 | ታህሣሥ<br>ጥር<br>የካቲት | | |
| 4 | መጋቢት<br>ሚያዝያ<br>ግንቦት | | |

## 1.7. የጊዜ ስሌት

እያንዳንዱ በመሬት ላይ ያለ ቦታ የራሱ የሆነ የፀሀይ መውጫና መግቢያ (መጥለቂያ) ጊዜ አለው:: ይህም አካባቢያዊ ጊዜ (Local Time) በመባል ይታወቃል:: ነገር ግን አካባቢያዊ ጊዜን በመጠቀም አገራዊም ሆነ ዓለም አቀፋዊ ግንኙነት ለማድረግ በጣም አስቸጋሪ ነው:: ለምን ይመስላችኋል? ስለዚህ ዓለም በመደበኛ የጊዜ ክልሎች (Standard Time Zones) የተከፋፈለች ናት::

### *ተግባር-15*

1. መሬት በየሰዓቱ በምታደርገው ሽክርክሪት በምትሸፍናቸው ዲግሪዎች መሰረት ብትከፋፈል ስንት የመሬት ክልሎች ይኖራሉ? ይህ ክፍፍል ከሰዓት አቆጣጠር ጋር ያለው ግንኙነትና ጠቀሜታው ምንድን ነው?




ምስል 16 - የዓለም መደበኛ የጊዜ ክልሎች

ለጊዜ ስሌት መሰረቱ የመሬት ሽክርክሪት ነው:: ስለዚህ የመሬት ሽክርክሪት ጊዜን ለማስላት ያገለግላል:: መሬት በ24 ሰዓታት ውስጥ አንድ ሽክርክሪት ታከናውናለች:: ይህም ማለት በመሬት ላይ የሚገኝ አንድ ነጥብ በአንድ ሽክርክሪት ወቅት አንድ ሙሉ ክብ ይሰራል ማለት ነው:: አንድ ሙሉ ክብ ደግሞ $360^0$ ነው::

## ተግባር-16

ከላይ በቀረቡት ምስሎችና መረጃዎች ላይ በመመስረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፦

1. መደበኛ የጊዜ ክልሎች (Standard Time Zones) ምንድን ናቸው?
2. ዓለም አቀፋዊ የቀን መለያ መስመር (The International Date Line) ምንድን ነው? በስንት ዲግሪ ኬንትሮስ ላይ ይገኛል?

ዓለም በ24 የጊዜ ክልሎች ተከፋፍላለች:: እያንዳንዱ የጊዜ ክልል ወርዱ (ጎኑ) $15^0$ ነው:: የእያንዳንዱን የጊዜ ክልል ድንበር (መስመር) ወደ ምስራቅ ስናቋርጥ በመነሻ ሰዓታችን ላይ 1 ሰዓት ስንጨምር ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ስናቋርጥ ደግሞ ከመነሻ ሰዓታችን ላይ 1 ሰዓት እንቀንሳለን:: መሬት አንድ ሽክርክሪት ($360^0$) ለመፈጸም 24 ሰዓት ይወስድባታል:: ታዲያ በ1 ሰዓት ውስጥ ስንት ዲግሪ ኬንትሮስ ትሾራለች?

24 ሰ = $360^0$ ኬንትሮስ

1 ሰ = ?

$$\frac{360^0 \times 1}{24\ ሰ} = 15^0\ ኬንትሮስ$$

ውድ ተማሪዎች! የሰዓት ስሌት የሚከናወነው ከታች በተቀመጠው ቅደም ተከተል (Step) መሰረት ነው::

ምሳሌ፦ በ$60^0$ ምእራብ ላይ ከጠዋቱ 3 ሰዓት ቢሆን በ$60^0$ ምስራቅ ላይ ስንት ሰዓት ይሆናል?

1. በቅድሚያ በሁለቱ ቦታዎች መካከል ያለውን የዲግሪ ልዩነት መፈለግ

   $60^0 + 60^0 = 120^0$ (ቦታዎቹ በተመሳሳይ ንፍቀ ክበብ ውስጥ የሚገኙ ከሆኑ በመቀነስ፣ ነገር ግን በተለያዩ ንፍቀ ክበቦች ውስጥ የሚገኙ ከሆኑ በመደመር የዲግሪ ልዩነታቸውን ማግኘት ይቻላል)::

2. የተገኘውን የዲግሪ ልዩነት በ$15^0$ ማካፈል፦ $\frac{120^0 \times 1}{15^0} = 8$ ሰዓት

3. የተጠየቀው ቦታ ከመነሻው ወደ ምስራቅ አቅጣጫ ከሆነ የተገኘውን ሰዓት በመነሻው ሰዓት ላይ መደመር፣ ወደ ምእራብ አቅጣጫ ከሆነ ደግሞ ከመነሻው ሰዓት ላይ መቀነስ

   3 ሰ + 8 ሰ = 11 ሰ

☞ ስለዚህ መልሱ ከቀኑ 11 ሰ ይሆናል።

## ተግባር-17

1. በ$0^0$ ኬንትሮስ (ግሪንዊች ሜሪዲያን) ላይ ከምሽቱ 6 ሰዓት ቢሆን በ$90^0$ ምስራቅ ላይ ስንት ሰዓት ይሆናል?
2. ኢትዮጵያ በግሪንዊች አማካይ ጊዜ (Greenwich Mean Time በአጭሩ GMT) +3 ላይ ትገኛለች:: ይህን ሀሳብ ከኢትዮጵያ መገኛ ኬንትሮስ እና ከጊዜ አቆጣጠር አንጻር ትንታኔ ስጡበት::
3. የኢትዮጵያ ምዕራባዊ ጫፍ መገኛ $33^0$ ምስራቅ ሲሆን የምስራቃዊው ጫፍ መገኛ ደግሞ $48^0$ ምስራቅ ነው:: በሁለቱ ቦታዎች መካከል ያለው የሰዓት ልዩነት ስንት ነው?


ዓለም ዓቀፍ የቀን መለያ መስመር (International Date Line) $180^0$ ምእራብና $180^0$ ምስራቅ ኬንትሮስ ላይ የሚገኙ ቋሚ መስመሮች የሚገናኙበት ስፍራ ሲሆን የመጀመሪያው ከፕራይም ሜሪዲያን በ12 ሰዓት ሲዘገይ ሁለተኛው ደግሞ በ12 ሰዓት ይቀድማል። ስለዚህ በምስል 16 ላይ እንደሚታየው ይህን መስመር አቋርጠን ከምስራቅ ወደ ምእራብ አቅጣጫ ስንጓዝ ከመነሻችን አንድ ቀን እንቀንሳለን (ለምሳሌ፦ እሁድ የነበረው ቅዳሜ ይሆናል)። ከምእራብ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ መስመሩን ካቋረጥን ደግሞ አንድ ቀን እንጨምራለን (ለምሳሌ፦ እሁድ የነበረው ሰኞ ይሆናል)።

## 1.8. የመሬት ገፅታዎች

የመሬት ገፅታዎች የሚባሉት በተለያዩ ውስጣዊ (ለምሳሌ፦ ቅልብሽ፣ ዝንፈት፣ ገሞራዊነት) እና ውጫዊ ኃይሎች (ለምሳሌ፦ ሸርሸራ፣ ግጥግጦሽ፣ ክምችት፣ ፍርፈራ) አማካኝነት የተፈጠሩ በላይኛው የመሬት ሽፋን ላይ የሚገኙ የተለያዩ መልክዓ ምድራዊ ቅርጾች ናቸው።

ዋና ዋናዎቹ የመሬት ገጽታዎች አህጉራት፣ ውቅያኖሶች፣ ባህሮች፣ ሐይቆች፣ የታችኛው ከባቢ አየር፣ ሕይወት የሚኖርበት የላይኛው የመሬት ንጣፍ እና ሰው ሰራሽ መልክዓ ምድሮች ናቸው።

አህጉር ከባህር ወለል በላይ የሚገኝ የመሬት ክፍል ነው። አህጉራት ከጠቅላላው የመሬት የቆዳ ስፋት ውስጥ 29% ሲይዙ ውሀማ አካላት ደግሞ 71% ይሸፍናሉ። ገበቶዎች (Plateaus)፣ ሜዳማ ስፍራዎች (Plains)፣ ተራሮች (Mountains) እና ስምጥ ሸለቆዎች (Rift Valleys) በአህጉራት ላይ የሚገኙ አብይ መልክዓ ምድራዊ ገጽታዎች ናቸው።




ምስል 17 - ሰባቱ አህጉራት

**ሠንጠረዥ 2 - የዓለም አህጉራትና ውቅያኖሶች**

| አህጉር | ስፋት በኪ.ሜ$^2$ | ውቅያኖስ | ስፋት በኪ.ሜ$^2$ |
|---|---|---|---|
| እስያ | 44,810,880 | ፓስፊክ (ሰላማዊ) | 165,384,000 |
| አፍሪካ | 30,335,000 | አትላንቲክ | 82,217,000 |
| ሰሜን አሜሪካ | 24,367,875 | ሕንድ | 73,481,000 |
| ደቡብ አሜሪካ | 17,831,606 | አንታርቲክ (ደቡባዊ ውቅያኖስ) | 20,300,000 |
| አንታርክቲካ | 14,002,590 | አርክቲክ | 14,056,000 |
| አውሮፓ | 9,935,233 | | |
| አውስትራሊያ | 8,289,000 | | |
| ዓለም | 149,572,184 | | |


### ተግባር-18

በምስል 17 እና በሰንጠረዥ 2 ላይ በቀረቡት መረጃዎች መሰረት ተከታዮቹን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሩ::

1. ስንት አህጉራት አሉ? ስማቸውንና አንጻራዊ መገኛቸውን ግለጹ::
2. ስንት ውቅያኖሶች አሉ? ስማቸውንና አንጻራዊ መገኛቸውን ግለጹ::
3. በስፋታቸው ከ1ኛ-3ኛ ደረጃ ላይ የሚገኙትን አህጉራትና ውቅያኖሶች ዘርዝሩ::

## 1.9. የመሬት ውስጣዊ አወቃቀር (Internal Structure of the Earth)

የመሬት አወቃቀር ከአቮካዶ ፍሬ ወይም ከተቀቀለ እንቁላል ጋር ተመሳሳይነት አለው:: የአቮካዶ ፍሬ ወይም የተቀቀለ እንቁላል ሶስት ንብርብሮች ወይም ንጣፎች አሉት:: እነዚህ ንብርብሮችም ከላይ ወደ ታች ስስ ቅርፊት፣ አረንጓዴ/ነጭ ንጣፍ እና ድቡልቡል ዘር/አስኳል ናቸው:: በምስል 18 ላይ እንደሚታየው የመሬት አወቃቀርም እንደዚሁ በሶስት ንብርብሮች የተገነባ ነው:: እነዚህ የመሬት ንብርብሮች ምን ተብለው ይጠራሉ? መገኛቸው፣ መጠናቸውና ባህሪያቸውስ እንዴት ይገለጻል?




ምስል 18 - የመሬት ንብርብሮች

### ሀ) ቅርፊተ መሬት/ቅራፎ (Crust)

ቅርፊተ መሬት የአፈር፣ የደለል፣ የጨው፣ የጋዞች፣ የጨው አልባና ጨዋማ ውሃዎች መገኛ የሆነ የላይኛው የመሬት ንብር ወይም ንጣፍ ነው፡፡ የቅርፊተ መሬት ውፍረት በውቅያኖስ ስር ከ5 - 7 ኪ.ሜ ሲሆን በየብስ ስር ደግሞ ከ30- 65 ኪ.ሜ ይደርሳል፡፡ ይዘቱ (Volume) የመሬትን 1 - 2%፣ መጠነ ቁሱ የመሬትን 1%፣ ልከ ሙቀቱ በጣም ዝቅተኛ እና የተሰራባቸው ዋና ዋና ቁሶች ደግሞ ሲልካ፣ አልሙኒየምና ማግኒዥየም ናቸው፡፡

### ለ) ማእከለ መሬት/ልጤ መሬት (Mantle)

ማእከለ መሬት በጉተንበርግ ተቋርጦሽ ከመሬት ቡጥ በመለየት ወደ ውጭ እስከ ቅራፎ ተዘርግቶ ይገኛል፡፡ ማእከለ መሬት ጥልቀቱ 2885 ኪ.ሜ፣ ይዘቱ የመሬትን 82-84%፣ መጠነ ቁሱ የመሬትን 67-68%፣ ልከ ሙቀቱ 3700 ዲግሪ ሴልሸየስ እንዲሁም የተሰራባቸው ቁሶች ብረት፣ የማግኒዥየም ኦክሳይዶችና ሲልካ ንጥረ ነገሮች እንደሆኑ ይገመታል፡፡ ልጤ መሬትን ከቅራፎ የሚለየው ተቋርጦሽ የሞሆ ወይም የኤም ተቋርጦሽ (Moho Discontinuity) ተብሎ ይጠራል፡፡

### ሐ) እምብርተ መሬት/የመሬት ቡጥ (core)

እምብርተ መሬት ውስጣዊው የመሬት ንጣፍ ሲሆን ይዘቱ የመሬትን 15-16%፣ መጠነ ቁሱ የመሬትን 31-33%፣ ልከ ሙቀቱ ደግሞ ከ2500 - 4300 ዲግሪ ሴልሸየስ ይደርሳል፡፡ እምብርተ መሬት በሁለት ይከፈላል፡፡ እነርሱም ውጨኛው እምብርተ መሬትና ውስጠኛው እምብርተ መሬት ናቸው፡፡ ውጨኛው እምብርተ መሬት የተሰራው በከፊል ከቀለጠ ብረትና ኒኬል ሲሆን ጥልቀቱ ደግሞ 6371 ኪሎ ሜትር እንደሆነ ይገመታል፡፡ የሙቀት መጠኑ ደግሞ 6000 ዲግሪ ሴልሸየስ አካባቢ ነው፡፡ ውስጠኛው እምብርተ መሬት የተገነባው ከጠጣር ብረትና ኒኬል ነው፡፡

## ማጠቃለያ

- የህብረተሰብ ትምህርት (Social Studies) የሰው ልጅ እርስ በርሱና በአካባቢው ከሚገኙ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ክስተቶች ጋር የሚያደርገውን መስተጋብር የሚያጠና የትምህርት ዓይነት ነው። ይህ የትምህርት ዓይነት ከተለያዩ የማህበራዊ ሳይንስ (Social Science) የትምህርት ዘርፎች (ለምሳሌ፦ ጂኦግራፊ፣ ታሪክ፣ ምጣኔ ሀብት፣ ፍልስፍና፣ ህግ፣ ወዘተ) ውስጥ የተመረጡ ቀለል ያሉ ይዘቶችን ያካተተ ነው።

- ሁለንታ ማለት ሁሉንም ቁስ አካላት አጠቃሎ የያዘ እጅግ በጣም ሰፊና ወሰን የለሽ ወይም ድንበር የለሽ ስፍራ ነው። ሁለንታን ሙሉ በሙሉ ማየት አይቻልም። በፍኖተ ሐሊብ ውስጥ ከሚገኙት በብዙ መቶ ቢሊዮን ከሚቆጠሩ ከዋክብት መካከል አንዷ ፀሀይ ናት። ፀሀይ የስርዓተ ፀሀይ ማእከል ናት። በስርዓተ ፀሀይ ውስጥ ከፀሀይ እና ከፈለኮች (Planets) በተጨማሪ ትንንሽ ፈለኮች (Aesteroids)፣ ተወርዋሪ ኮከቦች (Meteors)፣ ጅራታም ኮከቦች፣ ኮሜቶች እና ስብርባሪ ኮከቦች (Meteoroids) ይገኛሉ።

- መሬት የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን የምታደርግ ቢሆንም በሰው ልጅ ህይወትና እንቅስቃሴው ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ ያላቸው ግን ሽክርክሪትና ዙሪት ናቸው። መሬት በራሷ ዛቢያ ላይ የምታደርገው እንቅስቃሴ ሽክርክሪት ሲባል በምህዋሯ ላይ በፀሀይ ዙሪያ የምታደርገው ጉዞ ደግሞ ዙሪት ይባላል።

- እያንዳንዱ በመሬት ላይ ያለ ቦታ የራሱ የሆነ ፀሀይ የምትወጣበትና የምትጠልቅበት የራሱ ጊዜ አለው። ይህም አካባቢያዊ ጊዜ (local Time) በመባል ይታወቃል። ነገር ግን አካባቢያዊ ጊዜን በመጠቀም አገራዊም ሆነ ዓለም ዓቀፋዊ ግንኙነት ማካሄድ በጣም አስቸጋሪ ነው። ስለዚህ ዓለም በመደበኛ የጊዜ ክልሎች (Standard Time Zones) የተከፋፈለች ናት።

- የመሬት ገፅታዎች በተለያዩ ውስጣዊ (ለምሳሌ፦ ቅልብሽ፣ ዝንፈት፣ ገሞራዊነት) እና ውጫዊ ኃይሎች (ሸርሸራ፣ ግጥግጦሽ፣ ክምችት፣ ፍርፈራ) አማካኝነት የተፈጠሩ በላይኛው የመሬት ሽፋን ላይ የሚገኙ የተለያዩ መልክዓ ምድራዊ ቅርጾች ናቸው። መሬት እንደተቀቀለ እንቁላል ሶስት ንብርብሮች ወይም ንጣፎች አሏት። እነዚህ ንብርብሮችም ቅርፊተ መሬት (Crust)፣ ልጤ መሬት (Mantle) እና እምብርተ መሬት (Core) ናቸው።

# የክለሳ ጥያቄዎች

ሀ) ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ካልሆነ ሐሰት በማለት መልሱ::

1. የህብረተሰብ ትምህርት ይዘቶች ከማህበራዊ ሳይንስ የትምህርት መስኮች የተውጣጣ ነው::
2. ስርአተ ፀሀይ ሁሉንም ቁስ አካላት አጠቃሎ የያዘ ድንበር የለሽ ስፍራ ነው::
3. ሳተርን ጋዝማ አካል ናት::
4. የመሬት አብዛኛው ክፍል የተሸፈነው በየብስ ነው::
5. ለቀንና ሌሊት መፈራረቅ መንስኤው የመሬት ሽክርክሪት ነው::

ለ) በ'ሀ' አምድ ስር የተዘረዘሩትን በ'ለ' ስር ከተቀመጡት ጋር አዛምዱ::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ረጨት | ሀ) የካንሰር መስመር |
| 2. ሜርኩሪ | ለ) የከዋክብት ክምችት(ስብስብ) |
| 3. ጁፒተር | ሐ) ትልቁ ፕላኔት |
| 4. $23^{1}/2^{0}$ ሰሜን | መ) ጨረቃ አልባ ፕላኔት |
| 5. $23^{1}/2^{0}$ ደቡብ | ሠ) የካፕሪኮርን መስመር |
| | ረ) ፕሮክሲማ ሴንቱዋሪ |

ሐ) ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ::

1. የፀሀይ ቀጥተኛ ጨረር በካንሰር መስመር ላይ የሚሆነው እ.ኢ.አ መቼ ነው?

ሀ) ታህሳስ 15　　ለ) መስከረም 15

ሐ) ሰኔ 15　　መ) መጋቢት 15

2. በአገራችን የቀኑ ርዝማኔ ከሌሊቱ እጅግ የሚበልጠው በየትኛው ወቅት ነው?

   ሀ) በጋ ለ) ክረምት ሐ) መኸር መ) በልግ

3. አንድ መርከብ ሰኞ እለት ከምዕራባዊ ንፍቀ ክበብ ተነስቶ ዓለም ዓቀፍ የቀን መለያ መስመርን ወደ ምስራቅ አቅጣጫ ሲያቋርጥ እለቱ ምን ይሆናል?

   ሀ) እሁድ ለ) ሐሙስ ሐ) ማክሰኞ መ) ቅዳሜ

4. በ45$^0$ ምዕ ላይ ከቀኑ 10 ሰዓት ቢሆን በ45$^0$ ምስ ላይ ስንት ሰዓት ይሆናል?

   ሀ) ከቀኑ 12 ሰዓት ለ) ከምሽቱ 4 ሰዓት

   ሐ) ከምሽቱ 2 ሰዓት መ) ከቀኑ 7 ሰዓት

5. በአውሮፓ እና በሰሜን አሜሪካ መካከል የሚገኘው ውቅያኖስ ማን ይባላል?

   ሀ) ፓስፊክ ለ) አትላንቲክ ሐ) ሕንድ መ) አርክቲክ

መ) ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ፡፡

1. ቅርበ ፀሀይና ሩቀ ፀሀይ የሚፈጠሩበት ዋነኛው ምክንያት ምንድን ነው?
2. የፀሀይ ብርሀን መሬት ለመድረስ ምን ያህል ጊዜ ይወስድበታል?
3. የመሬት ዛቢያ ከቀጥተኛው አቀማመጥ በ23½$^0$ ያጋደለ ባይሆን ኖሮ ምን ዓይነት ክስተት ይፈጠር ነበር?
4. የመሬት ሽክርክሪት የሚያስከትላቸው አብይ ውጤቶች ምን ምን ናቸው?
5. አካባቢያዊ ጊዜን መጠቀም አገራዊም ሆነ ዓለም አቀፋዊ ግንኙነት ለማካሄድ አስቸጋሪ የሚሆንበት ምክንያት ምንድን ነው?

ሠ) ፈታኝ ጥያቄዎች

1. ፕሮክሲማ ሴንቹዋሪ የተባለችው ኮከብ ከመሬት ያላት ርቀት 4.3 የብርሃን ዓመት ነው፡፡ ይህች ኮከብ የምታመነጨው ብርሀን መሬት ለመድረስ ምን ያህል ጊዜ ይወስድበታል?
2. ፕሮክሲማ ሴንቹዋሪ ከመሬት በምን ያህል ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች?

3. ፀሀይ ከሌለች በመሬት ላይ ምንም ዓይነት ሕይወት አይኖርም:: ለምን?

## የቁልፍ ቃላት ፍቺ

- ☞ **ሁለንታ** - ሁሉንም ቁስ አካላት በጥጥር፣ በፈሳሽና በጋዝ መልክ አካቶ የያዘ ወሰን የለሽ ስፍራ ነው።
- ☞ **ስርዓተ ፀሀይ** (Solar System) - ፀሀይ እና በዙሪያዋ የሚንቀሳቀሱ ፈለኮችን (Planets)፣ ትንንሽ ፈለኮችን (Aesteroids)፣ ተወርዋሪ ኮኮቦችን (Meteors)፣ ጅራታም ኮኮቦችን፣ ኮሜቶችን (Comets)፣ ስብርባሪ ኮኮቦችን (Meteoroids) እና ጨረራን ያካተተ ስብስብ ነው።
- ☞ **ሽክርክሪት** - መሬት በራሷ ዛቢያ ላይ እንደ እንዝርት ስትሾር የምታደርገው እንቅስቃሴ ነው።
- ☞ **ዙሪት** - መሬት በፀሀይ ዙሪያ በምህዋሯላይ የምታደርገው ጉዞ ነው።
- ☞ **ቅርፊተ መሬት** - በዋነኛነት ጠጣር ዓለቶችን፣ አፈር እና የከርሰ ምድር ውሀን የያዘ እና ከሌሎቹ ንብርብሮች ቀዝቃዛ የሆነ የላይኛው የመሬት ንጣፍ ነው።
- ☞ **ማእከለ መሬት** - በቅርፊተ መሬት እና እምብርተ መሬት ንብርብሮች መካከል የሚገኝ በአብዛኛው ቅልጥ ዓለቶችን የያዘ መካከለኛው የመሬት ንጣፍ ነው።
- ☞ **እምብርተ መሬት** - በማእከለ መሬት ተከብቦ ከውስጥ የሚገኝ የእንቁላል አስኳል መሰል ውስጣዊ የመሬት ክፍል ነው።
- ☞ **ሜዳማ ስፍራ** - ዝርግ (flat) ወይም ደልዳላ (ጠፍጣፋ) የሆነ ቅርጽ ያለው ዝቅተኛ ቦታ ነው።
- ☞ **ገበቶ** - ከላይ የዝርግነት ወይም የደልዳላነት ቅርጽ ያለው ከፍተኛ ቦታ ወይም አምባ ምድር ነው።

# ምዕራፍ-2

# የዓለም ሕዝብ፣ መጓጓዣ እና የካርታ ጽንሰ ሐሳብ

## መግቢያ

በዚህ ምእራፍ ስር የዓለም ህዝብ ቁጥር ታሪካዊ እድገትና ጂኦግራፊያዊ ስርጭት፣ የመጓጓዣ ምንነትና ዓይነቶች፣ መጓጓዣ ለማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ያለው አስተዋጽኦ፣ የመንገድ ደህንነት መርሆዎች፣ የትራፊክ አደጋ የሚያስከትለው ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ችግሮች እንዲሁም መሰረታዊ የካርታ ጽንሰ ሐሳቦች ለጥናት ቀርበዋል።

**ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት:**

*ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦*

- ☞ *የዓለም ህዝብ ቁጥር ታሪካዊ እድገትን ሂደትና ስርጭት ሁኔታ ትገመግማላችሁ።*
- ☞ *የመጓጓዣን ምንነት፣ ዓይነቶችና ጠቀሜታዎች ትገልጻላችሁ።*
- ☞ *የመንገድ ደህንነት ጽንሰ ሐሳብንና መርሆዎችን ትተነትናላችሁ።*
- ☞ *የትራፊክ አደጋ የሚያስከትለውን ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ጉዳት ትገመግማላችሁ።*
- ☞ *የካርታን ምንነት፣ ዓይነቶችና አገልግሎቶች ታብራራላችሁ።*
- ☞ *የካርታና ሉልን ተመሳሳይነትና ልዩነት ታነጻጽራላችሁ/ ታወዳድራላችሁ።*
- ☞ *የካርታ ህዳግ መረጃዎችን ምንነትና አገልግሎቶች ትዘረዝራላችሁ።*
- ☞ *የዓለም ዓቀፋዊ መገኛ ስርአትን (Global Positionong System/ GPS) ምንነትና ጠቀሜታዎች ትመረምራላችሁ።*

## ቁልፍ ቃላት:

- ሉል (Globe)
- ቋሚ መስመር (Meridian)
- ኬክሮስ (Latitude)
- ኬንትሮስ (Longitude)
- ዓለም ዓቀፋዊ መገኛ ስርዓት (GPS)
- መስፈርት/ሚዛን (Scale)
- ተጓዳኝ መስመር (Parallel)
- ካርታ (Map)

## 2.1. የዓለም ህዝብ ቁጥር ታሪካዊ እድገትና ስርጭት

### ሀ) የዓለም ሕዝብ ቁጥር እድገት

ውድ ተማሪዎች! የሕዝብ ብዛትንና የህዝብ ቁጥር እድገትን የሚመለከቱ መረጃዎች መሰብሰብና ክስተቱን ማወቅ ለምን ይጠቅማል ትላላችሁ? እስቲ ይህን ሰፋ ያለና ጥልቀት ያለው ጽንሰ ሐሳብ ለመገንዘብ ትችሉ ዘንድ ቀጥሎ የቀረበላችሁን ተግባር ለማከናወን ሞክሩ፡

### ተግባር-1

1. የትምህርት ቤታችሁን ተማሪዎች በየክፍል ደረጃውና በፆታ ስርጭት የሚያሳይ መረጃ መምህራችሁ ከቤተ መዘክር አሰባስበው እንዲያመጡላችሁ አድርጉና በጥንድ በጥንድ በመሆን መረጃውን በባለ መስመር ግራፍና በባር ግራፍ ሰርታችሁ አቅርቡ፡፡
2. ከዛሬ 10 ዓመት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በየዓመቱ ያሉትን ጠቅላላ የተማሪዎች ቁጥር የሚያሳይ መረጃ መምህራችሁ ከቤተ መዘክር አሰባስበው እንዲያመጡላችሁ አድርጉና በቡድን በቡድን በመሆን፡-

   ሀ) የተማሪው ቁጥር በየዓመቱ በምን ያህል መቶኛ (Percent /%/) እንደ ጨመረ አስሉ፡፡ ዓመታዊ ጭማሪው ከፍተኛ ነው ወይስ ዝቅተኛ?


   ለ) የተማሪው ቁጥር በአስር ዓመት ውስጥ በምን ያህል መቶኛ (Percent /%/) እንደ ጨመረ አስሉ፡፡ በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ የታየው ጭማሬ ከፍተኛ ነው ወይስ ዝቅተኛ?

ሐ) የተማሪው ቁጥር እድገት በትምህርት አሰጣጡ፣ በመማሪያ ክፍሎች የማስተናገድ አቅም፣ በመጫወቻ ስፍራዎች፣ በቁሳቁስ አቅርቦትና በመሳሰሉት አገልግሎቶች ላይ ምን ችግር ፈጠረ?

በዓለማችን ፈጣን የህዝብ ቁጥር ጭማሬ የሚታየው በተለይ በታዳጊ አገሮች ነው። በበለፀጉት አገሮች ግን የህዝብ ቁጥር ጭማሬው አነስተኛና አዝጋሚ እንደሆነ በምስል 1 ከቀረበው መረጃ መረዳት ይቻላል። ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት በዓለም ላይ የተመዘገበው በተለይ ከኢንዱስትሪው አብዮት (Industrial Revolution) መከሰት በኂላ ነው። የኢንዱስትሪው አብዮት የተጀመረው በእንግሊዝ አገር እ.አ.አ. በ1750 ዓ.ም ሲሆን የሰው ልጅ ጉልበት በማሽን የተተካበትና የተለያዩ መድሀኒቶች በመሰራታቸው በሰው ልጅ ላይ ሞት ሊያደርሱ የሚችሉ በሽታዎችን መከላከል የተቻለበት እንዲሁም ዘመናዊ የትራንስፖርት አገልግሎት መታየት የተጀመረበት ክስተት ነው።

## ተግባር-2

1. የኢንዱስትሪ አብዮት ለፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት እንዴት መንስኤ ሊሆን እንደቻለ አብራሩ?




ምስል 1- የዓለም ህዝብ ቁጥር እድገት እ.አ.አ. ከ1750 — 2050

## ተግባር-3

1. በምስል 1 ላይ እንደተመለከተው የሕዝብ ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ ጭማሪ የሚያሳየው በታዳጊ አገሮች ነው:: ይህ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ጭማሪ ከምን የመነጨ ነው ትላላችሁ?
2. ቀጥሎ ከቀረቡት ሁለት ተቃራኒ ሀሳቦች ውስጥ የምትስማሙበትን አንዱን በመምረጥ ደግፋችሁ ሌላኛውን በመቃወም የመከራከሪያ ሀሳብ አቅርቡ፦


   ሀ) ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ለልማት (ለእድገት) እንቅፋት ነው::

   ለ) ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ለልማት (ለእድገት) ጠቃሚ ነው::

ተማሪዎች! እስኪ የአገራችንን የሕዝብ ቁጥር ታሪካዊ እድገት ደግሞ በመጠኑ ለመዳሰስ እንሞክር:: በ2013 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት 115,000,000 እንደሆነ ይገመታል:: ዓመታዊ የሕዝብ ቁጥር እድገቱ 2.54% ነው:: ይህም ማለት በ1000 ሰዎች መካከል በዓመት በአማካይ 25 ሰዎች ይጨመሩና 1025 ይሆናሉ ማለት ነው:: በዚህ ሁኔታ ከቀጠለ አሁን ያለው የሕዝብ ቁጥር በ30 ዓመታት ውስጥ በእጥፍ እንደሚጨምር ይገመታል:: ኢትዮጵያ በዓለም ላይ የሕዝብ ቁጥራቸው በከፍተኛ መጠንና ፍጥነት እየጨመረ ከሚሄዱ አገሮች ውስጥ አንዷ ናት::

## ተግባር-4

1. ከታች በምስል 2 ላይ የቀረበውን መረጃ ከመረመራችሁ በኋላ የቀድሞውን፣ የአሁኑንና የወደፊቱን የሕዝብ ጭማሪ ሁኔታ እያነጻጸራችሁ ተንትኑ:: ከዚያም ከተፈጥሮ ሀብትና ከአካባቢ እንዲሁም ከማህበራዊ፣ ከምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ጋር እያዛመዳችሁ አጭር የማጠቃለያ ጽሁፍ አዘጋጅታችሁ በየተራ እየወጣችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ገለጻና ማብራሪያ አቅርቡ::



ምስል 2 - የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ታሪካዊ እድገት

## ለ) የዓለም ሕዝብ ስርጭት

የዓለም ህዝብ ስርጭትና አሰፋፈር በሁሉም ስፍራዎች ላይ ተመሳሳይ አይደለም:: ከጠቅላላው የዓለም ሕዝብ $^2/_3$ የሚሆነው ሰፍሮ የሚገኘው $^1/_7$ በሚሆነው የመሬት ክፍል ላይ ብቻ ነው:: በሌላ በኩል 90% የሚሆነው የዓለም ህዝብ በሰሜናዊ ንፍቀ ክበብ ተሰራጭቶ ሲገኝ 10% ብቻ በደቡባዊ ንፍቀ ክበብ ይገኛል::

### ተግባር-5

1. አብዛኛው የዓለም ህዝብ ተሰራጭቶ የሚገኘው በሰሜናዊ ንፍቀ ክበብ ሊሆን የቻለበት ምክንያት ምንድን ነው? ለዚህ ተግባር ይረዳችሁ ዘንድ በምዕራፍ አንድ ምስል 17 ላይ የሚገኘውን የአህጉራትንና የውቅያኖሶችን ስርጭት መርምሩ::
2. በህዝብ ስርጭት ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ክስተቶችን ከዘረዘራችሁ በኋላ እያንዳንዱ ክስተት እንዴት ተጽእኖ እንደሚፈጥር አብራሩ::
3. በአፍሪካና በዓለም ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ያላቸውን አገሮች ጥቀሱ፣ የህዝብ ብዛታቸውንም ግለጹ::

## 2.2. የመጓጓዣ (Transport) ጽንሰ ሐሳብ፣ ዓይነቶች እና ለማህበረ- ምጣኔ ሀብታዊ እድገት ያለው ጠቀሜታ

ውድ ተማሪዎች! መጓጓዣ ለሚለው ቃል እንግዳ እንዳልሆናችሁ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል:: ምክንያቱም የእርሻ ምርትና ሸቀጣ ሸቀጦች እንዲሁም ሰዎች ከቦታ ወደ ቦታ ሲጓጓዙ የምትመለከቱት የእለት ከእለት ክስተት በመሆኑ ነው:: እስኪ በአካባቢያችሁ ከገጠር ወደ ከተማ፣ ከከተማ ወደ ገጠር እንዲሁም ከከተማ ወደ ከተማ የሚጓጓዙ ሰዎችና ቁሳቁሶች እንዴት እንደሚጓጓዙ ለመምህራችሁ ንገሯቸው::

በአገራችን የተለያዩ የሰውና የእቃዎች መጓጓዣ ዘዴዎች (Modes of Transport) አሉ:: እነርሱም የእንስሳት፣ የመኪና፣ የባቡር፣ የአውሮፕላን ወይም የመርከብ ናቸው:: በብዙ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ሰዎችና እቃዎች በባህላዊ ዘዴ ማለትም በአህያ፣ በበቅሎ፣ በፈረስ ወይም በግመል እንደሚጓጓዙ ይታወቃል:: ዘመናዊ የመጓጓዣ ዘዴዎች በሶስት ምድቦች ይከፈላሉ:: እነርሱም፦

1. የየብስ መጓጓዣ (land transport) - የየብስ መጓጓዣ በመሬት ላይ በተሽከርካሪዎችና በባቡር አማካኝነት የሚከናወን ነው::
2. የውሀ መጓጓዣ (water transport) - የውሀ መጓጓዣ በመርከቦችና በጀልባዎች አማካኝነት ሰዎችና ከባድ እቃዎች (ለምሳሌ፦ የነዳጅ ዘይት ድፍድፍ) በባህር፣ በሐይቅ ወይም በውቅያኖስ ላይ የሚጓጓዙበት በጣም ርካሽ የሆነ የመጓጓዣ ዓይነት ነው:: ተማሪዎች! የውሀ መጓጓዣ ርካሽ

የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው?

3. የአየር መጓጓዣ (Air Transport) - የአየር መጓጓዣ ውድ (ለምሳሌ፦ ወርቅ፣ አልማዝ) እና በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚበላሹ (perishable goods) እንደ አትክልትና ፍራፍሬ የመሳሰሉ ምርቶችን እንዲሁም ሰዎችን በፍጥነት ለመጓጓዝ የሚያስችል የመጓጓዣ ዓይነት ነው።




ምስል 3- የመጓጓዣ ዓይነቶች

### ተግባር-6

1. የሚከተለውን ሠንጠረዥ በየደብተራችሁ ላይ ካሰፈራችሁ በኋላ በተራ ቁጥር 1 ላይ በተቀመጠላችሁ ምሳሌ መሰረት ከፍተኛ፣ መካከለኛ ወይም ዝቅተኛ በማለት ክፍት ሳጥኖቹን አሟሉ::
2. መጓጓዣ በማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች (ግብርና፣ ኢንዱስትሪ፣ ንግድ፣ ወዘተ) የሚጫወተውን ሚና ግለጹ::
3. በምትኖሩበት አካባቢ ሰዎችንና እቃዎችን፣ ሸቀጣ ሸቀጦችን፣ የእርሻ ምርቶችን በማጓጓዝ ከፍተኛውን ሚና የሚጫወቱትን የመጓጓዣ ዓይነቶች ለይታችሁ አመልክቱ::

| ተ.ቁ | የመጓጓዣ ዓይነት | የመጫን አቅም | ፍጥነት | የማጓጓዣ ዋጋ | ለኢትዮጵያ መልክዓ ምድር (የመሬት አቀማመጥ) ያለው ተስማሚነት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አህያ፣ በቅሎ፣ ፈረስ | ዝቅተኛ | ዝቅተኛ | ዝቅተኛ | ከፍተኛ |
| 2 | መኪና | | | | |
| 3 | ባቡር | | | | |
| 4 | መርከብ | | | | |
| 5 | አውሮፕላን | | | | |

## 2.3. የመንገድ ደህንነት፣ የትራፊክ አደጋ እና ማህበረ-ምጣኔ ሀብታዊ ችግሮቹ

ተማሪዎች! የመንገድ ደህንነት ማለት ምን ማለት ነው? እስኪ ለጥቂት ደቂቃዎች አስቡበትና ሀሳባችሁን በአጭሩ በወረቀት ላይ ካሰፈራችሁ በኋላ ቀጥሎ ከተቀመጠው ገለጻ ጋር አነጻጽሩት::

የመንገድ ደህንነት ማለት ሰዎች በመንገድ ላይ ሲንቀሳቀሱ በተሽከርካሪዎች ሊደርስባቸው ከሚችል አደጋ ራሳቸውን የሚጠብቁበት መርህ ማለት ነው:: ምክንያቱም የአንድ ተሽከርካሪ ፍጥነት በሰዓት ከ30 ኪ.ሜ በላይ እየጨመረ በሄደ ቁጥር በመኪናው የሚገጭ ሰው በሕይወት የመትረፍ እድሉ በዚያው መጠን እየቀነሰ የሚሄድ በመሆኑ ነው::




ምስል 4ሀ - የተሽከርካሪዎችና የእግረኞች እንቅስቃሴ

## ተግባር-7

1. በምስል 4ሀ የምታዩትን ፎቶግራፍ ከመንገድ ደህንነት አንጻር በየግላችሁ ገምግሙትና በግምገማችሁ ውጤት ላይ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩበት::



ምስል 4ለ - የመንገድ ደህንነት ምልክቶች ናሙና




ምስል 4ሐ - ለአሽከርካሪዎች የመንገድ ደህንነት ምልክቶች ናሙና

## ተግባር-8

ከላይ በምስል 4ለ እና 4ሐ ላይ የቀረቡትን ፎቶግራፎች መርምራችሁ ተከታዮቹን ጥያቄዎች መልሱ፦

1. የመብራቱ ተግባር ምንድን ነው?
2. በአስፋልት ላይ በነጭ ቀለም የተቀቡ መስመሮች (Zebra Cross) የምን ምልክት ናቸው?
3. እያንዳንዱ ከተራ ቁጥር 1- 4 የሚታየው የተሽከርካሪ መብራት (Traffic Light) ለእናንተ (ለእግረኞች) በሚያስተላልፈው መልእክት ላይ አጭር ጽሁፍ አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ገለጻ አድርጉላቸው፡፡

ተማሪዎች! ከላይኞቹ የመብራት ምልክቶች በተጨማሪ የቆመ የሰው ምስል ያለበት ቀይ መብራት ሲበራ ቁም ማለት ስለሆነ መንገድ ማቋረጥ የለባችሁም፡፡ የሚራመድ የሰው ምስል ያለበት አረንጓዴ መብራት ሲበራ ደግሞ ሂድ ማለት ስለሆነ ፈጠን ብላችሁ መንገዱን ማቋረጥ አለባችሁ፡፡

## ተግባር-9

**ውድ ተማሪዎች!**

ከቦታ ወደ ቦታ ስትንቀሳቀሱ ወይም በተለያዩ የዜና ሽፋኖች በመኪና አደጋ ምክንያት ስለደረሰ ጉዳት ተመልክታችሁ ወይም ሰምታችሁ ይሆናል:: አደጋው ምን ዓይነት እንደሆነ (ለምሳሌ፦ የመኪና መገልበጥ፣ የመኪናዎች ግጭት ወይም በመኪና የተገጨ ሰውና እንስሳ፣ ወዘተ) እና በአደጋው ምክንያት ስለተከሰተው ሁኔታ የተሰማችሁን ስሜትና ስለደረሰው ችግር አጭር የጽሁፍ ዘገባ አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ገለጻ አድርጉ::

በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በመኪና አደጋ ምክንያት በየዓመቱ የ1,300,000 ሰዎች ሕይወት እንደሚያልፍ ይገመታል:: ቁጥራቸው ከ20,000,000 - 50,000,000 የሚደርስ ሰዎች ደግሞ በዚሁ አደጋ ምክንያት ቀላልና ከባድ የአካል ጉዳት ይደርስባቸዋል:: የአገራችንን ሁኔታ ስንፈትሽ ደግሞ በጎንደርና ደብረ ታቦር የኒቨርሲቲዎች የህክምና ትምህርት ቤቶች የተደረገ ጥናት እንደሚያሳየው በመኪና አደጋ በከፍተኛ ደረጃ ተጠቂ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች እድሜያቸው ከ20 -29 (33.01%) የሆኑ ወጣቶችና ከ30 - 39 (26.2%) የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ጎልማሶች ናቸው:: በመኖሪያ አድራሻቸው ሲነጻጸሩ ደግሞ አብዛኞቹ የአደጋው ሰለባዎች የከተማ ነዋሪዎች (54.4%) ናቸው:: የአደጋው ሁኔታ ከስራ ባህሪ አንጻር ሲመረመር ደግሞ ከፍተኛውን ቁጥር (30.1%) የሚይዙት ተማሪዎች ናቸው::

## ተግባር-10

1. ተማሪዎች ከሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች በተለይ ለትራፊክ አደጋ ተጋላጭ የሆኑበት ምክንያት ምንድን ነው ትላላችሁ?
2. የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ ማን ምን ማድረግ እንዳለበት (ለምሳሌ፦ መንግስት፤ ህብረተሰቡ፤ ተማሪዎች፤ አሽከርካሪዎች፣ ወዘተ) ተወያይታችሁ ስምምነት ላይ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ?

የመኪና አደጋ ከፍተኛ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ችግሮችን ያስከትላል:: ለምሳሌ፦ ህልፈተ ሕይወት፣ አካል ጉዳተኛነት፣ የስነ ልቦና ቀውስ፣ የንብረት ውድመት፣ የቤተሰብ መበተንና የገቢ መቋረጥ፣ ለከፍተኛ የህክምና ወጪ መዳረግ፣ ድህነት፣

ወዘተ ናቸው::

## 2.4. የካርታ እና ሉል ጽንሰ ሐሳቦች፣ ጠቀሜታዎችና ዓይነቶች

### 1. የሉል ምንነትና ጠቀሜታዎች

ውድ ተማሪዎች! ሉል ለእናንተ አዲስ ነገር እንዳልሆነ ይታመናል:: በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ እንደሚኖርም ይገመታል:: ሉል በመሬት ላይ የሚገኙ አህጉራዊና ውሀማ አካላትን የሚያሳይ የመሬት ትክክለኛ ቅርጽ ወካይ ሞዴል ነው:: በሉል ላይ ሁሉም የመሬት አካባቢዎች በትክክለኛ ቅርጾቻቸውና መገኛቸው ላይ ይታያሉ:: ሉል የሚከተሉት አገልግሎቶች አሉት፦

- ☞ የቀንና ሌሊት መፈራረቅን በቀላሉ ለመገንዘብ ያስችላል።
- ☞ የወቅቶች መፈራረቅንና የአየር ንብረት ክልሎችን ለመለየት ይጠቅማል።
- ☞ በጉዞ ወቅት የአየርና የባህር ጉዞ መስመሮችን ለመለየት ያገለግላል።
- ☞ ሉልን በማሽከርከር መሬት በራሷ ዛቢያ ላይ ከምእራብ ወደ ምስራቅ የምትሽከረከር መሆኗን ለማየት ይቻላል።



ምስል 5 - ሉል

## 2. የካርታ ምንነትና ጠቀሜታዎች

ካርታ የመሬትን ገጽታ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ከላይ ወደታች በሚታይ መልኩ ከትክክለኛ መጠኑ አሳንሶ በዝርግ (ንጣፍ) ወረቀት ላይ ስርአት ባለው መንገድ አስፍሮ መረጃዎችን የሚያስተላልፍ መሳሪያ ነው:: ካርታ የሚያሳየው ውስን ወይም የተመረጡ መረጃዎችን ብቻ ነው:: ምክንያቱም ሁሉንም መሬት ላይ የሚገኙ አካላት በወረቀት ላይ ማስፈር ስለማይቻል ነው::

### ተግባር-11

1. በትምህርት ቤታችሁ ግድግዳዎች ላይ የተሳሉ ካርታዎችን ወይም በተለያዩ መጽሀፎች ላይ ያያችኋቸውን የኢትዮጵያ፣ የአፍሪካ ወይም የዓለም ካርታዎች በመሬት ላይ ከሚወክሉት የቆዳ ስፋት ጋር ስታነጻጽሯቸው ምን ትገነዘባላችሁ?
2. የክፍላችሁን ወርድና ርዝመት በእርምጃችሁ ለኩት:: ይህን ወርድና ርዝመት ሳትቀንሱ እንዳለ በወረቀት ላይ ማስቀመጥ ይቻላል? ለምን?

ካርታ የሚከተሉት መሰረታዊ አገልግሎቶች (ጥቅሞች) አሉት፦

ካርታ፦

1. አንድን ሰፊ ክልል በአንድ ጊዜ መመልከት እንድንችል የሚረዳ ከመሆኑም በተጨማሪ የቦታዎች እና የሌሎች ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ክስተቶችን አንጻራዊ መገኛና ስርጭት ያመለክታል::
2. በተለያዩ ቦታዎች፣ ክስተቶችና አካላት መካከል ያለን ርቀት በቀላል ስሌት ለማወቅ (ለመረዳት) የሚያስችሉ መረጃዎችን ያሳያል (ያቀርባል)::
3. ቦታዎች በመሬት ላይ ያላቸውን የቆዳ ስፋት ለማወቅ ወይም በስሌት ለማግኘት የሚያስችሉ መረጃዎችን ያቀርባል::
4. ቦታዎችና ሌሎች ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ አካላት የሚገኙበትን አቅጣጫ ያመለክታል::
5. በተለያዩ ክስተቶች መካከል ያለውን መልክዓ ምድራዊ ዝምድና (Spatial relationship) ለማጥናት ያገለግላል:: ለምሳሌ፦ በከፍታና በአየር ንብረት መካከል ያለውን ዝምድና ለማጥናት የካርታ መረጃዎችን መጠቀም ይቻላል::
6. የተለያዩ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ችግሮች ያሉባቸውን ጂኦግራፊያዊ

አካባቢዎች ለመለየትና የልማት እቅድ ለመንደፍ እንዲሁም ለተለያዩ ጥናትና ምርምር ሥራዎች የሚረዱ መረጃዎችን ያስጨብጣል።

7. ለወታደራዊ ስትራተጂዎች (ለምሳሌ፦ የጦርነት እቅድ ለመንደፍ፣ የጠላትን መገኛ ለማሳየት፣ የወታደራዊ ዘመቻዎችን ወይም የእንቅስቃሴ አቅጣጫዎችን ለማመልከት፣ ወዘተ) ያገለግላል።

## ተግባር-12

1. እያንዳንዳችሁ ከቤታችሁ ወደ ትምህርት ቤታችሁ ስትሄዱ ከመንገዳችሁ ግራና ቀኝ ላይ የሚገኙ ዋና ዋና አካላትንና የጉዞ አቅጣጫችሁን የሚያሳይ ንድፈ ካርታ (Sketch Map) አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ገለጻ አድርጉ።
2. ሉልንና ካርታን እያወዳደራችሁ ተመሳሳይነታቸውንና ልዩነታቸውን በጽሁፍ አስፍሩና ያዘጋጃችሁትን ጽሁፍ ከታች ከቀረበው ሀሳብ ጋር አነጻጽሩት።

ሉል ድቡልቡል ወይም ባለ ሶስት ስፍረት (3 dimensional) ነው። ስለዚህ በአንድ ጊዜ ማየት የሚቻለው ግማሽ አካሉን ብቻ ነው። በዚህም ምክንያት በሉል ላይ ከዓለም አህጉራትና ውቅያኖሶች ውስጥ የሚታዩት ገሚሶቹ ብቻ ሲሆኑ በካርታ ላይ ግን ሁሉንም አህጉራትና ውቅያኖሶች በአንድ ጊዜ ማየት ይቻላል። ምክንያቱም ካርታ ባለ ሁለት ስፍረት (2 dimensional) ወይም ዝርግ ወረቀት ስለሆነ ነው። ሉል ድቡልቡል በመሆኑ በሁለት ነጥቦች መካከል ያለን ርቀት ለመለካት ያስቸግራል። በካርታ ላይ ግን ይህን ተግባር ለማከናወን በጣም ቀላል ነው። ከእነዚህ በተጨማሪ የመሬትን የተወሰነ ክፍል ለማሳየት ሉል ሙሉውን መስራት ሲኖርበት በካርታ ላይ ግን የሚፈለገውን የመሬት ክፍል ብቻ ነጥሎ ማሳየት ይቻላል።


ተማሪዎች! እስተውላችሁ ከሆነ በሉልና በካርታ ላይ ከላይ ወደ ታችና ወደ ጎን (አግድም) የተሰመሩ መስመሮች አሉ። ወደ ጎን የተሰመሩት ተጓዳኝ ወይም ትይዩ መስመሮች (Parallels) ሲባሉ ከላይ ወደ ታች የተሰመሩት ደግሞ ቋሚ መስመሮች (Meridians) በመባል ይታወቃሉ። ተጓዳኝና ቋሚ መስመሮች በመሬት ላይ የሚገኝ አንድ ቦታ ከምድር ወገብ (Equator) በስተሰሜንና በስተደቡብ እንዲሁም ከግሪንዊች ሜሪዲያን (Greenwich Meridian) በስተምስራቅና በስተምእራብ በምን ያህል ርቀት ላይ እንደሚገኝ ፍጹማዊ መገኛውን (Abslolute Location) በዲግሪ

ልኬት የሚያመለክቱ ናቸው:: ቋሚ መስመሮች ከዚህ በተጨማሪ ዓለም ዓቀፋዊ ጊዜን ለማስላት ያገለግላሉ::

## ተግባር-13

ምስል 6ን መርምራችሁ ለተከታዮቹ ጥያቄዎች ምላሽ ስጡ፡-

1. መሬትን በምስራቃዊና ምእራባዊ ንፍቀ ክበቦች እኩል የሚከፍላት ቋሚ መስመር ምን ይባላል?
2. መሬትን በሰሜናዊና ደቡባዊ ንፍቀ ክበቦች እኩል የሚከፍለው ተጓዳኝ መስመር ምን ይባላል?
3. የኬክሮስ የመጨረሻ ዲግሪ ልኬት ስንት ነው? የኬንትሮስስ?
4. በሚከተሉት ዲግሪዎች ላይ የሚገኙትን ተጓዳኝ መስመሮችን ስያሜ (ስም) ግለጹ፡-
   - $23\frac{1}{2}^{\circ}$ ሰሜን ኬክሮስ
   - $23\frac{1}{2}^{\circ}$ ደቡብ ኬክሮስ




ምስል 6 - ተጓዳኝና ቋሚ መስመሮች

የተጓዳኝ መስመሮች ርዝመት ከምድር ወገብ ወደ ዋልታዎች እየቀነሰ ይሄድና ዋልታዎች ላይ 0 ኪ.ሜ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ሁሉም ቋሚ መስመሮች በሰሜንና ደቡብ ዋልታዎች ላይ የሚያልፉ በመሆናቸው ርዝመታቸው እኩል ነው፡፡

### ተግባር-14

1. የተጓዳኝ መስመሮች ርዝመት ከምድር ወገብ ወደ ዋልታዎች የሚቀንሰው ለምንድን ነው? ረጅሙ ተጓዳኝ መስመር ማን ነው?
2. ሁሉም ቋሚ መስመሮች ርዝመታቸው እኩል የሚሆነው በምን ምክንያት ነው?

## 3. የካርታ ዓይነቶች

በካርታዎች ላይ የሚሰፍሩ /የሚታዩ/ መረጃዎች እንደ ካርታዎቹ ዓላማና አገልግሎት ስለሚለያዩ ካርታዎች በዓይነታቸው የተለያዩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እንመልከት፡-

ሀ) በያዙት መግለጫ ወይም በሚያስተላልፉት መልእክት ላይ ተመስርተን ካርታዎችን በሚከተሉት ዋና ዋና ምድቦች መፈረጅ ይቻላል፡-

1. ፊዚካል ካርታ - የመሬትን መልክዓ ምድራዊ ገጽታ ያሳያል፡፡
2. ፖለቲካዊ ካርታ - የአገሮችን ክፍፍል ወይም የአገሮችን ድንበሮች ያሳያል፡፡
3. የልዩ ተግባር ካርታ - የአየርና የባህር የጉዞ ካርታዎች፣ የክልላዊ ጊዜ ካርታዎች፣ ስታቲስቲካዊ ካርታዎችና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡

### ተግባር-15

1. ከተራ ቁጥር 1 - 3 በተጠቀሱት የካርታ ምድቦች ውስጥ የሚካተቱ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ነገሮችን የሚገልጹ ምሳሌዎችን ዘርዝሩ፡፡

ለ) ካርታዎች ከተሰሩበት ሚዛን አንጻር በሚከተሉት ምድቦች ይፈረጃሉ፡-

1. ባለ ትልቅ መስፈርት (ሚዛን) ካርታ
2. ባለ መካከለኛ መስፈርት (ሚዛን) ካርታ
3. ባለ ትንሽ መስፈርት (ሚዛን) ካርታ

1:50,000ና ከዚህ በላይ የተሰሩ ካርታዎች (ለምሳሌ 1:30,000) ባለ ትልቅ መስፈርት (ሚዛን) ካርታ ሲባሉ ከ1:50000 እስከ 1:250,000 የተሰሩ ካርታዎች (ለምሳሌ 1:100,000) ደግሞ ባለ መካከለኛ መስፈርት (ሚዛን) ካርታ ይባላሉ:: እነዚህ መካከለኛ የሆነ የቦታ ስፋትን የሚሸፍኑ ስለሆነ ከባለ ትንሽ ሚዛን ካርታ የተሻለ ዝርዝር ጂኦግራፊያዊ መረጃዎችን ይይዛሉ:: 1:250,000 እና ከዚህ በታች (ለምሳሌ፡- ባለ 1:1,000,000 ሚዛን) የተሰሩ ካርታዎች ባለ ትንሽ መስፈርት (ሚዛን) ካርታ ይባላሉ::

### ተግባር-16

1. እያንዳንዱ የካርታ ምድብ ከሚሸፍነው የቆዳ ስፋትና ከሚይዛቸው መረጃዎች ጋር ያለውን ዝምድና አብራሩ::
2. የሚከተሉትን ካርታዎች በየትኛው ምድብ ትፈርጃላችሁ (ባለ ትልቅ መስፈርት፣ ባለ መካከለኛ ወይስ ባለ ትንሽ)?
   - የዓለም ካርታ
   - የቀበሌ ካርታ
   - የአፍሪካ ካርታ
   - የትምህርት ቤታችሁ ካርታ

ከላይ ከተገለጹት የካርታ ዓይነቶች በተጨማሪ ቻርቶች (ሠንጠረዦች) እና ግራፎችም ከካርታ ዓይነቶች ውስጥ የሚመደቡበት ሁኔታ አለ:: ቻርቶችና ግራፎች መረጃን ለማቅረብ፣ መልእክት ለማስተላለፍና ለመቀበል ያገለግላሉ::

### ተግባር-17

1. በቻርቶችና በግራፎች አማካይነት የሚቀርቡ (የሚገለፁ) መረጃዎች ምን አይነት ናቸው? ምሳሌ በመስጠት አብራሩ::

## 2.5. የካርታ ሕዳግ መረጃዎች እና የካርታ ንባብ መርሆዎች

ካርታን ማንበብ የሚቻለው የካርታውን ዝርዝር ባህርያትና አጠቃላይ ሁኔታ በሚገልፁ በካርታው ዙሪያ በሚገኙ መረጃዎች አማካኝነት ነው:: እነዚህ መረጃዎች የካርታ ህዳግ መረጃዎች በመባል ይታወቃሉ::

**የካርታ ህዳግ መረጃዎች የሚከተሉትን ዋና ዋና ክፍሎች ይይዛሉ፦**

1. የካርታው ሚዛን (መስፈርት) - የካርታ ሚዛን (መስፈርት) በካርታው ላይ የሰፈሩ ክስተቶችና ቦታዎች ከወከሉት እውነተኛ አካል በምን ያህል መጠን ተቀንሰው እንደተቀመጡ ያሳያል። ስለዚህ የካርታ ሚዛንን በቀላሉ በሚከተለው ቀመር መግለፅ ይቻላል፦

$$\text{የካርታ ሚዛን} = \frac{\text{በካርታ ላይ ያለ ርቀት}}{\text{በመሬት ላይ ርቀት}}$$

ለምሳሌ፦ በቤታችሁና በትምህርት ቤታችሁ መካከል ያለው ርቀት 5 ኪ.ሜ ነው እንበል። ይህ ርቀት በከተማችሁ ካርታ ላይ በ1 ሳ.ሜ ተወክሎ ቢገኝ ከላይ በቀረበው ቀመር መሰረት የከተማው ካርታ ሚዛን የሚከተለው ይሆናል ማለት ነው፦

$$\frac{1}{500,000}$$

ወይም 1፡500,000 ወይም 1 ሳ.ሜ ለ 5 ኪ.ሜ።

2. የካርታው ርእስ - ይህ ክፍል ካርታው የሚወክለውን አካባቢና ይዘቱን የሚያመለክት ነው።
3. የካርታው ቁልፍ ወይም መፍቻ - በመሬት ላይ የሚገኙ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ክስተቶች በካርታ ላይ የሚወከሉባቸውን ምልክቶችና ቀለማት የሚገልፅ ክፍል ነው።
4. እውን ሰሜን (True North) እና ማግኔታዊ ሰሜን (Mgnetic North)- አብዛኞቹ ካርታዎች የላይኛው ጠርዛቸው ወደ ሰሜን አቅጣጫ እንዲያመለክቱ ሆነው እንዲታተሙ ይደረጋል። ካርታዎች ትክክለኛ አቅጣጫቸውን የሚጠቁም ምንም ዓይነት መረጃ ከሌላቸው የላይኛው ጠርዝ ሰሜን አቅጣጫን አመልካች መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። እውን ሰሜን የሚባለው ትክክለኛው የሰሜን ነጥብ መገኛ ሲሆን ማግኔታዊ ሰሜን ደግሞ የማግኔት መርፌ ከዚህ ነጥብ ጋደል በማለት የሚያመለክተው የሰሜን አቅጣጫ ነው።


5. ካርታው የተዘጋጀበት ጊዜ - ይህ መረጃ የሚያሳየው ካርታው የተዘጋጀበትን ጊዜ ወይም ዓመተ ምህረቱን ነው።
6. የቦታዎች መገኛ አመልካች መስመሮች - የቦታዎች መገኛ አመልካች መስመሮች ዓለም ዓቀፋዊ (Parallels and Meridians) እና ብሔራዊ (Grids) በሚል በሁለት ይከፈላሉ።
7. የካርታው አሳታሚና የቅጅ ባለ መብት - የካርታውን ህጋዊ አሳታሚና ባለቤት ይገልፃል።

**ተግባር-18**

ተማሪዎች! አንድ አካል በካርታ ላይ የሚወከለው መጠኑ ተቀንሶ መሆኑ ከላይ ተቀምጧል። ይህም ሊከናወን የሚችለው በካርታው ሚዛን/መስፈርት አማካኝነት ነው። ይህን ጽንሰ ሐሳብ ለመረዳት ትችሉ ዘንድ የክፍላችሁን ወርድና ርዝመት ከመምህራችሁ ጋር በሜትር ከለካችሁ በኋላ በየግላችሁ ሚዛን/መስፈርት አዘጋጅታችሁ በወረቀት ላይ ካርታውን አስፍሩ።

## 2.6 ዓለም ዓቀፋዊ መገኛ ስርዓት (Global Positioning System/GPS/)


ዓለም ዓቀፋዊ መገኛ ስርዓት አንድ አካል በመሬት ላይ የሚገኝበትን ትክክለኛ ቦታ የሚያሳይ የመረጃ ቅብብሎሽ ስርአት ነው። ይህ ስርአት ሳተላይቶችን (Satel- lites)፣ መረጃ ተቀባዮችን (Receivers) እና የኮምፒውተር ሶፍት ዌሮችን (Soft- ware) በአንድነት አጣምሮ የያዘ ነው።




ምስል 7 - በዓለም ዓቀፋዊ መገኛ ስርዓት (ጂ ፒ ኤስ) የመረጃ ቅብብሎሽ ሂደት

## ተግባር-19

1. ከላይ በምስል 7 ከሚታየው ስእላዊ መግለጫ ምን ትገነዘባላችሁ? እስኪ በቅድሚያ በየግላችሁ አስቡበትና ቀጥሎ በጥንድ በጥንድ በመሆን ከተወያያችሁ በኋላ ለመምህራችሁ ንገሯቸው::
2. ዓለም ዓቀፋዊ መገኛ ስርዓት (GPS) ለአውሮፕላኖች በረራና ለመርከቦች ጉዞ የሚሰጠው አገልግሎት ምን ይመስላችኋል?



ምስል 8 - የዓለም ዓቀፋዊ መገኛ ስርዓት ሳተላይቶች

ዓለም ዓቀፋዊ መገኛ ስርዓት /GPS/ ለአውሮፕላን በረራ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት፦

- በማንኛውም የመሬት አካባቢ የሚበር አውሮፕላን ስለሚገኝበት ቦታና የአየር ሁኔታ ትክክለኛና ተከታታይ መረጃዎችን ያቀብላል::
- የበረራውን ደህንነት በከፍተኛ ሁኔታ ይከታተላል::
- የአየር ጉዞ መዘግየት ችግርንና የነዳጅ ፍጆታን ይቀንሳል (ምክንያቱም አውሮፕላኖች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ቀጥተኛ በረራ እንዲያደርጉ ስለሚያስችላቸው ነው)::
- በጭጋጋማና ለእይታ አስቸጋሪ በሆነ የአየር ሁኔታ ውስጥ አውሮፕላኖች ማረፍ እንዲችሉ ያደርጋል::

## ማጠቃለያ

- በዓለማችን ፈጣን የህዝብ ቁጥር ጭማሬ የሚታየው በተለይ በታዳጊ አገሮች ሲሆን በበለፀጉት አገሮች ግን የህዝብ ቁጥር ጭማሬው አነስተኛና አዝጋሚ ነው:: ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት በዓለም ላይ የተመዘገበው በተለይ ከኢንዱስትሪው አብዮት በኋላ ነው:: የዓለም ህዝብ አሰፋፈር በሁሉም አካባቢዎች ተመሳሳይ አይደለም::

- ሰዎችንና ሸቀጣ ሸቀጦችን ከቦታ ወደ ቦታ የሚያጓጉዙ ዘመናዊ የትራንስፖርት አይነቶች በሶስት ምድቦች ይከፈላሉ:: እነርሱም የየብስ መጓጓዣ፣ የውሃ መጓጓዣና የአየር መጓጓዣ ናቸው::

- የመንገድ ደህንነት ሰዎች በመንገድ ላይ ሲንቀሳቀሱ በተሽከርካሪዎች ሊደርስ የሚችልን አደጋ የሚከላከሉበት ስልት ነው:: የመኪና አደጋ ከፍተኛ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ችግሮች ያስከትላል:: ከእነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹ የሕይወት መጥፋት፣ አካል ጉዳተኝነትና የስነ ልቦና ቀውስ፣ የንብረት ውድመት፣ የቤተሰብ መበተንና ገቢ መቋረጥ፣ ለከፍተኛ የህክምና ወጪ መዳረግና ድህነት ናቸው::

- ሉልና ካርታ ተመሳሳይነት እንዳላቸው ሁሉ ልዩነትም አላቸው:: ሉል እንደ መሬት ክብ ሆኖ በመሬት ላይ የሚገኙ የየብስና የውሀማ አካላትን መገኛ የሚያሳይ የመሬት ቅርጽ ወካይ ሞዴል ነው:: በሉል ላይ ሁሉም የመሬት አካባቢዎች በትክክለኛ ቅርጾቻቸውና መገኛዎቻቸው ላይ ይታያሉ:: ካርታ የመሬትን ገጽታ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ከላይ ቁልቁል ወደታች በሚታይ መልኩ ከትክክለኛ መጠኑ አሳንሶ በዝርግ ወረቀት ላይ መረጃን የሚያቀርብ መሳሪያ ነው::

- ዓለም ዓቀፋዊ መገኛ ስርዓት አንድ አካል በመሬት ላይ የሚገኝበትን ትክክለኛ ቦታ በማንኛውም ጊዜና የአየር ሁኔታ የሚያሳይ ስርአት ነው:: ይህ ስርአት ሳተላይቶችን (Satellites)፣ መረጃ ተቀባዮችን (Receivers) እና የኮምፒውተር ሶፍት ዌሮችን (Software) በአንድነት አካትቶ የያዘ ሲሆን ለአውሮፕላን በረራና ለመርከብ ጉዞ የሚያገለግል የዘመኑ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤት ነው::

## የክለሳ ጥያቄዎች

ሀ) ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ካልሆነ ሐሰት በማለት መልሱ::

1. በዓለም በስፋት ትልቁ አህጉር አፍሪካ ነው::
2. አብዛኛው የዓለም ሕዝብ የሚኖረው በደቡባዊ ንፍቀ ክበብ ነው::
3. የዓለም ህዝብ ቁጥር በፍጥነት መጨመር የጀመረው ከኢንዱስትሪ አብዮት በኋላ ነው::
4. ካርታ የመሬት ቅርጽ ወካይ ሞዴል ነው::
5. ባለ 1፡200,000 መሰፈርት ካርታ ባለ ትንሽ መስፈርት ካርታ ነው::

ለ) በ'ሀ' አምድ ስር የተዘረዘሩትን በ'ለ' ስር ከተቀመጡት ጋር አዛምዱ::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ኬክሮስ | ሀ) ባለ ትንሽ መስፈርት ካርታ |
| 2. ኬንትሮስ | ለ) ባለ ትልቅ መስፈርት ካርታ |
| 3. 1፡25000 | ሐ) ባለ መካከለኛ መስፈርት ካርታ |
| 4. 1፡300000 | መ) የመጨረሻ ዲግሪ ልኬቱ $90^0$ ነው |
| 5. 1፡80000 | ሠ) የመጨረሻ ዲግሪ ልኬቱ $180^0$ ነው |
| | ረ) ቋሚ መስመር |

ሐ) ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ::

1. ከሚከተሉት ውስጥ ባለ ትልቅ መስፈርት ካርታ የቱ ነው?

ሀ) 1፡500,000 ለ) 1፡200,000

ሐ) 1፡100,000 መ) 1፡10,000

2. ከሚከተሉት ውስጥ ባለ መካከለኛ መስፈርት ካርታ የቱ ነው?

ሀ) 1፡500,000 ለ) 1፡200,000

ሐ) 1፡1,000,000 መ) 1፡10,000

3. አብዛኛው የዓለም ሕዝብ የሚገኘው በየትኛው አህጉር ውስጥ ነው?

ሀ) አፍሪካ ለ) ሰሜን አሜሪካ ሐ) እስያ
መ) አውስትራሊያ

4. ሕዝብ የማይኖርበት አህጉር የትኛው ነው?

ሀ) ደቡብ እስያ ለ) አንታርክቲካ ሐ) አውሮፓ መ) አፍሪካ

5. በቆዳ ስፋቱ ትልቁ አህጉር ማነው?

ሀ) ሰሜን አሜሪካ ለ) አፍሪካ ሐ) አውሮፓ መ) እስያ

መ) ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ፡፡

1. በምድር ወገብና በግሪንዊች ሜሪዲያን መካከል ያለውን ልዩነት ግለጹ፡፡
2. በካርታ መስፈርት እና በሚሸፍነው የቦታ መጠን መካከል ያለውን ዝምድና አብራሩ፡፡
3. በቋሚና ተጓዳኝ መስመሮች መካከል ያለውን ልዩነትና አገልግሎታቸውን ግለጹ፡፡

ሠ) ፈታኝ ጥያቄዎች

1. ሉል የመሬት ወካይ ሞዴል ነው የሚባለው ለምንድን ነው?
2. ሉል ባለ 3-ስፍረት አካል (3-dimensional object) ሲሆን ካርታ ደግሞ ባለ 2-ስፍረት (2-dimensional) ነው፡፡ ለምን?
3. በካርታ፣ በቻርትና በግራፍ መካከል ያለውን ተመሳሳይነትና ልዩነት አብራሩ፡፡

# የቁልፍ ቃላት ፍቺ

- **ሉል** - እንደ መሬት ድቡልቡል የሆነ የመሬትን ቅርጽ በትክክል የሚወክል ሞዴል ነው፡፡
- **ካርታ** - በመሬት ላይ የሚገኙ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ክስተቶችን መጠናቸውን ቀንሶ በዝርግ ወረቀት ላይ የሚያሳይ መሳሪያ ነው፡፡
- **መስፈርት** - አንድ በካርታ ላይ የሚገኝ አካል ከእውነተኛ መጠኑ በምን ያህል እንደተቀነሰ የሚያሳይ የካርታ ህዳግ መረጃ ነው፡፡
- **ኬክሮስ** (Latitude)- በሉል ወይም በካርታ ላይ አንድ ቦታ ከምድር ወገብ በስተ ሰሜንና ደቡብ የሚገኝበትን ርቀት የሚያሳይ የዲግሪ ልኬት ነው፡፡
- **ኬንትሮስ** (Longitude) - በሉል ወይም በካርታ ላይ አንድ ቦታ ከግሪንዊች ሜሪዲያን በስተምስራቅና ምእራብ የሚገኝበትን ርቀት የሚያሳይ የዲግሪ ልኬት ነው፡፡
- **ተጓዳኝ (ትይዩ) መስመር** (Parallel) - በተመሳሳይ ዲግሪ ኬክሮስ ላይ የሚገኙ ቦታዎችን የሚያገናኝ መስመር ነው፡፡
- **ቋሚ መስመር** (Meridian) - በተመሳሳይ ዲግሪ ኬንትሮስ ላይ የሚገኙ ቦታዎችን የሚያገኛኝ መስመር ነው፡፡
- **ዓለም አቀፋዊ መገኛ ስርዓት /GPS/** - አንድ ተፈጥሯዊ ወይም ሰው ሰራሽ ክስተት በመሬት ላይ የት ቦታ እንደሚገኝ የሚያመለክት ሳይንሳዊ ዘዴ ነው፡፡

# ምዕራፍ-3

# የሰው እና የተፈጥሮ ሀብቶች መስተጋብር

## መግቢያ

ውድ ተማሪዎች! በዚህ ምዕራፍ ስር በሰው ልጅና በተፈጥሮ ሀብቶች መካከል ያለውን ትስስርና ግንኙነት፣ በሕዝብ ስርጭትና በተፈጥሮ ሀብቶች መካከል ያለውን ዝምድና፣ የሕዝብ ጥግግት መለኪያዎችንና የስሌት ዘዴዎችን እንዲሁም ዋና ዋና የተፈጥሮ ሀብቶች ምድቦችንና በአገራችን ለተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን መንስኤ የሆኑ አብይ ምክንያቶችን ታጠናላችሁ:: በቀረቡት ይዘቶች ላይ በቂ ግንዛቤ ለመጨበጥ ትችሉ ዘንድ በየክፍሉ የቀረቡላችሁን ተግባራት ትኩረት ሰጥታችሁ መመርመርና ማከናወን ይጠበቅባችኋል::

**ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት:**

*ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦*

- ☞ *በሰው ልጅ እና አካባቢ መካከል ያለውን ተፈጥሯዊ መስተጋብር ትገመግማላችሁ::*
- ☞ *የተፈጥሮ ሀብትን ምንነት ትገልጻላችሁ::*
- ☞ *የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶችን ትዘረዝራላችሁ::*
- ☞ *በሕዝብ ስርጭት እና በተፈጥሮ ሀብቶች መካከል ያለውን ግንኙነት ትመረምራላችሁ::*
- ☞ *ከፍተኛና ዝቅተኛ የሕዝብ ጥግግት ያለባቸውን ቦታዎች ታነጻጽራላችሁ::*
- ☞ *የሕዝብ ጥግግትን ትርጉም ትገልጻላችሁ::*
- ☞ *የተለያዩ ቀመሮችን በመጠቀም የሕዝብ ጥግግትን ታሰላላችሁ::*
- ☞ *በኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን ምክንያቶችን ትገመግማላችሁ::*

**ቁልፍ ቃላት:**

- የተፈጥሮ ሀብት(Natural resources)
- አካባቢ (Environment)
- የህዝብ ጥግግት (Population density)
- ታዳሽ የተፈጥሮ ሀብት (Renewable resources)
- ኢ-ታዳሽ የተፈጥሮ ሀብት (Non Renewable resources)

## 3.1. የሰው እና የአካባቢ ግንኙነት

ተማሪዎች! ሰዎች እርሻ ሲያርሱና ሰብል ሲያበቅሉ፣ ቤትና መንገድ ሲሰሩ ወይም ፋብሪካ ሲገነቡ አይታችኋል:: በተለያየ የአየር ንብረት ክልል (ለምሳሌ፦ ውርጭ፣ ደጋ፣ ቆላ) ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ደግሞ የአለባበስና የአመጋገባቸውን ስርአት እንደየሁኔታው እንደሚቀያይሩ አስተውላችሁ ይሆናል:: እነዚህ እውነታዎች የሰው እና የአካባቢን ግንኙነት የሚገልጹ ቀላል ምሳሌዎች ናቸው:: በሰውና በአካባቢ መካከል ያለው ግንኙነት የሁለትዮሽ መስተጋብር (Two - Way Interaction) ነው:: ይህም ማለት አካባቢ (ለምሳሌ፦ የአየር ንብረት) በሰው ልጅና በእንቅስቃሴዎቹ ላይ ተጽእኖ ሲያሳድር በተገላቢጦሽ ሰው ደግሞ በአካባቢው ላይ ተጽእኖ ያደርጋል ማለት ነው:: የሰው ልጅ በመሬት ላይ የተለያዩ ተግባራትን በሚያከናውንበት ጊዜ የተፈጥሮ ሀብቶችን ሁኔታ እንዲሁም የስፍራውን ተፈጥሯዊ ገጽታ ይቀይረዋል::

### ተግባር-1


1. የአካባቢያችሁ ማህበረሰብ በዙሪያው ከሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች (ለምሳሌ፦ ወንዝ፣ ኩሬ፣ ምንጭ፣ አፈር፣ ደን፣ የዱር እንስሳት፣ ወዘተ) ጋር ያለውን ግንኙነትና አንደኛው በሌላኛው ላይ ያሳደረውን አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተጽእኖዎች አስረዱ::



ምስል 1 - የሰውና የአካባቢ መስተጋብር ናሙና

## ተግባር-2

1. ከላይ በምስል 1 የቀረቡት ፎቶግራፎች በሰው ልጅና በአካባቢው መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሳዩ ናሙናዎች ናቸው:: ፎቶግራፎቹን በጥሞና ከፈተሻችሁ በኋላ ምን እንደተገነዘባችሁ አስረዱ::




ምስል 2 - የሰውና የአካባቢ መስተጋብር

## 3.2. የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶች

ተማሪዎች! የተፈጥሮ ሀብት ምንድን ነው? ቀጣዩን ተግባር ካከናወናችሁ በኋላ ለዚህ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ ታገኛላችሁ::

*ተግባር-3*

1. በምትኖሩበት አካባቢ ለሰው ልጅ ጠቀሜታ ወይም አገልግሎት የሚውሉ የተፈጥሮ ሀብቶችን የምትችሉትን ያህል ዘርዝሩ::
2. ተቀራራቢ ባህሪ ያላቸውን በአንድነት በማሰባሰብ በተለያዩ ምድቦች ፈርጇቸው::
3. ለየምድቦቹ ስያሜ ስጧቸውና መገለጫ ባህሪያቸውን ተንትኑ::
4. በመጨረሻ የተፈጥሮ ሀብትን ትርጉም በአጭሩ አስቀምጡና በስንት ምድብ እንደሚፈረጁ ግለጹ::

የተፈጥሮ ሀብቶች በዓይነታቸው፣ በባህሪያቸውና በጥቅማቸው እጅግ በጣም ይለያያሉ:: በመሆኑም በርካታ መስፈርቶችን በመጠቀም በተለያዩ ምድቦች ልንፈርጃቸው እንችላለን:: ለምሳሌ፦ ሕይወት ያላቸው/ biotic/ (ለምሳሌ፦ እጽዋትና እንስሳት) እና ሕይወት የሌላቸው /abiotic/ (ለምሳሌ፦ማእድናት፣ ውሀ፣ አፈር)፣ አላቂ ወይም ኢ-ታዳሽ /Exhaustible or Non-renewable/(ለምሳሌ፦ ማእድናት፣ ነዳጅ፣ የድንጋይ ከሰል፣ የተፈጥሮ ጋዝ) እና ዘላቂ ወይም ታዳሽ /Inexhaustible or Renewable/ (ለምሳሌ፦ አየር፣ ውሀ፣ እጽዋት፣ የፀሀይ ብርሀን) በሚል መመደብ ይቻላል:: ታዳሽ የተፈጥሮ ሀብቶች ዘላቂ ናቸው ቢባልም ራሳቸውን ለመተካት የተወሰነ ጊዜ ስለሚወስድባቸው በፈጣን ሁኔታ በብዛት ጥቅም ላይ ከዋሉ ሊመናመኑ ወይም ሊራቆቱ እንደሚችሉ መገንዘብ ያስፈልጋል:: ዋና ዋናዎቹ የተፈጥሮ ሀብቶች ከዚህ በታች ቀርበዋል፦

*ሀ) ውሀ* - ውሀ ለሰው ልጅ፣ ለእጽዋትና ለእንሰሳት እጅግ በጣም አስፈላጊ የተፈጥሮ ሀብት ነው:: ያለ ውሀ ህይወት ፈጽሞ ሊታሰብ አይችልም:: የውሀ ዋነኛ ችግር ብክለት (Water Pollution) ነው::

### ተግባር-4

1. የውሀን ጥቅሞች ዘርዝሩ፡፡
2. የውሀ ብክለት ምንድን ነው?
3. ዋና ዋናዎቹን የውሀ ብክለት መንስኤዎችና በካዮች ዘርዝሩ፡፡

**ለ) አየር** - አየር ሕይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ አስፈላጊ የሆነ የተፈጥሮ ሀብት ነው፡፡ ልክ እንደ ውሀ የአየር መሰረታዊ ችግር ብክለት /Air Pollution/ ነው፡፡

### ተግባር-5

1. የአየርን ጥቅም ዘርዝሩ፡፡
2. የአየር ብክለት ምንድን ነው?
3. ዋና ዋናዎቹን የአየር ብክለት መንስኤዎችና በካዮች ዘርዝሩ፡፡

**ሐ) እጽዋት** - እጽዋት የምግብ፣ የማገዶና የግንባታ እንጨቶች ምንጮች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በዓለምም ሆነ በአገራችን ደኖች በከፍተኛ ደረጃ በመመናመን ላይ ይገኛሉ፡፡

### ተግባር-6

1. ለደኖች መመናመን አብይ የሆኑ መንስኤዎች ምንድን ናቸው?
2. የደን ውድመትን ለመግታትና ደኖችን ለመንከባከብ ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?

**መ) የዱር እንስሳት** - የዱር እንስሳት ለሳይንሳዊ ምርምሮች ከማገልገላቸውም በተጨማሪ ምጣኔ ሀብታዊና ስነ ውበታዊ ጠቀሜታዎች አሏቸው፡፡ ይሁን እንጂ የዱር እንስሳት በአገራችን ቁጥራቸው በከፍተኛ ሁኔታ ከመቀነሱም በላይ እንደ ዋሊያና የደጋ አጋዘን (ኒያላ) ያሉ ብርቅዬ የዱር እንስሳት ዝርያቸው ለመጥፋት (Endangered Species) ተቃርቧል፡፡

### ተግባር-7

1. በአገራችን ለዱር እንስሳት ቁጥር መቀነስ ዋነኞቹ መንስኤዎች ምንድን ናቸው?
2. የዱር እንስሳትን ከጥፋት ለማዳንና ለመንከባከብ ምን ዓይነት እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው ትላላችሁ?

ሠ) አፈር - አፈር ሕይወት ያላቸውንና ሕይወት የሌላቸውን አካላትና ንጥረ ነገሮች አቀላቀሎ የያዘ የቅርፊተ መሬት የላይኛው ክፍል ነው:: የአፈር ዋነኛ ችግር በተለያዩ ወኪሎች (Agents of Erosion) አማካኝነት የሚከሰትበት ሸርሸራ (Soil Erosion) ነው::

### ተግባር-8

1. በአካባቢያችሁ ለአፈር ሸርሸራ መንስኤ የሆኑ አብይ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
2. የአፈር ሸርሸራ የሚያስከትላቸው ችግሮች ምንድን ናቸው?
3. የአፈር ሸርሸራን ለመከላከል ምን ዓይነት እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው ትላላችሁ?

## 3.3. የሕዝብ አሰፋፈር እና የተፈጥሮ ሀብቶች ግንኙነት

በዓለም ላይም ሆነ በአገራችን የሕዝብ ስርጭት የተመጣጠነ አይደለም:: በአንዳንድ አካባቢዎች ከፍተኛ የሕዝብ ክምችት ወይም ጥግግት ሲታይ በሌሎች ደግሞ ዝቅተኛ የሕዝብ ክምችት ወይም ጥግግት ይታያል::

### ተግባር-9

1. ለሕዝብ ጥግግት መለያየት ወይም ለሕዝብ ስርጭት አለመመጣጠን ምክንያቱ ምንድን ነው?

የህዝብ አሰፋፈር ከተፈጥሮ ሀብቶች ስርጭት ጋር ቀጥተኛ ዝምድና አለው:: እንደ ምግብ፣ ውሀና መጠለያ የመሳሰሉት የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች በመሆናቸው የእነዚህ የተፈጥሮ ሀብቶች መገኛና ስርጭት የህዝብ አሰፋፈር

ሁኔታን ይወስናል። የሕዝብ አሰፋፈርን የሚቆጣጠሩ ዋነኞቹ የተፈጥሮ ሀብቶች ውሀ፣ አፈር፣ እጽዋትና የአየር ንብረት ናቸው።

**ሀ) ውሀ** - የሰው ልጅ አሰፋፈር የውሀ ምንጭ ከሆኑት የተፈጥሮ ሀብቶች ማለትም ከወንዞች፣ ከሐይቆች፣ ከኩሬዎችና የከርሰ ምድር ውሀዎች ጋር የተቆራኘ ነው። ለምሳሌ፡ ጥንታዊ ስልጣኔዎች የነበሯቸው ህዝቦች የሰፈሩት በናይል፣ ኤፍራጠስ፣ ጤግሮስ እና ኤንደስ ወንዞች ዳርቻዎች ነው። ውሀ ለኃይል ማመንጫ፣ ለግብርና ስራ፣ ለመጠጥና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውል የተፈጥሮ ሀብት ነው።

**ለ) አፈር** - አንድን አካባቢ ለሕዝብ ሰፈራነት ተመራጭ ከሚያደርጉት የተፈጥሮ ሀብቶች መካከል አንዱ የአፈሩ ተፈጥሯዊ ይዞታ ነው።

## ተግባር-10

1. በአካባቢያችሁ ከፍተኛ የሕዝብ ክምችት የሚሸከመው ምን ዓይነት አፈር ነው? ምሳሌዎችን በመጥቀስ አብራሩ።

**ሐ) እጽዋት** - እጽዋት ለምግብነት፣ ለግንባታ፣ ለማገዶነትና ለተለያዩ ቁሳቁሶች መስሪያነት የሚያገለግሉ በመሆናቸው የሰው ልጅ አሰፋፈር ሁኔታም የእጽዋት ስርጭት ነጸብራቅ ነው። የእጽዋት ሽፋን መኖር አንድን ስፍራ ለመኖሪያነት ተመራጭ ያደርገዋል።

## ተግባር-11

1. የምድር ወገብ አካባቢ የእጽዋት ሽፋኑ በጣም ጥቅጥቅ ያለ ቢሆንም የሕዝቡ አሰፋፈር ግን የተበታተነ ነው። ይህ ሀሳብ ከላይ ከተቀመጠው እውነታ ጋር ይጋጫል። ለምን እንደሆነ ምክንያቱን አስረዱ።

**መ) የአየር ንብረት** - ለኑሮ አመቺ ያልሆነ የአየር ንብረት ያላቸው አካባቢዎች የሕዝብ ጥግግታቸው ዝቅተኛ ሲሆን በተቃራኒው ተስማሚ የአየር ንብረት ያላቸው ስፍራዎች የሕዝብ ክምችታቸው መካከለኛ ወይም ከፍተኛ ነው።

*ተግባር-12*

1. በአካባቢያችሁ ለኑሮ ምቹ ያልሆነ የአየር ጸባይ (ሁኔታ) ምን ዓይነት ነው? ምቹ የሆነውስ? ለእያንዳንዳቸው ምሳሌዎችን በመጥቀስ አብራሩ::

## 3.4. የሕዝብ ጥግግት መለኪያዎች

የህዝብ አሰፋፈር በአንዳንድ ቦታ ላይ በጣም የተከማቸ፣ በአንዳንድ ቦታዎች ደግሞ መጠነኛ፤ በሌላ ስፍራ ደግሞ በጣም የተበታተነ ሆኖ እናገኘዋለን:: ይህ የህዝብ አሰፋፈር ቅርርቦሽ ወይም መራራቅ ሁኔታ የህዝብ ጥግግት (Population Density) ይባላል:: የህዝብ ጥግግት የሚለው ጽንሰ ሀሳብ የሚያመለክተው በአንድ ካሬ ኪሎ ሜትር ላይ የሰፈረውን የህዝብ ብዛት ነው:: በአንድ ካሬ ኪ.ሜ ቦታ ላይ የሰፈረው ህዝብ ከ100 በላይ ከሆነ ጥግግቱ ከፍተኛ፣ ከ21-100 ከሆነ መካከለኛ፣ ከ5-20 ከሆነ ደግሞ ዝቅተኛ እንደሆነ ይታመናል:: በአንድ ካሬ ኪ.ሜ ላይ የሰፈሩት ሰዎች ቁጥር ከ5 በታች ከሆነ ግን ህዝብ የማይኖርበት ስፍራ ተደርጎ ይወሰዳል::

ተማሪዎች! የህዝብ ጥግግትን ለመለካት የሚያገለግሉ በርካታ ቀመሮች ቢኖሩም ለእናንተ የእድሜ ደረጃ የሚመጥኑት ብቻ ተመርጠው ከዚህ በታች ቀርበውላችኋል::

### ሀ) ግርድፍ የህዝብ ጥግግት (Crude Density)

ግርድፍ የህዝብ ጥግግት በአንድ በተወሰነ ቦታ ላይ በሚኖረው ጠቅላላ ህዝብ ብዛትና ህዝቡ በሰፈረበት የቦታ ስፋት መካከል ያለውን ንፅፅር የሚያሳይ የህዝብ ስርጭት መለኪያ ነው:: ግርድፍ የህዝብ ጥግግት በሚከተለው ሂሳባዊ ቀመር ይገለጻል፦

$$\text{ግርድፍ የሕዝብ ጥግግት} = \frac{\text{ጠቅላላ የሕዝብ ቁጥር}}{\text{ጠቅላላ የቆዳ ስፋት}}$$

*ተግባር-13*

1. የአንድ ወረዳ የህዝብ ብዛት 10,000,000 እንዲሁም የወረዳው የቆዳ ስፋት 2,000 ኪ.ሜ$^2$ ቢሆን ግርድፍ የህዝብ ጥግግቱ ስንት ነው?
2. የህዝቡ ብዛት ከመሬቱ የቆዳ ስፋት ጋር ሲነጻጸር ተመጣጣኝ መሆንና አለመሆኑን ገምግሙ::

ግርድፍ የሕዝብ ጥግግት ስሙ እንደሚያመለክተው የሚለካው በጠቅላላው ሕዝብ እና በጠቅላላው የመሬት ስፋት መካከል ያለውን ዝምድና ስለሆነ ለሰብል ምርት የማይውሉ ቦታዎች ጭምር በውስጡ ተካተዋል፡፡ ስለዚህ የአካባቢውን የምግብ አቅርቦት ሁኔታ በተመለከተ ትክክለኛውን ምስል እንደማያሳይ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

### ለ) ፊዚዮሎጂካል የህዝብ ጥግግት (Physiological Population Density)

ፊዚዮሎጅካል የህዝብ ጥግግት በአንድ አካባቢ በሚኖረው የህዝብ ቁጥርና ለእርሻ ስራ ተስማሚ በሆነው መሬት የቆዳ ስፋት ላይ የተመሰረተ መለኪያ ነው፡፡

$$\text{ፊዚዮሎጂካል የህዝብ ጥግግት} = \frac{\text{የአንድ አካባቢ ጠቅላላ የህዝብ ብዛት}}{\text{ለእርሻ የሚሆን ቦታ ስፋት}}$$

## ተግባር-14

1. በአንድ ዞን የሚኖረው ጠቅላላ ሕዝብ ብዛት 20,000,000፣ የዞኑ ጠቅላላ የቆዳ ስፋት 5,000 ኪ.ሜ$^2$ እንዲሁም ለእርሻ ተግባር ምቹ የሆነው ቦታ የቆዳ ስፋት ከጠቅላላው መሬት 20% ቢሆን ፊዚዮሎጅካል የህዝብ ጥግግቱ ምን ያህል ነው?
2. ያገኛችሁትን ውጤት ከተነተናችሁ በኋላ የዞኑ ፊዚዮሎጅካል ጥግግት ሁኔታ በምግብ አቅርቦት ላይ የሚኖረውን አንድምታ ገምግሙ፡፡

### ሐ) የግብርና ህዝብ ጥግግት (Agricultural Density)

በአንድ በተወሰነ የገጠር አካባቢ በሚኖር ህዝብ ብዛትና ለእርሻ አገልግሎት በዋለው መሬት መካከል ያለውን ዝምድና የሚገልጽ መለኪያ የግብርና ህዝብ ጥግግት ይባላል፡፡

$$\text{የግብርና ህዝብ ጥግግት} = \frac{\text{በገጠር የሚኖረው ጠቅላላ የህዝብ ብዛት}}{\text{የታረሰ መሬት የቆዳ ስፋት}}$$

*ተግባር-15*

1. በአንድ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ የሚኖረው ጠቅላላ ህዝብ ብዛት 200,000 እንዲሁም የቀበሌው ጠቅላላ የቆዳ ስፋት 4,000 ኪ.ሜ$^2$ ነው:: ለእርሻ ስራ የዋለው መሬት የቆዳ ስፋት ከጠቅላላው መሬት 60% ቢሆን የግብርና ህዝብ ጥግግቱ ምን ያህል ነው?
2. የተገኘውን ውጤት ተንትናችሁ የማጠቃለያ ሀሳብ አቅርቡ::

## 3.5. በኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን

**ተማሪዎች!** የተፈጥሮ ሀብቶች መመናመን ማለት ምን ማለት ነው? በምትኖሩበት አካባቢ በመመናመን ላይ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን ልትጠቅሱ ትችላላችሁ? እስኪ ከመምህራችሁ ጋር በዚህ ጉዳይ ላይ ሀሳብ ተለዋወጡበት::

አንድ የተፈጥሮ ሀብት ራሱን ሊተካ በማይችልበት የጊዜ ፍጥነት በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ እየዋለ ከጊዜ ወደ ጊዜ መጠኑና አቅርቦቱ እየቀነሰ ሲሄድ ክስተቱ የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ተብሎ ይገለጻል:: የተፈጥሮ ሀብት መመናመን በተለይ ከእርሻ ስራ፣ ከዓሳ ማስገር፣ ከማእድን ቁፋሮ፣ ከውሀና የነዳጅ ሀብት አጠቃቀም ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው:: በአገራችን የእርሻ መሬቶች ያለማቋርጥ ለብዙ ዓመታት መታረስና ኋላ ቀር የመሬት አያያዝ፣ የግጦሽ መሬቶች የሳር ሽፋን መራቆት፣ የደኖች መጨፍጨፍ፣ የሐይቆች የዓሣ ምርት መቀነስ፣ የአፈር መሸርሸር፣ የውሀ አቅርቦት እጥረት ከመቼውም ጊዜ በላይ አሳሳቢ እየሆኑ የመጡ ችግሮች ናቸው::

እንደ ግብጽና እስራኤል ያሉ አገሮች የአየር ንብረታቸው በረሀማ ሆኖ ሳለ የምግብ አቅርቦት ችግር ግን የለባቸውም:: እንደ ኖርዌይና ፊንላንድ ያሉ አገሮች ደግሞ በአብዛኛው በበረዶ ውስጥ እየኖሩ ነገር ግን ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች አገሮች ምርታቸውን ይሸጣሉ ወይም እርዳታ ይሰጣሉ:: ኢትዮጵያ የተሻለ የተፈጥሮ ሀብቶች ቢኖሯትም በተደጋጋሚ ረሀብ የሚከሰትባት አገር ናት:: ልዩነታችን ከምን የመነጨ ነው ትላላችሁ?

## ተግባር-16

1. በአገራችን በተደጋጋሚ ለሚከሰተው ረሀብ መንስኤው ድርቅ ነው ሲባል ብዙ ጊዜ ትሰማላችሁ:: ድርቅ የረሀብ መንስኤ ነው በሚለው አስተሳሰብ ትስማማላችሁ ወይስ አትስማሙም? ተከራከሩበት::

በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የምግብ አቅርቦት ችግርን ለመፍታት ሲባል በደን የተሸፈኑ ስፍራዎችና የግጦሽ መሬቶች ወደ እርሻ መሬትነት እየተቀየሩ ነው:: ይህ ሁኔታ ከከተሞች መስፋፋት ጋር ተዳምሮ የደኖችን መመናመንና የአፈርን መሸርሸር እያባባሰው ይገኛል::

## ተግባር-17

1. የደኖች መጨፍጨፍና መራቆት እንዲሁም የአፈር መሸርሸር በተለይ በእርሻ ስራ በሚተዳደረው የገጠሩ ማህበረሰብና በአገሪቱ የምግብ ዋስትና ላይ ምን ዓይነት ተጽእኖ ያሳድራሉ? የችግሩስ መፍትሔ ምንድን ነው ትላላችሁ?

የመጠጥ ውሀ አቅርቦት እጥረት በብዙ የኢትዮጵያ ከተሞችና የገጠር አካባቢዎች የሚስተዋል ሌላው ችግር ነው:: በአየር ንብረት ለውጥ፣ በከተሞች መስፋፋት፣ በብክለትና በገደብ የለሽ አጠቃቀም የተነሳ የምንጮችና የወንዞች የውሀ አቅርቦት መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ ነው::

## ተግባር-18

1. በአካባቢያችሁ ለሚታየው የመጠጥ ውሀ አቅርቦት ችግር መንስኤው ምንድን ነው? መፍትሄውስ ምንድን ነው ትላላችሁ?

## ማጠቃለያ

- በሰው ልጅና በአካባቢ መካከል ያለው ግንኙነት የሁለትዮሽ መስተጋብር ነው:: ይህም ማለት አካባቢ (ለምሳሌ፦ የአየር ንብረት) በሰው ልጅና በእንቅስቃሴዎቹ ላይ ተጽእኖ ሲያሳድር በተገላቢጦሽ ሰው ደግሞ በአካባቢ ላይ ተጽእኖ ያደርጋል ማለት ነው:: የተፈጥሮ ሃብቶች በዓይነታቸው፣ በባህሪያቸውና በጥቅማቸው እጅግ በርካታ በመሆናቸው የተለያዩ መስፈርቶችን በመጠቀም በተለያዩ ምድቦች መፈረጅ ይቻላል:: ለምሳሌ፦ ሕይወት ያላቸው/ biotic/ (ለምሳሌ፦ እጽዋትና እንስሳት) እና ሕይወት የሌላቸው /abiotic/ (ለምሳሌ፦ ማእድናት፣ ውሀ፣ አፈር)፣ አላቂ ወይም ኢ-ታዳሽ /Exhaustible or Non-renewable/(ለምሳሌ፦ ማእድናት፣ ነዳጅ፣ የድንጋይ ከሰል፣ የተፈጥሮ ጋዝ) እና ዘላቂ ወይም ታዳሽ /Inexhaustible or Renewable/ (ለምሳሌ፦ አየር፣ ውሀ፣ እጽዋት፣ የፀሀይ ብርሀን) በሚል መመደብ ይቻላል::
- በዓለምም ሆነ በኢትዮጵያ የሕዝብ አሰፋፈር ሁኔታ የተመጣጠነ አይደለም:: በአንዳንድ አካባቢዎች ከፍተኛ የሕዝብ ክምችት ወይም ጥግግት ሲታይ በሌሎች ደግሞ ዝቅተኛ የሕዝብ ጥግግት ይታያል:: የህዝብ አሰፋፈር ከተፈጥሮ ሀብቶች ስርጭት ጋር ቀጥተኛ ዝምድና አለው:: እንደ ምግብ፣ ውሃና መጠለያ የመሳሰሉት የሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች በመሆናቸው የእነዚህ የተፈጥሮ ሀብቶች መገኛና ስርጭት የህዝብ አሰፋፈር ሁኔታውን ይወስነዋል:: የሕዝብ አሰፋፈርን የሚቆጣጠሩ ዋነኞቹ የተፈጥሮ ሀብቶች ውሀ፣ አፈር፣ እጽዋትና የአየር ንብረት ናቸው:: የህዝብ አሰፋፈር ቅርርቦሽ ወይም መራራቅ ሁኔታ የህዝብ ጥግግት ይባላል:: የህዝብ ጥግግት የሚያመለክተው በአንድ በተወሰነ የመሬት የቆዳ ስፋት ላይ ምን ያህል ሰዎች ሰፍረው እንደሚገኙ ነው:: የዚህ መለኪያ ደግሞ በአንድ ካሬ ኪሎ ሜትር ላይ የሰፈረው የህዝብ ብዛት ነው::

➢ አንድ የተፈጥሮ ሀብት ራሱን ሊተካ በማይችልበት ፍጥነት በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ ሲውልና ከጊዜ ወደ ጊዜ መጠኑና አቅርቦቱ እየቀነሰ ሲሄድ ክስተቱ የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ተብሎ ይገለጻል። የተፈጥሮ ሀብት መመናመን በተለይ ከእርሻ ስራ፣ ከዓሳ ማስገር፣ ከማእድን ቁፋሮ፣ ከውሀና የነዳጅ ሀብት አጠቃቀም ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ የምግብ አቅርቦት ችግርን ለመፍታት ሲባል በደን የተሸፈኑ ስፍራዎችና የግጦሽ መሬቶች ወደ እርሻ መሬትነት እየተቀየሩ ይገኛሉ። ለደኖች መመናመንና ለአፈር መራቆት ሌላው ተጨማሪ ምክንያት የከተሞች መስፋፋት ነው። በአየር ንብረት ለውጥ፣ በከተሞች መስፋፋት፣ በብክለትና በገደብ የለሽ አጠቃቀም የተነሳ የከርሰ ምድር ውሀ፣ የወንዞችና ምንጮች የውሀ አቅርቦት መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሽቆለቆለ የሚሄድ የተለመደ ክስተት እየሆነ ነው። የመጠጥ ውሀ አቅርቦት እጥረት በብዙ የኢትዮጵያ ከተሞችና የገጠር አካባቢዎች የሚስተዋል አብይ ችግር ነው።

## የክለሳ ጥያቄዎች

ሀ) ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ካልሆነ ሐሰት በማለት መልሱ።

1. የሰው ልጅ በተፈጥሮ ቁጥጥር ስር ነው።
2. የሕዝብ አሰፋፈር ከተፈጥሮ ሀብቶች ስርጭት ጋር የተያያዘ ነው።
3. ድርቅ የረሀብ መንስኤ ላይሆን ይችላል።
4. ኢ-ታዳሽ የተፈጥሮ ሀብትን ጥቅም ላይ ማዋል ተገቢ አይደለም።
5. የውሀና የአየር ብክለት ዋነኛው መንስኤ የሰው ልጅ ነው።

ለ) በ‘ሀ’ አምድ ስር የተዘረዘሩትን በ‘ለ’ ስር ከተቀመጡት ጋር አዛምዱ::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ማእድን | ሀ) የገጠር ነዋሪዎችን ቁጥር ከእርሻ ስፋት ጋር ያነጻጽራል |
| 2. የሰው ልጅ | ለ) ጠቅላላ የህዝብ ቁጥርን ከጠቅላላ የቦታ ስፋት ጋር ያነጻጽራል |
| 3. የሁለትዮሽ መስተጋብር | ሐ) ሰውና አየር ንብረት |
| 4. የግብርና ህዝብ ጥግግት | መ) ኢ-ታዳሽ የተፈጥሮ ሀብት |
| 5. ግርድፍ የህዝብ ጥግግት | ሠ) ታዳሽ የተፈጥሮ ሀብት |
| | ረ) የተፈጥሮ እጽዋት |

ሐ) ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ::

1. ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ አንደኛውን በመንከባከብ ሌሎቹን የተፈጥሮ ሀብቶች ከውድመት መከላከል ይቻላል:: የትኛው ነው?

   ሀ) ውሀ ለ) አፈር ሐ) ደን መ) የዱር እንስሳት

2. በኢትዮጵያ ውስጥ ዝርያው ሊጠፋ የተቃረበ የዱር እንስሳ የትኛው ነው?

   ሀ) ጅብ ለ) አንበሳ ሐ) ኒያላ መ) ዝንጀሮ

3. ከሚከተሉት ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች መካከል የተፈጥሮ ሀብት መራቆት የማያስከትለው የትኛው ነው?

   ሀ) ኢንዱስትሪ ለ) እርሻ ሐ) ከብት እርባታ መ) ቱሪዝም

4. ከሚከተሉት ውስጥ ታዳሽ የተፈጥሮ ሀብት የሆነው የቱ ነው?

   ሀ) ውሀ ለ) ነዳጅ ሐ) የድንጋይ ከሰል መ) ብረት

5. ከሚከተሉት ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች መካከል የአየር ብክለት አብይ መንስኤ የሚሆነው የትኛው ነው?

   ሀ) ኢንዱስትሪ ለ) እርሻ ሐ) ከብት እርባታ መ) ንግድ

መ) ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ::

1. በሰውና በአካባቢ መካከል ያለውን የእርስ በርስ ትስስር አስረዱ::

2. የአፈርን መራቆት ለመከላከል መወሰድ የሚገባቸውን እርምጃዎች ጥቀሱ፡፡

ሠ) ፈታኝ ጥያቄዎች

የሚከተለውን መረጃ መሰረት አድረጋችሁ ተከታዮቹን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

- ጠቅላላ የህዝብ ብዛት = 600000
- ጠቅላላ የቆዳ ስፋት = 100000 ኪ.ሜ$^2$
- የከተማ ነዋሪዎች ብዛት = 20%
- በሰብል የተሸፈነ መሬት = 40%
- ለእርሻ የሚሆን መሬት = 60%

1. ፊዚዮሎጂካል የህዝብ ጥግግቱን አስሉ፡፡
2. የግብርና ህዝብ ጥግግቱን አስሉ፡፡
3. በተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ ያገኛችሁትን ውጤት ከምግብ አቅርቦት ሁኔታ አንጻር እንዴት ትገመግሙታላችሁ?

## የቁልፍ ቃላት ፍቺ

- የተፈጥሮ ሀብት - ማንኛውም ለሰው ልጅ አገልግሎት ሊውል የሚችል የተፈጥሮ ቁስ ነው፡፡
- አካባቢ - በዙሪያችን የሚገኝ ማንኛውም ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ነገር ነው፡፡
- የሕዝብ ጥግግት - በአንድ በተወሰነ የመሬት ክፍል ላይ ሰፍሮ የሚገኝ ሕዝብ ከቦታ አንጻር ያለው ቅርርቦሽ ወይም መራራቅ ነው፡፡
- ታዳሽ የተፈጥሮ ሀብት - በአጭር ጊዜ ውስጥ ራሱን ሊተካ የሚችል ተፈጥሯዊ ቁስ ነው (ለምሳሌ፦ ውሀ፣ አየር)፡፡
- ኢ-ታዳሽ የተፈጥሮ ሀብት - በአጭር ጊዜ ወይም በሰው ልጅ የእድሜ ክልል ውስጥ ራሱን መተካት የማይችል ተፈጥሯዊ ቁስሰ ነው (ለምሳሌ፦ የተፈጥሮ ጋዝ፣ ማእድናት)፡፡

# ምዕራፍ-4

# ጥንታዊ እና የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ

## መግቢያ

በሀገራችን ታሪክ አፃፃፍ የጊዜ ቅደም ተከተል መሰረት ከጥንት እስከ 1270 ዓ.ም ያለው ዘመን ጥንታዊ የኢትዮጵያ ታሪክ በመባል ይታወቃል:: ጥንታዊ የኢትዮጵያ ታሪክ በውስጡ የቅድመ አክሱም መንግስታትን፣ የአክሱም ስልጣኔን እና የዛግዌ ስርወ መንግስት ዘመንን የያዘ ነው:: የመካከለኛው ዘመን ታሪክ ደግሞ ከ1270- 1855 ዓ.ም ያለውን ጊዜ ይሸፍናል:: በመካከለኛው ዘመን ታሪክ ውስጥ ያሉ ይዘቶች ደግሞ የሰለሞናዊ ስርወ መንግስት ዳግም መመለስ፣ የደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት የመስፋፋት ዘመቻ፣ የሙስሊም ሱልጣኔቶች መመስረት፣ የደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት እና የሙስሊም ሱልጣኔቶች ግንኙነት፣ የኦሮሞ ህዝብ መስፋፋት፣ የጎንደር ዘመን እና ዘመነ መሳፍንት የሚሉ ይዘቶችን አካትቷል:: የደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት የሚለው ሀረግ ለእንግሊዝኛው (Christian Highland Kingdom) አቻ ፍች ተደርጎ ተወስዷል::

**ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት:**

*ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-*

- *የአክሱም ስልጣኔን ዋና ዋና አበርክቶዎችን ትዘረዝራላችሁ::*
- *በዛጉዌ ዘመን የነበሩ ዋና ዋና ታሪካዊ ሁነቶችን ትተነትናላችሁ::*
- *ዋና ዋና የሙስሊም ሱልጣኔቶች መገለጫዎችን ትዘረዝራላችሁ::*
- *የኦሮሞ ህዝብ መስፋፋት ምክንያቶችን ትዘረዝራላችሁ::*
- *በጥንት እና በመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ ስለነበረው የግብርና፣ ንግድ እና የግብር ስርዓት ልዩነቶችን ትተነትናላችሁ::*

- ☞ በሀገራችን በጥንትታዊው እና በመካከለኛው ዘመን የነበሩ ስልጣኔዎችን ታደንቃላችሁ::
- ☞ የጎንደር ዘመን ዋና ዋና መገለጫዎች ምን ምን እንደነበሩ ታብራራላችሁ::
- ☞ ለዘመነ መሳፍንት መጀመር ምክንያቶችን ትለያላችሁ::

## 4.1 የጥንታዊ ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ

### 4.1.1.ቅድመ አክሱም መንግስታት

**ፑንት**

**ቁልፍ ቃል:**

☞ አርኪኦሎጂ

**ተግባር-1**

1. በሰዎች መቃብር ላይ ፅሁፍ ወይም ሀውልት የሚያስቀምጡ ሰዎች አሉ:: ይህንን ተግባር የማይደግፉ ሰዎችም አሉ:: የሚፅፉት ወይም ሀውልት የሚያስቀምጡት ለምን ይመስላችኋል?
2. ሙጫ ምንድን ነው? በአካባቢችሁ ማግኘት ትችላላችሁ? ለምን ጥቅም ይውላል?

በሀውልቶች፣ በመካነ መቃብሮች ላይ የተቀረፁ የሂሮግሊፊክስ ፅሁፎች እና የአርኪኦሎጂ መረጃዎች መሰረት ከግብፅ በስተደቡብ ተመስርተው ከነበሩ መንግስታት በጣም ጥንታዊው እና በተደጋጋሚ የሚጠቀሰው የፑንት መንግስት ነበር:: ግብፃውያን በዝነኛዋ የግብፅ ንግስት ሀሻፕሱት (1490-1468) ተከታታይ የባህር ላይ የንግድ ጉዞዎችን ወደ ፑንት መንግስት አድርገዋል:: ከዚህ የንግድ ጉዞ ግብፃዊያን እጣን፣ ከርቤ፣ ቀረፋ፣ የዝሆን ጥርስ፣ የአውራሪስ ቀንድ፣ የነብር ቆዳ፣ ቀበሮ፣ ድብ፣ ቀጭኔ፣ ወርቅ፣ ብር፣ ነሀስ፣ ጥቁር እንጨት ከፑንት ይዘው ተመልሰዋል::

የፑንት መንግስት ተመስርቶበት የነበረው ቦታ እና የግዛት ወሰን በትክክል አይታወቅም:: የተወሰኑ ምሁራን ግዛቱን ሰሜን ወይም ሰሜን ምስራቅ ሶማሊያ

ነው ብለው እጣን እና ለሽቶ መቀመምያ የሚያገለግል ሙጫ በግብፃዊያን ፅሁፎች መጠቀሱን እንደማሳመኛ ያቀርባሉ:: ሌሎች ምሁራን ደግሞ የፑንትን መንግስት ግዛት ሰሜን ኢትዮጵያ ነው ይላሉ:: ለዚህ ማስረጃቸው በሄሮግሊፊክስ ፅሁፎች ወርቅ እና ጥቁር እንጨት በሰሜን ኢትዮጵያ እንደሚገኙ ተፅፎ መገኘቱን ነው:: አብዛኛው ምሁራን ግን የዛሬዎቹን ኤርትራ፣ ጂቡቲ፣ ኢትዮጵያ፣ ሶማሊያ እና የመንን እንደሚያካልል ይገልጻሉ:: የእነዚህ ምሁራን ማስረጃቸው በፑንት እና በግብፅ መንግስታት መካከል በነበረው የንግድ ልውውጥ ይጠቀሙባቸው የነበሩት ሸቀጦች በአካባቢው በመገኘታቸው ነው::

## ተግባር-2

1. ስለ ፑንት መንግስት መማራችሁ ምን የሚያስደስት ነገር አገኛችሁ? የተሰማችሁን ነገር ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁላቸው::

### ዳዓማት

**ቁልፍ ቃላት፦**

- ☞ ሙካሪብ
- ☞ ወደብ

## ተግባር-3

1. ከፑንት ቀጥሎ የተመሰረተው ጥንታዊ መንግስት ማን ነው? መልሱን ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ::

የዳዓማት መንግስት በሰሜናዊ ኢትዮጵያ ተመስርተው ከነበሩት ጥንታዊ መንግስታት አንዱ ነበር:: የዳዓማት መንግስት የተመሰረተባቸው ቦታዎች ከዛሬዋ አክሱም በስተደቡብ አካበቢ ነበር:: የዳዓማት መንግስት ማዕከል የሃ ነበረች:: የዳዓማት ነገስታት ሙካሪብ የሚባል የደቡብ አረቢያዎችን የፖለቲካ እና የሃይማኖት ማዕረግ ይጠቀሙ ነበር:: ሙካሪብ ለደቡብ አረቢያ ነገስታት የሃይማኖት የበላይ ጠባቂ፣ የፍትህ አካላት የበላይ ዳኛ እና የጦር አዛዥ እንዲሆኑ አስችሏቸው ነበር:: ይህ የሚያመለክተው በኢትዮጵያ እና በደቡብ አረቢያ መካከል የጠበቀ ፖለቲካዊ ግንኙነት መኖሩን ነው:: የዳዓማት ነገስታትም የሚያመልኳቸው አማልክት ነበሯቸው::



ምስል 4.1. የሃ ውስጥ የተገኘ ዙፋን እና ጣኦት

### ተግባር-4

1. ስለ ዳዓማት መንግስት ከተማራችሁ በኋላ ያገኛችሁት ጥቅም ምንድን ነው? ለጓደኞቻችሁ ግለፁላቸው::
2. ዳዓማት መንግስት ሙካሪብ የሚባለውን የደቡብ አረቢያ የንግስና ማዕረግ መጠቀማቸው ምንን ያሳያል? በጥንድ በጥንድ ስሩ::

## 4.1.2. የአክሱም ስልጣኔ

**ቁልፍ ቃላት፦**


- ☞ ርስት
- ☞ ጠረፍ
- ☞ ሽኩቻ
- ☞ ሂጅራ

### ተግባር-5

1. የአሁኗ አክሱም ከተማ የት እንደምትገኝ በካርታ ላይ አሳዩ::

የአክሱም ስልጣኔ የተመሰረተው በአንደኛው መቶ ክፍል ዘመን አካባቢ ነበር:: ከ4ኛው - 7ኛው ክፍለ ዘመን አክሱም የአካባቢው ጠንካራ መንግስት ሆኖ ነበር:: እርሻ የአክሱማዊያን ኢኮኖሚ መሰረት ነበር:: የመስኖ ስራ በመጠቀም የእርሻ


ምርታማነትን አሳድገው ነበር:: ገበሬዎች የርስት ባለቤት ሲሆኑ ለአክሱም መንግስት ግብር ይከፍሉ ነበር:: ሌላው ለአክሱም መንግስት ገቢ ያስገኝ የነበረው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የውስጥ እና የውጭ ንግድ ነበር:: የውስጥ ንግድ ከቀይ ባህር እና አዶሊስ የንግድ መነሻዎች ወደ መሀል ሀገር ነበር::




ምስል 4.2. የአክሱም የውስጥ እና የውጭ ንግድ

አክሱም ወደ ውጭ ትልካቸው ከነበሩ ሸቀጦች መካከል የዝሆን ጥርስ፣ ሙጫ፣ የከበሩ ድንጋዮች፣ እጣን፣ ቅመማ ቅመም፣ ወርቅ፣ የአውራሪስ ቀንድ፣ የጉማሬ ቆዳ እና የኤሊ ቅርፊት ይጠቀሳሉ:: በምትኩ አልባሳት፣ የቤት ውስጥ ዕቃዎች፣ መስታወት፣ የወይራ ዘይት እና የወይን ጠጅ ወደ አክሱም ይገቡ ነበር::

ለአክሱም ታሪክ መረጃ የሚሆኑ ቀደምትነት ካላቸው ፅሁፎች መካከል የኤርትራ የባህር ጉዞ (periplus of the Eritrean Sea) ይጠቀሳል:: ይህ መፅሀፍ የተፃፈው በ50 ዓ.ም ሲሆን ፀሀፊው እንደገለፀው የአዶሊስ ወደብን ጎብኝቷል:: የዘመኑ የአክሱም ንጉስ ዞስካለስ እንደሚባልና የግሪክን ቋንቋ አጣርቶ የሚናገር እንደነበረ ዘግቧል:: በወቅቱ የአክሱም መንግስት የተደራጀ እና ጠንካራ እንደነበርም ጠቅሷል::




ምስል 4.3. በየሃ የተገኘ የድንጋይ ላይ ፅሁፍ

ሌላው የአክሱም ታሪክ ምንጭ በግሪክ ቋንቋ የተፃፈ የአዶሊስ የድንጋይ ላይ ፅሁፍ ነው:: ይህ ፅሁፍ በኮስማስ ኢንዲኮፕሊስተስ ክርስቲያን ቶፖግራፊ በሚለው መፅሀፍ የተጠቀሰ ነበር:: በመፅሀፉ ንጉሱ ስለ አደረጓቸው የግዛት ማስፋፋት ዘመቻዎች ገልጿል:: በተለይም በሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ቀይ ባሕርን ተሻግሮ እስከ ደቡብ ዓረቢያ በአክሱማዊያን ስር ስለማድረጉ ያስረዳል::



ምሥል 4.4. በነህስ ላይ በሳባኛ ቋንቋ የተጻፈ ፅሁፍ

አክሱም ከምትታወቅበት ነገር አንዱ ኪነ ሕንፃ ሲሆን ከድንጋይ የተፈለፈሉ ሐውልቶችን ሰርታ ነበር:: አሁን ወድቆ እና ተሰባብሮ የሚገኘው ትልቁ ሀውልት 33 ሜትር ርዝማኔ አለው:: ሁለተኛው ትልቁ ሀውልት 24 ሜትር ርዝመት ያለው ከስር የምትመለከቱት አሁን አክሱም ቆሞ ያለው ሲሆን ሶስተኛው 22 ሜትር ርዝማኔ ያለው በጣሊያን ተወስዶ በ2005 ዓ.ም የተመለሰው ነው::




ምስል 4.5. የአክሱም ሀውልት

በአፄ ኢዛና ዘመነ መንግስት (325-360) የክርስትና ሃይማኖት በሶሪያዊው ፍሬምናጦስ (በኋላ አቡነ ሰላማ) በ330 ዓ.ም አካባቢ ወደ አክሱም ገባ:: አፄ ኢዛና ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስትናን ተቀብለው በግልጽ የመንግስት ሃይማኖት እንዲሆን አወጁ:: በ5ኛው ክፍለ ዘመን ከሶሪያ፣ ሊባኖስ እና ቆጵሮስ በመጡ ዘጠኙ ቅዱሳን ማለትም አባ አፍጼ፣ አባ አሌፍ፣ አባ አረጋዊ፣ አባ ገሪማ፣ አባ ጉባ፣ አባ ሊቃኖስ፣ አባ ጴንጠሊዮን፣ አባ ጽሕማ እና አባ ይምዓታ አማካኝነት ክርስትና ወደ ታችኛው የህብረተሰብ ክፍል መድረስ ቻለ:: የክርስትና ሃይማኖት ወደ አክሱም መግባት ካስገኛቸው ለውጦች መካከል የመፅሐፍ ቅዱስ ከግሪክ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ቋንቋ መተርጎም እና የአክሱም የውጭ ግንኙነት እንዲጠናከር ማድረጉ ይጠቀሳሉ::

የኢትዮጵያን የውጭ ግንኙነት ያጠናከረው ሌላው ታሪካዊ ሁነት ደግሞ ነጃሽ አል አስሐማ /አርማህ (615-631) የነብዩ ሙሐመድን ተከታዮች በግዛታቸው መቀበላቸው ነበር:: የመጡበት ምክንያት በመካ ይኖሩ የነበሩት የቁረይሽ ጎሳዎች ባደረሱባቸው ችግር ነበር:: በመጀመሪያው ሂጅራ 615 ዓ.ም ከ15-18 የሚደርሱ ሰዎች የነብዩ መሐመድ ልጅ ሩቅያን ጨምሮ ዑስማን ኢብን መዝዑን (የቡድኑ መሪ)፣ ሙሳ ዓብ ኢብኑ ዑመይር፣ ዑስማን ኢብኑ አፋን፣ አቡ ሁዘይፋ እና ኡሙ አይመን ጥቂቶቹ ነበሩ:: በሁለተኛው ሂጅራ በ616 ዓ.ም 119 አካባቢ ተከታዮችን ይዞ የመጣው ጃዕፈር ኢብኑ አቡ ጧሊብ ነበር::

በሁለቱም ሂጅራ ከ126-129 የሚገመቱ ሙስሊሞችን ንጉስ አል አስሐማ ተቀብለው በሰላም እንዲኖሩ ፈቅደዋል:: የመጡት የነብዩ ሙሐመድ ተከታይ ሙስሊሞች ወደ አረቢያ (መካ) በ629 አብዛኞቹ ተመልሰው ሄደዋል:: ከፊሎቹ

ኑሯቸውን በአክሱም የመሰረቱም እንደነበሩም ይነገራል፡፡ በዚያን ጊዜ ወደ አክሱም ከመጡት ከ15-20 ያህሉ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ህይወታቸው አልፎ አፅማቸው ነጋሽ በተባለው ቦታ በክብር አርፏል፡፡ ይህ ታሪካዊ ክስተት የሚያሳየው በሀገራቸው ያጡትን ነፃነት በኢትዮጵያ ማግኘታቸውን ነው፡፡ ሙስሊሞቹ በንጉስ አል አስሐማ ግዛት በነፃነት መኖር ከመጀመራቸውም በተጨማሪ ሀገራችን ሰላም የሰፈነባት፣ ፍትሀዊ ንጉስ የነበራት፣ የራሷ ስርዓተ መንግስት ያላት፣ እንግዳ ተቀባይ መሆኗን ያስመሰከረችበት ወቅት ነበር፡፡



ምስል 4.6. ንጉስ አል አስሐማ የነብዩን ተከታዮች እና የቁረይሽ ተወካዮችን ሲያወያዩ

በተጨማሪም የአክሱም ስልጣኔ ሀገራችን ኢትዮጵያ የራሷ የሆነ የስነ-ፅሁፍ ቋንቋ እንዲኖራት፣ ስነ ፅሁፍ፣ እደጥበብ፣ በግሪክ እና በግዕዝ የተፃፈባቸው ከወርቅ፣ ከብር እና ከነሀስ የተሰሩ ሳንቲሞች ዋና ዋና አበርክቶዎች ናቸው፡፡



ምስል 4.7. የንጉስ ኢዛና የወርቅ ሳንቲም

ለአክሱም ስልጣኔ መውደቅ ውጫዊ እና ውስጣዊ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ:: ውጫዊ ምክንያት የነበረው ከ7ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ አረቦች የቀይ ባህርን ንግድ ለመቆጣጠር መፈለጋቸው ነበር:: በ702 ዓ.ም የአዶሊስ ወደብን በመቆጣጠራቸው የአክሱምን ኢኮኖሚያዊ አቅም አዳከመው:: ውስጣዊ ምክንያቶችን በተመለከተ ደግሞ የቤጃ አርብቶ አደር ህዝብን አመፅ እና ወረራ መቋቋም አለመቻል፣ የስልጣን ሽኩቻ እና የኢኮኖሚ መዳከም ነበሩ:: በመጨረሻም የአክሱም መንግስት ማዕከል ወደ ላስታ ከተዛወረ በኋላ በ1150 ዓ.ም የመንግስቱ ፍፃሜ ሆነ::

**ተግባር-6**

1. ንጉስ አስሐማ በሰባተኛው ክፍለ ዘመን የነብዩ ሙሐመድን ተከታዮች ተቀብለው ማስተናገዳቸው ለአሁኑ ሀገራዊ አንድነት ግንባታ ያለውን ጥቅም ገምግሙ::
2. ለአክሱም ስልጣኔ መውደቅ ምክንያቶችን ዘርዝሩ::

### 4.1.3. የዛግዌ ስርወ መንግስት አነሳስና መጠናከር

**ቁልፍ ቃላት:**

- ቤተ ክህነት
- ባህረ ሰላጤ
- ቋጥኝ


**ተግባር-7**

1. ሰላም ለሀገር ግንባታ ያለውን ጥቅም ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁላቸው::
2. በምትኖሩበት አካባቢ የተሰራ ህንፃ አይታችኋል? ስለ ተሰራበት ቁሳቁስ እና ስለ አሰራሩ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁላቸው::

የዛግዌ ስርወ መንግስት መስራቹ መራ ተክለ ሃይማኖት ይባል ነበር:: የግዛቱን ከተማ ላስታ ግዛት አዳፋ ላይ መሰረተ:: ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን ወደ ሮሃ ከተማ ተዛወረ:: በመጨረሻ በንጉስ ላሊበላ ዘመነ ንግስና ንጉስ ላሊበላ በስሙ ላሊበላ ከተማን የግዛቱ ማዕከል አደረገ:: የዛግዌ ነገስታት እንደ አክሱማዊያን ከግብፅ እና ከፍልስጤም ጋር የነበራቸው ግንኙነት ጠንካራ ነበር:: የዛግዌዎች የአገዛዝ ዘመን በአውሮፓዊያን እና በሰልጆክ ቱርኮች መካከል የተካሄደ ጦርነት (የመስቀል ጦርነቶች) ወቅት ጋር የተገጣጠመ ነበር:: የዛግዌ ነገስታት በመስቀል ጦርነት

አልተሳተፉም፡፡ ዛግዌዎች ከሙስሊም እና ክርስቲያን መንግስታት ጋር በወዳጅነት ላይ የተመሠረተ ግንኙነትም ነበራቸው፡፡ በዚህ ሰላማዊ ግንኙነታቸው በእየሩሳሌም የነበራቸውን የመሬት ይዞታ አፀኑላቸው፡፡

በተጨማሪም ዛግዌዎች በዳህላክ ደሴቶች፣ በዘይላ ወደብ እና በኤደን ባህረ ሰላጤ የንግድ ግንኙነቶች እንዲጠናከሩ አድርገዋል፡፡ ነገስታቱ ያላቸውን እምቅ ሀይል እና ሐብት ያዋሉት አብያተ ክርስቲያናት ግንባታ ላይ ነበር፡፡ የዛግዌ የአገዛዝ ዘመን ልዩ ስኬት ከአንድ ወጥ ቋጥኝ የተፈለፈሉ አስደናቂ የሆኑ ስነ-ህንፃዊ ጥበብ የሚታይባቸው አብያተ ክርስቲያናትን መገንባታቸው ነበር፡፡ ይህ ተግባራቸው ከአክሱማዊያን ጋር ያመሳስላቸዋል፡፡ አክሱማዊያን ቤተ ክርስቲያናትን ከቋጥኝ ፈልፍሎ የመስራት ልምድ ነበራቸው፡፡ ዛግዌዎች ቤተ ክርስቲያናትን በማነፅ እና ገዳማትን በመመስረት ክርስትናን አስፋፍተዋል፡፡ የንግድ እና የእርሻ ስራም የገቢ ምንጫቸው ነበር፡፡ ለዛግዌ መንግስት ውድቀት ምክንያት ከሆኑት ውስጥ ሠላማዊ የሥልጣን ሽግግር ህግ አለመኖሩ እና የስልጣን ሽኩቻ ይጠቀሳሉ፡፡



ምስል 4.8 የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያን(ቤተ-ጊዮርጊስ)

### *ተግባር-8*

1. ጥንድ ጥንድ በመሆን ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ማለት ምን ማለት እንደሆነ እና ያለውን ጥቅም ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩላቸው፡፡
2. የዛግዌ ነገስታት የሰሯቸውን አበርክቶዎች ከለያችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁላቸው፡፡
3. በዛግዌ እና በአክሱም መንግስታት መካከል ያለውን አንድነት እና ልዩነት ከለያችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ሪፖርት አቅርቡ፡፡

# 4.2 የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ

## 4.2.1. የሰለሞናዊ ስርወ መንግስት ዳግም መመስረት

**ቁልፍ ቃል፦**

☞ ሰለሞናዊ

### ተግባር-9

1. የሰለሞናዊ ስርወ መንግስት ሲባል ከአዕምሯችሁ የሚመጣው ሀሳብ ምንድን ነው? አጠር አድርጋችሁ ከጎናችሁ ካለው/ችው ጓደኛችሁ ጋር ተነጋገሩ እና መልሱን ለመምህራችሁ ግለፁ::
2. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ሰዎችን በመጠየቅ ስለ ንጉስ ሰለሞን እና ስለ ንግስት ሳባ ታሪክ ሁለት አንቀፅ ፃፉ:: የፃፋችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው::

አፄ ይኩኖ አምላክ በ1270 ዓ.ም አፄ ይትባረክን (የመጨረሻው የዛግዌ ንጉሰ ነገስት) ድል በማድረግ የኢትዮጵያ ንጉስና ሰለሞናዊ ስርወ መንግስት ዳግም መስራች መሆናቸውን አወጁ:: አፄ ይኩኖ አምላክ እና ተከታዮቻቸው የሰለሞናዊ ስርወ መንግስት የሚለውን ሥያሜ የመረጡበት ምክንያት ለመንገስ ህጋዊነታቸውን ለማስመስከር እና የዛግዌ ገዥዎች ስልጣን የማይገባቸው ናቸው የሚባለውን አስተሳሰብ ለማሳየት ነበር:: አፄ ይኩኖ አምላክ (ከ1270-1285) በሰላም ሲገዙ ከቆዩ በኋላ አፄ ያግባ ፅዮን ለሚባለው ልጃቸው (1285- 1294) ስልጣናቸውን አስረከቡ:: ከ1294 -1299 ዓ.ም ባሉት አምስት አመታት ውስጥ አምስቱ የአፄ ይኩኖ አምላክ ልጆች ነግሰው ነበር::

የአፄ ይኩኖ አምላክ የልጅ ልጆች በመካከላቸው ባካሄዱት የስልጣን ሽኩቻ ምክንያት ውስጣዊ የፖለቲካ አለመረጋጋት ተፈጥሮ ነበር:: ይህን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት ሁሉም የአፄ ይኩኖ አምላክ የልጅ ልጆች (ከነገሰው በስተቀር) አምባ ግሸን በማሰር በታማኝ ሰራዊት እንዲጠበቁ አድርገዋል:: አፄ አምደ ፅዮን (1314-1344 ) ስልጣን ከያዙ በኋላ የግዛት ማስፋፋት ዘመቻዎችን አካሂደዋል:: በዘመቻውም ዳሞትን፣ ጎጃምን፣ የጣና ሀይቅ ዙሪያን፣ በምስራቅ እና በደቡብ ምስራቅ የነበሩ የሙስሊም ሱልጣኔቶችን በጦርነት በማሸነፍ ሁሉንም ገባር ግዛቶች አድርገዋቸዋል:: የእነዚህ

ግዛቶች በቁጥጥር ስር መዋል አፄ አምደ ፅዮን ተጨማሪ የሰው ሀይል እና ሀብት እንዲያገኙ አስችሏቸዋል።

*ተግባር-10*

1. የመካከለኛው ዘመን ነገስታት ከዛግዌ ነገስታት በተሻለ የስልጣን ሽኩቻን ለማስቆም የወሰዱትን እርምጃዎች በመለየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ።

### 4.2.2. የሙስሊም ሱልጣኔቶች

*ተግባር-11*

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙ የሃይማኖት አባቶችን /የሚያውቁ ሰዎችን በመጠየቅ እስላም፣ ሙስሊም፣ ሱልጣን እና ሱልጣኔት የሚሉ ቃላትን አብራርታችሁ በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ።

በኢትዮጵያ እና በአፍሪካ ቀንድ ለተመሰረቱት የሙስሊም ሱልጣኔቶች ዋናውን ሚና የተጫወቱት ንግድ እና የእስልምና ሃይማኖት ነበሩ። የእስልምና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በንግድ እና በንግድ መስመሮች በኩል ነበር። እስልምና ወደ ኢትዮጵያ በዳህላክ ደሴቶች፣ በዘይላ እና በርበራ በኩል ገብቷል። በሰሜን የሀገራችን ክፍል እስልምና እምብዛም መስፋፋት አልቻለም። ምክንያቱም በሰሜን ደጋማ ስፍራዎች የክርስትና እምነት ተከታዮች በመኖራቸው እስልምና በቀይ ባህር አዋሳኝ ጠረፎች ብቻ ሊገደብ ችሏል።

ለእስልምና መስፋፋት እና ለሙስሊም ሱልጣኔቶች መመስረት ከፍተኛውን ሚና የተጫወቱት በዘይላ በኩል ወደ ውስጥ ዘልቆ ይገባ የነበረው የንግድ መስመር፣ የሙስሊም አረብ ነጋዴዎች፣ በሙስሊም አረቦች እና በአካባቢው አርብቶ አደር ማህበረሰቦች መካከል የነበረው ሰላማዊ ግንኙነት ይጠቀሳሉ። የክርስትና ሃይማኖት ባልደረሰባቸው የምስራቅ እና ደቡብ ምስራቅ አካባቢዎች እስልምና ከፍተኛ ተከታዮችን አፍርቷል። የእስልምና ሃይማኖት ሐረር፣ ወሎ፣ ባሌ፣ አርሲ እና ሌሎችንም የኢትዮጵያ ግዛቶች አዳርሷል። የእስልምና መግባት እና የንግድ መስፋፋት የዘይላ የንግድ መስመሮች በሚያልፍባቸው አካባቢዎች በሱልጣን የሚመሩ የሙስሊም ሱልጣኔቶች ተመስርተዋል።

**ተግባር-12**

1. በንግድ መስመር አካባቢ የሙስሊም ሱልጣኔቶች ለምን ሊመሰረቱ ቻሉ? ከጎናችሁ ካለው/ችው ተማሪ ጋር ተወያዩ::
2. እስልምና ወደ ኢትዮጵያ በሰላማዊ መንገድ እንደገባ ተምራችኋል:: ይህም ለማህበረሰባዊ መስተጋብር የነበረውን ጠቀሜታ በቡድን ተወያይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁላቸው::

### ሀ) የዳህላክ ሱልጣኔት

**ተግባር-13**

1. ለአክሱም ስልጣኔ መውደቅ ምክንያቶቹን አስታውሳችሁ ለመምህራችሁ ግለፁ::

ዳህላክ በቀይ ባህር ለሚገኙ ደሴቶች የጋራ/የወል መጠሪያ ነው:: አረቦች አዶሊስን በ702 ዓ.ም በመያዝ ዳህላክ ደሴት ላይ ሰፍረዋል:: በ10ኛው ክፍለ ዘመን በደሴቱ ላይ ከእስልምና ሃይማኖት መስፋፋት በኋላ የሙስሊም ሱልጣኔት ተመስርቷል:: የደሴቱ ኢኮኖሚ የተመሰረተው በንግድ ነበር:: ዘይላ ዋና የንግድ ማዕከል ከመሆኗ በፊት የውጭ ንግድ የሚካሄደው በዳህላክ ደሴቶች በኩል ነበር:: የዳህላክ ሱልጣኔት የአረቦች እና የኢትዮጵያን መንግስታት ትኩረት ስባ ነበር:: እነዚህ መንግስታት የዳህላክ ሱልጣኔትን ለመቆጣጠር ቢሞክሩም የዳህላክ ሱልጣኖች በሰላማዊ መንገድ የግዛታቸውን ነፃነት አስጠብቀዋል:: በኦቶማን ቱርኮች በ16ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በመያዛቸው ሀያልነታቸው አከተመ::

**ተግባር-14**

1. ዳህላክ እና ዘይላ የሚባሉ ቦታዎችን የንድፍ ካርታ በመሳል አሳዩ::
2. የዳህላክ ሱልጣኔት የአረቦችን እና የኢትዮጵያን መንግስታትን ትኩረት ሊስብ ለምን ቻለ? ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩላቸው::

### ለ) የይፋት ሱልጣኔት

**ተግባር-15**

1. ስለ ገባር እና ግብር የምታውቁትን ለመምህራችሁ ግለፁ::

የይፋት ሱልጣኔት በ13ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ተመሰረተ። የይፋት ሱልጣኔት መስራቹ እና ገዥው ዑመር ወላስማ ነበር። የኢትዮጵያን ውስጣዊ ግዛቶች ከዘይላ ወደብ ጋር የሚያገናኙ የንግድ መስመሮች የሚያልፉት በይፋት ሱልጣኔት ግዛት ውስጥ ነበር። የይፋት ሱልጣኔት መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ የአካባቢውን ንግድ በበላይነት እንዲቆጣጠር አስችሎት ነበር። የአካባቢው ህዝብም እስልምናን ሊቀበል ችሏል።

የይፋት ሱልጣኔት በኢትዮጵያ ውስጥ ከነበሩት ሱልጣኔቶች ግንባር ቀደምና በጣም ጠንካራ ነበር። በ14ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ ይፋት ተጎራባች ከነበሩት የሙስሊም ሱልጣኔቶች ላይ የበላይነቱን አስፍኗል። ይህ የይፋት የበላይነት ያከተመው በአፄ አምደ ፅዮን የግዛት ማስፋት ዘመቻ ነበር። ሱልጣን ሰብረዲን የሱልጣኔቱን ነፃነት ለማስከበር ተደጋጋሚ ዘመቻዎችን ከአፄ አምደ ፅዮን ጋር ቢያደርግም ተሸንፎ ገባር ሱልጣን ሆኗል።

### ተግባር-16

1. የይፋት ሱልጣኔት የነበረችው አሁን በየትኛው የኢትዮጵያ ክፍል ትገኛለች?

## ሐ) የሀዲያ ሱልጣኔት

### ተግባር-17

1. ስለ ባሪያ ንግድ የምታውቁትን ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩላቸው።

የሀዲያ ሱልጣኔት መቼ እንደተመሰረተ የሚጠቁም መረጃ አልተገኘም። የሀድያ ሱልጣኔት ለመጀመሪያ ጊዜ የታወቀው ለአፄ አምደ ፅዮን ገባር ከሆነ በኋላ ነበር። የሀዲያ ሱልጣኔት ኢኮኖሚ የተመሰረተው በግብርና እና በንግድ ነበር። የሀዲያ ሱልጣኔት ባሪያን ለንግድ በማቅረብ ይታወቅ ነበር። አፄ አምደ ፅዮን በ1316 ዓ.ም የሀዲያ ሱልጣኔትን አስገብሯል።

### መ) የባሌ ሱልጣኔት

**ተግባር-18**

1. ባሌ የሚባለውን ቦታ የንድፍ ካርታ በመሳል አሳዩ::

የባሌ ሱልጣኔት መቼ እንደተመሰረተ መረጃ አልተገኘም:: ለደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት ከ14ኛው ክፍለ ዘመን እስከ 16ኛው ክፍለ ዘመን ገብሯል:: የባሌ ሱልጣኔት ገዥዎች ገራድ የሚባል ማዕረግ ይጠቀሙ ነበር:: የባሌ ሱልጣኔት በኢትዮጵያ ደቡባዊ ግዛት ላይ ሲገኝ ከደቡብ አቅጣጫ በስተቀር ዙሪያውን በሌሎች ሱልጣኔቶች የተከበበ ነበር:: የባሌ ሱልጣኔት በሰሜን ደዋሮ እና ሻርካ፣ በምዕራብ ሀድያ እና በምስራቅ አዳል ያዋስኑት ነበር::

**ተግባር-19**

1. ገራድ የሚባለው የስልጣን መጠሪያ ስያሜው ምንድን ነው?
2. ስለባሌ ሱልጣኔት ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ሪፖርት አቅርቡ::

### ሠ) የአዳል ሱልጣኔት

**ተግባር-20**

1. ስለ ደከር እና ሀረር የምታውቁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩላቸው::

የአዳል ሱልጣኔት በ14ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ተመሰረተ:: ከይፋት ጋር የጋራ ታሪክ ነበራቸው:: ሁለቱም በወላስማ ስርወ መንግስት ስር ነበሩ:: የይፋት ሱልጣኔት በደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት ገባር ከሆነ በኋላ የገዥ መደብ አባላቱ በሁለቱ ቡድኖች ተከፍለው ነበር:: የመጀመሪያው የነጋዴዎች ስብስብ የደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት በይፋት ሱልጣኔት ላይ ያለውን የበላይነት አምኖ ለመቀበል የወሰነ ነበር::

ሁለተኛው ቡድን ግን የይፋት ሱልጣኔትን ራስ ገዝነትን ለማስመለስ የቆረጠ ነበር:: የይፋት ሱልጣኔት በአቀማመጡ ለደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት ቅርብ ስለነበረ የሱልጣኔቱ የትግል ማዕከል ሊሆን አልቻለም:: በዚህም ምክንያት ሁለተኛው ቡድን በደቡብ ምስራቅ የሐረር ቆላማ ቦታዎች በማፈግፈግ የአዳል ሱልጣኔትን በ1380 ዓ.ም መሰረቱ:: የመጀመሪያው የሱልጣኔቱ ማዕከል ደከር ከጊዜ በኋላ

ደግሞ ሐረር ሆነ::

## ተግባር-21

1. ቤተ መፃህፍት በመግባት ስለ ሌሎች የሙስሊም ሱልጣኔቶች አመሰራረት፣ የገቢ ምንጭ እና ከደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት ጋር የነበራቸውን ግንኙነት የተመለከተ ዘገባ አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ::

### 4.2.3. የአዳል ሱልጣኔት እና የደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት ጦርነት

## ተግባር-22

1. የአዳል ሱልጣኔት እንዴት እንደተመሰረተ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ::

የሙስሊም ሱልጣኔቶች እና የደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት ጦርነቶች መነሻ ምክንያቶች አንደኛው የዘይላ የንግድ መስመርን እና በንግዱ የሚገኘውን ሀብት ለመቆጣጠር ነበር:: ሁለተኛው የደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት የሙስሊም ሱልጣኔቶችን ለማስገበር ሲሆን የሙስሊም ሱልጣኔቶች ደግሞ በደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት ያጡትን ግዛቶቻቸውን ለማስመለስ እና ራስ ገዝነታቸውን ለማስከበር ነበር:: የሙስሊም ሱልጣኔቶች እና የደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት ጦርነት በሁለት ዘመናት ከፍሎ ማየት ይቻላል:: የመጀመሪያው ከ1314 -1527 ያለው ዘመን ሲሆን አፄ አምደ ፅዮን (1314-1344) የግዛት መስፋፋት ዘመቻ ጀምሮ እስከ ኢማም አህመድ የአዳል ሱልጣኔት ኢማም እስከሆኑበት ያለውን ጊዜ ያካትታል::

በዚህ ጦርነት አፄ ሰይፈ አርዕድ(1344-1370) ከኢፋት ሱልጣን ሰብረዲን ጋር፣ አፄ ዳዊት (1382-1413) ከሶስት የሙስሊም ሱልጣኔት ሱልጣኖች ጋር ተዋግተዋል:: ሀቀዲን ሁለተኛን በ1387፣ ሰዓዳዲንን በ1403፣ እና ሱልጣን አህመድን በ1430 አሸንፈው ነበር:: አፄ ይስሃቅ (1413-1430) መጠነ ሰፊ ጦርነቶችን ከሙስሊም ሱልጣኔት ሱልጣኖች ጋር አድርገዋል:: አፄ ዘርዓያቆብ (1434-1468) ሱልጣን አህመድ እና ገራድ ማሂኮ የሚባሉ የሀድያ ሱልጣኔት ሱልጣኖችን በመግጠም አሸንፈዋል:: የአፄ በዕደ ማርያም (1468-1478)፣ አፄ እስክንድር (1478-1494) እና አፄ ናኦድ (1494-1508) ያደረጓቸውን ጦርነቶችንም ያካትታል:: በዚህ ጦርነት የበላይነት የደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት ነበር::

ሁለተኛው ከ1527-1543 የሙስሊም ሱልጣኔቶች (በኢማም አህመድ ኢብን ኢብራሂም አል ጋአዚ / አህመድ ግራኝ) እና የደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት በአፄ ልብነ ድንግል (1508-1540) እንዲሁም ከአፄ ገላውዴስ (1540-1559) ጋር ጦርነት ገጥመዋል፡፡ በዚህ ጦርነት ኢማም አህመድ አሸናፊ ከመሆን አልፈው እስከ 1543 ዓ.ም የፖለቲካውን የበላይነት ይዘው ነበር፡፡ ኢማም አህመድ የሙስሊም ሱልጣኔቶችን በማስተባበር ጦርነቱን በ1527 ዓ.ም በሽምብራ ኩሬ ጀመሩ፡፡ በዚህ ጦርነት በአፄ ልብነ ድንግል ስር የነበሩት ግዛቶች በኢማም አህመድ ተያዙ፡፡ ከ1531-1535 ባሉት ዘመናት ደዋሮ፣ ባሌ፣ ወጅ፣ ደብረ ብርሀን፣ ትግሬ እና የቀይ ባህር አካባቢዎችን ተቆጣጥረዋል፡፡

ይህን ያልተጠበቀ የኢማም አህመድን ስኬት ለመቀልበስ አፄ ልብነ ድንግል የፖርቱጋሎችን እገዛ ለማግኘት በ1535 ዓ.ም ቤርሙደዝ የተባለ ፖርቱጋላዊ ሚሲዮን ልከው በ1541 ዓ.ም 400 የፖርቱጋል ወታደሮችን ማግኘት ቻሉ፡፡ በተመሳሳይ ቀደም ብሎ ኢማም አህመድ ደግሞ 900 ወታደሮችን ከቱርክ ለማግኘት ችለው ነበር፡፡ በ1543 ዓ.ም ወይናደጋ በተባለው የጦር አውድማ ኢማም አህመድ ተሸነፉ፡፡ የጦርነቱ ውጤቶች ከሆኑት ውስጥ ከሁለቱም ወገን የሰዎች እና የንብረቶች መጥፋት፣ የደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት ጠንካራ ወታደሮቹን ማጣት፣ የህብረተሰብ ፍልሰት፣ በቆላማ አካባቢ ይኖሩ የነበሩት ሙስሊሞች ደጋማ አካባቢ ከሚኖሩት ክርስቲያኖች ጋር አብሮ መኖር፣ የፖርቱጋሎችን እና የኦቶማን ቱርኮችን ጣልቃ ገብነት እና ለኦሮሞ ህዝብ መስፋፋትም እድል ፈጥሯል፡፡

**ተግባር-23**

1. የ16ኛው ክፍለዘመን የሙስሊም ሱልጣኔቶች እና የደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት ጦርነቶች ያስከተሉትን አሉታዊ እና አዎንታዊ ገፅታዎች በመለየት ሪፖርት አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ዘገባ አቅርቡ፡፡

### 4.2.4. የኦሮሞ ህዝብ መስፋፋት

**ተግባር-24**

1. በምትኖሩበት አካባቢ ሰዎችን ከሚኖሩበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እንዲሄዱ የሚያደርጓቸውን ሁነቶች በመለየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡

ኦሮሞ የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝብ ነው:: እንደ ኦሮሞ አፈ ታሪካዊ መረጃዎች ኦሮሞዎች ከመስፋፋታቸው በፊት መኖሪያቸው በዛሬው የባሌ ከፍተኛ ቦታ (መዳ ወላቡ) እንደነበረ ይነገራል:: ለኦሮሞ ህዝብ መስፋፋት ምክንያቶች የህዝብ ቁጥር መጨመር፣ የግጦሽ መሬት ፍለጋ እና በገዳ ስርዓት መሰረት አዲስ ቦታን መያዝ ስለሚበረታታ የሚሉት ይጠቀሳሉ:: ከ1550ዎቹ እስከ 1580ዎቹ ባሉት ጊዜያት ወደ ማዕከላዊ፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ እና ሰሜናዊ የኢትዮጵያ ግዛት ኦሮሞ በፍጥነት ተስፋፉ:: በተጨማሪም ወደ ኬንያ እና ሶማሊያ ተስፋፍተዋል::

የኦሮሞ ህዝብ መስፋፋት በመልባህ ገዳ በ1522 ዓ.ም ቢጀመርም በ1530ዎቹ ቦታዎችን መያዝ ችለው ነበር:: ይህ መስፋፋት በ1604 ዓ.ም ቀዝቀዝ ቢልም ኢናርያን ለመያዝ ዘመቻው እስከ 1710 ዓ.ም ድረስ ቆይቷል:: የኦሮሞ ህዝብ እንቅስቃሴን ውጤታማ እንዲሆን የኦሮሞ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ወታደራዊ አደረጃጀታቸው (የገዳ ስርዓት) ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል:: ከ16ኛው ክፍለ ዘመን መስፋፋት እንቅስቃሴ በፊት ኦሮሞ በሁለት የተለያዩ የጎሳ ክፍሎች የተከፈለ ነበር:: እነርሱም ቦረና እና ባሬንቱ ይባላሉ:: ቦረና በውስጡ ሜጫ እና ቱለማ፣ ጉጂ እና የደቡባዊ ቦረና ነገዶችን ሲያቅፍ ባሬንቱ ደግሞ ከረዩ፡ ኢቱ፣ ረቀ፣ አካቼ፣ ዋራንቲሻ እና ሀምባናን ያጠቃልላል::

ኦሮሞ የክርስትናን እና የእስልምናን ሃይማኖት ከመቀበላቸው በፊት የራሳቸው ሃይማኖት ነበራቸው:: የሃይማኖታቸው መሠረት ዋቃ (የሰማይ አምላክ) የመላው አለም ፈጣሪ እና ሀያል አምላክ መሆኑን ያምናሉ:: የዋቃ ሀይል የሚገለፀው አያና በሚባል መንፈስ ነው:: የኦሮሞ መንፈሳዊ መሪዎች ቃሉ ይባላሉ:: ቃሉ የኦሮሞ ሃይማኖት መሪዎች ሲሆኑ አያና ያደረባቸው ናቸው ተብሎ ይታመናል:: የኦሮሞ ህዝብ መስፋፋት ከተለያዩ የኢትዮጵያ ማህበረሰቦች ጋር መገናኘት እና ከብዙ ነገስታት ጋር ጦርነትን አስከትሏል:: የእንቅስቃሴው ውጤት በኦሮሞ ህዝብ፣ በደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት፣ በሙስሊም ሱልጣኔቶች እና በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድሯል:: የደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት ማዕከል ከዓባይ ወንዝ በስተሰሜን ወዳሉ ቦታዎች እንዲዛወር አድርጎታል:: እንዲሁም የአዳል ሱልጣኔት የግዛቱን ማዕከል ሐረርን በግንብ አጥሮ የከተማ መንግስት ሊሆን ችሏል::



ምስል 4.9 የሐረር ጀጎል የግንብ አጥር

የከፋ እና ወላይታ ግዛቶች ባደረጉት ከፍተኛ ተጋድሎ አሸናፊ በመሆን ራስ ገዝነታቸውን አስጠብቀዋል:: እንደ ዳሞት፣ ጋፋት፣ ቢዛሞ፣ ባሌ፣ ሀድያ፣ ኢፋት፣ ደዋሮ፣ ፈጠጋር የመሳሰሉት በመስፋፋቱ ምክንያት ሙሉ በሙሉ ወድመዋል::

### ተግባር-25


1. ኦሮሞ ከመኖሪያ አካባቢያቸው በመነሳት ወደ ሌላ አካባቢ እንዲስፋፉ ያደረጓቸውን ሁነቶች በትንንሽ ቡድን ከለያችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ::
2. በምትኖሩበት አካባቢ ከገዳ ስርዓት ጋር ተመሳሳይ የሆነ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ አለመግባባቶችን ሊፈታ የሚችል ማህበራዊ ተቋም ካለ አመሰራረቱን እና ተግባሮቹን በጥንድ በጥንድ በመሆን ተወያዩበት::

## 4.2.5 የመካከለኛው ዘመን ምጣኔ ሀብታዊ መሰረቶች እና ዋና ዋና የረጅም ርቀት ንግድ መስመሮች

### ተግባር-26

1. የረጅም ርቀት ንግድ እና የንግድ መስመር ሲባል ምን ማለት እንደሆነ አብራሩ::

በመካከለኛው ዘመን የንግድ መግቢያ እና መውጫ መስመሩ ከአዶሊስ ወደ ዘይላ ተዛወረ፡፡ ይህ ሲባል የሰሜኑ ንግድ እና የንግድ መስመር ሙሉ በሙሉ ተቋርጧል ማለት አይደለም፡፡ ምፅዋ በመካከለኛው ዘመንም የሰሜን ምስራቁን የሀገራችን የንግድ መውጫ በር ሆና ታገለግል ነበር፡፡ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ አቅጣጫን ተከትሎ ሀረርን፣ ደዋሮን እና ፈጠጋርን አቋርጦ የሚያልፍ የንግድ መስመር ነበር፡፡ በዚህ የንግድ መስመር ምክንያት ሀርላ፣ ሀረር፣ ጨርጨር እና ደከር ከተሞች ተመስርተዋል፡፡ በተጨማሪም በይፋት- ዋስል- አውሳ የንግድ መስመር ነበር፡፡ በመካከለኛው ዘመን የንግድ መለዋወጫ እቃዎች ውስጥ ባሪያ፣ የዝሆን ጥርስ፣ ወርቅ እና ዝባድ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ባሪያዎች ከተለያዩ አካባቢዎች በከፍተኛ ደረጃ ለአረቢያ፣ ፋርስ እና ህንድ ገበያ ይቀርቡ ነበር፡፡ አሞሌ ጨው ለንግድ ልውውጥ ያገለግል ነበር፡፡




ምስል 4.10 የመካከለኛው ዘመን ረጅም ርቀት ንግድ መስመሮች

## 4.2.6. የጎንደር ዘመን

*ተግባር-27*

1. አፄ ፋሲል እና የጎንደር ዘመን ሲባል ስምታችሁ ታውቃላችሁ? ከጎናችሁ ካለው/ችው ተማሪ ጋር ስለምታውቁት ነገር ተወያዩ።
2. ዜጎችን በሀገራቸው ሀብት እኩል ተጠቃሚ ማድረግ ጠቀሜታው ምን እንደሆነ ለመምህራችሁ ግለፁ።

አፄ ሱስንዮስ (1607-1632) በ1607 ነግሰው ዋና ከተማቸውን ደንቢያ አደረጉ። አስተዳደራዊ መዋቅሩ ያልተማከለ ይዘት ነበረው። ለአካባቢያዊ ገዥዎች ግዛታቸውን ከወረራ የመጠበቅ፣ ግብር የመሰብሰብ እና አካባቢያዊ ሰራዊቶችን የማዘጋጀቱን ስልጣን ሰጥተዋቸው ነበር። አፄ ፋሲለደስ (1632-1667) ሀገራዊ እና ሀይማኖታዊ አንድነትን ለማምጣት ጎንደርን የደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት ማዕከል አድርገው በ1636 ዓ.ም ቆረቆሩ። ከ1636-1855 ጎንደር የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ እና የባህል ማዕከል በመሆን አገልግላለች። አፄ ፋሲለደስ ሀይማኖታዊ ክፍፍል ይፈጥሩና የሀገርን አንድነት ያጠፋሉ ያሏቸውን የውጭ ሀገር ሰዎች በ1633 ዓ.ም ከግዛቶቻቸው አስወጥተዋል። ይህን አላማቸውን ለማሳካት ከስዋኪን፣ ምፅዋ እና ቱርክ ነገስታት ጋር የጠበቀ ግንኙነት መፍጠር ችለውም ነበር።



ምስል 4.11 ጎንደር የአፄ ፋሲለደስ ቤተ መንግስት

ጎንደር ዋና ከተማ ሆና መመስረቷ የደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት የባህል ተሃድሶ እንዲጀመር አስተዋፅኦ አድርጓል:: የነገስታቱ መኖሪያ መንደር በውስጡ አስደናቂ የሆኑ ቤተ-መንግስታት፣ የአቡኑ እና የእጨጌው መኖሪያዎች እና አብያተ ክርስቲያናት እንዲገነቡ አስተዋፅኦ አድርጓል:: የስነ-ህንፃ ንድፉ የአክሱም እና የዛግዌን ነገስታት የአሠራር ጋር ይመሳሰል ነበር:: ከነገስታቱ ከመኖሪያ ግቢ ውጭ ዋና የሃይማኖታዊ ትምህርት (ምሳሌ፦የዜማ እና የቅኔ ማዕከል) የነበሩ አብያተ ክርስቲያናትም ተገንብተው ነበር:: ጎንደር ዋና የንግድ ማዕከል ነበረች:: ከጎንደር ከተማ ሁለት የንግድ መስመሮች የሚነሱ ሲሆን አንዱ ወደ ሰሜናዊ የኢትዮጵያ ክፍል ሌላው ደግሞ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ሱዳን ይደርሳል:: በጎንደር በየዕለቱ በሚውለው ገበያ የውጭ ሀገር ነጋዴዎች፣ የከተማው ነዋሪዎች እና የገጠሩ ህዝብ የተለያዩ ምርቶቻቸውን ይለዋወጡ ነበር:: ቤተ-እስራኤላዊያንም በግንበኝነት፣ በሽክላ፣ ቅርጫት እና የብረታብረት ሥራዎች ላይ ተሰማርተውም ነበር::

በቀዳማዊ አፄ ዮሐንስ(1667-1682) እስልምና በመንግስቱ ግዛት ውስጥ የተስፋፋ ሲሆን ለሙስሊሙ ማህበረሰብ፣ ለቤተ-እስራኤላዊያን፣ አርመኖች፣ ህንዶች እና ለግሪክ ነጋዴዎች ከከተማዋ ዳር ባለ መንደር እንዲሰፍሩ አድርገዋል:: ታላቁ ወይም ቀዳማዊ አፄ እያሱ (1682-1706) ወደ ሸዋ ዘምተው ለሸዋ ነገስታት ዕውቅና ሰጥተው ዓመታዊ ግብር አሰብስበው ነበር:: የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ህግ መፅሐፍ የነበረው ፍትሐ ነገስትን አሻሽለዋል:: አፄ እያሱ ከነበረባቸው የቆዳ በሽታ ለመፈወስ ፈረንሳዊ ሀኪምን ጃኮስ ፓንሴትን (1699-1700) በማስመጣት ታክመዋል:: ይህን ተከትሎም ሶስት ሚሲዮናዊያን ለጉብኝት መጥተው ነበር:: በተጨማሪም አፄ እያሱ ሰባት ወጣት ክርስቲያን ኢትዮጵያዊያንን ያካተተ የመልዕክተኞች ቡድን ወደ ሮማው ጳጳስ ልከው ነበር::

አፄ በካፋ(1721-1730) በጎንደር ከነገሱት ተፅዕኖ ፈጣሪ ነገስታት መካከል አንዱ ነበሩ:: አፄ በካፋ እቴጌ ምንትዋብን አግብተው እያሱ ትንሹን ወልደዋል:: እቴጌ ምንትዋብ የራሳቸውን ቤተ መንግስት ገንብተዋል:: ግብር ለማስገበር ወደ በጌምድር፣ ደንቢያ እና ላስታ ዘምተዋል:: ዳግማዊ አፄ እያሱ ወይም ‹‹እያሱ ትንሹ››(1730-1755) በዕድሜ ልጅ ንጉስ ስለነበሩ በእናታቸው በእቴጌ ምንትዋብ ሞግዚትነት ማስተዳደር ችለው ነበር:: አፄ እያሱ ውቢት የተባለችውን የወሎ ኦሮሞ አግብተው እዮዓስን ወለዱ::

በአፄ እዮዓስ(1755- 1769) ዘመን በጎንደር ቤተ መንግስት ኦሮምኛ መነገር ጀምሮ ነበር:: የኦሮሞ ጠባቂ ወታደሮችም ነበሯቸው:: እቴጌ ምንትዋብ በልጅ ልጃቸው ላይ የተነሳውን የተቃውሞ ጎራ ተቀላቅለው ነበር:: ተቃውሞው የተፈጠረው

በቤጌምድር ግዛታቸው ነበር፡፡ ተቃውሞ ለማርገብ እቴጌ ምንትዋብ የትግሬውን ገዥ ራስ ሚካኤል ስሁልን የበላይ ጠባቂው እንዲሆኑ ጋበዘቻቸው፡፡ ራስ ሚካኤልም ግዙፍ ሠራዊታቸውን በማስከተል ጎንደር ገቡ፡፡ ነገር ግን ራስ ሚካኤል አፄ እዮዓስ በ1769 ዓ.ም አስገድለው ዳግማዊ አፄ ተክለ ኃይማኖትን (1769-1777) አነገሱ፡፡

**ተግባር-28**

1. ተማሪዎች ስለ ጎንደር ዘመን በመማራችሁ ምን የሚጠቅም ነገር አገኛችሁ?

## 4.2.7. ዘመነ መሳፍንት (1769-1855)

**ተግባር-29**

1. የመስፍን፣ መሳፍንት፣ መኮንን እና መኳንንትን ምንነት አብራሩ፡፡

ዘመነ መሳፍንት የማዕከላዊ መንግስት ስልጣን የተዳከመበት እና የአካባቢ ባላባቶች ሀይል የገነነበት ጊዜ ነበር፡፡ በዚህ ዘመን ኢትዮጵያ በበርካታ ግዛቶች የተከፋፈለችበት እና የማዕከላዊ መንግስት የተዳከመበት ነበር፡፡ ለዘመነ መሳፍንት መጀመር አስተዋፅኦ ካደረጉ ምክንያቶች ውስጥ ዋናው መንስኤ የነገስታቱ ስልጣን እና ሀይል ቀስ በቀስ እየተሸረሸረ መምጣት ቢሆንም ለዘመነ መሳፍንት መጀመር ሰበብ የአፄ እዮዓስ በ1769 መገደል ነበር፡፡

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ስልጣን የተያዘው በራሶች እጅ ነበር፡፡ ራሶች የነገስታቱ ሿሚና ሻሪ መሆን ችለው ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት የተለያዩ መሳፍንት የትግል ጥረት ራስ የሚለውን ማዕረግ ወይም የግዛቱ ራስ የመሆን ፍላጎት ነበር፡፡ በጣም ጠንካራ የነበሩ የአካባቢ ባላባቶች ጎንደር ከነበረው ማዕከላዊ መንግስት እውቅና ውጭ የራሳቸውን የውጭ ግንኙነት መስርተውም ነበር፡፡

በሌላ በኩል በዘመነ መሳፍንት ወቅት በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ላይ አደጋ ተጋርጦበት ነበር፡፡ የግብፅ ገዥ መሀመድ አሊ በ1821 ዓ.ም ሀይሉን በማጠናከር የቀይ ባህርን የንግድ መስመር ከመቆጣጠሩም በላይ ምፅዋን መያዝ ችሎ ነበር፡፡ በተጨማሪም የአሚሮች መቀመጫ፣ የንግድ እና የእስልምና ትምህርት ማዕከል የሆነችውን ሐረርን መያዛቸው ሀገራዊ ችግር መከሰቱን ይጠቁማል፡፡ ሀገርን ከወረራ የመከላከሉ ኃላፊነት በአካባቢያዊ መሳፍንቶች ትከሻ ላይ ወድቆ ነበር፡፡ ለሀገራቸው ነፃነት

መስዋዕትነት ከከፈሉት መካከል የሰሜኑ ደጃዝማች ውቤ፣ የቋራው ደጃዝማች ክንፉ እና የቋራው ካሣ ሀይሉ ተጠቃሽ ነበሩ።



ምስል 4.12 በዘመነ መሳፍንት የነበረውን ዘመቻ የሚያሳይ

የዘመነ መሳፍንት ብጥብጥ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በተለይም በገበሬው ላይ ከባድ ተፅዕኖ ነበረው። ገበሬው በመሳፍንቱ የማይቋረጥ ጦርነት እንዲሳተፍ መገደድ፤ ያመረተው ምርት በባላባቶች ሠራዊት መዘረፍ፤ የእርሻ ማሳው የጦር አውድማ መሆን እና ለመሳፍንት የሚያስፈልጋቸውን ስንቅ ማቅረብ የገበሬው ግዴታ ነበር። በዚህም ምክንያት በርካታ ገበሬዎች መደበኛ ሥራቸውን በመተው ሽፍትነትን መርጠው ነበር። ነጋዴዎችም በሽፍታዎች የመዘረፍ እና በተለያዩ መሳፍንት ኬላዎች ላይ ተደራራቢ ቀረጥ እንዲከፍሉ በመገደዳቸው የንግድ እንቅስቃሴው ተዳክሞ ነበር። የባህል እና የእደጥበብ እንቅስቃሴም በተመሳሳይ ሁኔታ ተዳክሟል። ሌላው የዘመነ መሳፍንት ጦርነቶች ውጤት የኢትዮጵያ ህዝብ ብሔራዊ ስሜት ያሽቆለቆለበት ጊዜም ነበር። ስለዚህ ዘመነ መሳፍንት በኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ኋላቀርነትን አስከትሏል።

## ተግባር-30

1. ዘመነ መሳፍንት በምን በምን ምክንያቶች ሊፈጠር ቻለ? ምክንያቶቹን ዘርዝሩ።
2. ዘመነ መሳፍንት በኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ኋላቀርነትን አስከትሏል። ያስከተለውን ችግር በቡድን ተወያይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

## ማጠቃለያ

- ሀገራችን ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ትገኛለች፡፡ ቀደምት ስልጣኔ ከተመሰረተባቸው የአለም ሀገሮች መካከል አንዷ ናት፡፡ የፑንት እና የዳዓማት መንግስታት ከአክሱም ስልጣኔ መጀመር በፊት የተመሰረቱ ቀደምት ስልጣኔዎች ነበሩ፡፡
- የአክሱም ስልጣኔ የተመሰረተው ጥንታዊ ዳዓማት ያስተዳድረው ከነበረው ቦታ ላይ ማዕከሉን አክሱም አድርጎ ነበር፡፡ ከ4ኛው እስከ 7ኛው ክፍለ ዘመን አክሱም ከፍተኛ የስልጣኔ ደረጃ ላይ የደረሰችበት ወቅት ነበር፡፡ ንግድ እና እርሻ የአክሱም መንግስት ዋና የገቢ ምንጮች ነበሩ፡፡
- አክሱም ስልጣኔ ሲዳከም የዛግዌ ስርወ መንግስት ማዕከሉን ላሊበላ አድርጎ ማስተዳደር ቢጀምርም በገዥው መደብ አባላት መካከል የነበረው የእርስ በርስ የሥልጣን ሽኩቻ ምክንያት ስርወ መንግስቱ እንዲከስም አድርጎታል፡፡
- የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1270 ዓ.ም እስከ 1855 ዓ.ም ያለውን ጊዜ ያካትታል፡፡ ይህ ዘመን ደግሞ የሰለሞናዊ ስርወ መንግስት ዳግም የተመስረተበት ጊዜ ነበር፡፡ የደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት መስፋፋት በሚያደርጉበት ጊዜ ከሙስሊም ሱልጣኔቶች ጋር በዘይላ የንግድ መስመር እና በሚገኘው ጥቅም ምክንያት ወደ ግጭት እንዲያመሩ አደረጋቸው፡፡
- የሙስሊም ሱልጣኔቶች እና የደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት ግጭት ደግሞ የኦቶማን ቱርክ እና የፖርቱጋልን ጣልቃ ገብነት አስከትሎ ነበር፡፡ ይህ የሚያሳየው ደግሞ ጦርነቱ የውጭ ተፅዕኖ እንዳለበት ነው፡፡ ነገር ግን ጦርነቱ ሀይማኖታዊ አልነበረም፡፡
- ለኦሮሞ ህዝብ መስፋፋት ከረዱ ታሪካዊ ሁነቶች ውስጥ የሙስሊም ሱልጣኔቶች እና የደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት ጦርነት፣ የገዳ ስርዓታቸው እና የግጦሽ መሬት ፍላጎት ነበሩ፡፡
- የጎንደር ዘመን እንዲመሰረት እና ጎንደር የደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት መናገሻ እንድትሆን ያደረገው ታሪካዊ ድርጊት በሙስሊም ሱልጣኔቶች እና በደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት መካከል የነበረው ጦርነት አንዱ ምክንያት ነበር፡፡

# የክለሳ ጥያቄዎች

**ክፍል አንድ፡- ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በትክክል ካነበባችሁ በኋላ ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆነ ደግሞ ሀሰት በማለት መልሱ፡፡**

1. ፑንትና ዳዓማት ከአክሱም በፊት የተመሰረቱ ስልጣኔዎች ነበሩ፡፡
2. የዛግዌ እና የአክሱም መንግስታት ደቡባዊ ወሰናቸው ኤርትራ ነበር፡፡
3. በ1632 ዓ.ም ጎንደር የሀገራችን ሶስተኛ ቋሚ ከተማ ሆና ተመሰረተች፡፡
4. በመካከለኛው ዘመን ከነበሩት የንግድ መስመሮች ውስጥ አንዱ ዋስልን ያቋርጥ ነበር፡፡

**ክፍል ሁለት፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተስማሚውን መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ፡፡**

1. ለአክሱም ስልጣኔ መጀመር እና ማደግ ከረዱ ዋና ዋና ምክንያቶች የማይመደበው የቱ ነው?
   ሀ) በአካባቢው የነበረው ቅድመ አክሱም ስልጣኔ
   ለ) የአክሱም መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ
   ሐ) የቀይ ባህር ንግድ እድገት
   መ) የዘይላ ወደብን መጠቀም መቻል
2. ለአክሱም መንግስት መዳከም ውስጣዊ ምክንያት የሆነው የቱ ነው?
   ሀ) የአረብ ሙስሊሞች መነሳት እና በቀይ ባህር ንግድ ላይ ተፎካካሪ ሆኖ መገኘት
   ለ) ሙስሊም አረቦች የዘይላ ወደብን መቆጣጠር
   ሐ) አክሱማዊያን ከንግድ ሲያገኙ የነበረውን ገቢ ማጣት
   መ) የቤጃ አርብቶ አደሮች ከፍተኛ ተቃውሞ እና አመፅ
3. ለዛግዌ ስርወ መንግስት መውደቅ ምክንያት የሆነው ፡-
   ሀ) የአዶሊስ ወደብ መደምሰስ
   ለ) የባላባቶችና የሃይማኖት መሪዎች ተቃውሞ
   ሐ) የዘይላ የንግድ መስመር በሊሙ ኢናርያ እጅ መውደቅ

መ) የውጭ ሃይሎች ወረራ

**ክፍል ሶስት፡ አጭር መልስ ስጡ**

1. ጥንድ ጥንድ በመሆን በአክሱም እና ዛግዌ ስርወ መንግስታት መካከል ከተፈጠሩት ታሪካዊ ሁነቶች ውስጥ የሚያመሳስሏቸውን ብቻ በመለየት አብራሩ።
2. የክርስትና ሀይማኖት ወደ ሀገራችን መግባት ጋር ተያይዞ የተከሰቱ ለውጦችን በመለየት አብራሩ።
3. የአፄ ፋሲለደስን የዝግ በር ፖሊሲን በመገምገም ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ።
4. የደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት ነገስታት የግዛት የማስፋፋት ዘመቻ ምን ውጤት ነበረው።
5. የኦሮሞ ህዝብ መስፋፋት ስኬታማ እንዲሆን ያደረጉት ሁነቶችን በመለየት አብራሩ።
6. ጎንደር እንዴት ልትመሰረት ቻለች? በጎንደር ዘመን የታዩትን ታሪካዊ ሁነቶች በመለየት አብራሩ።
7. ዘመነ መሳፍንት በሀገራችን ያስከተለውን ችግር በመለየት አብራሩ።

**ፈታኝ ጥያቄዎች**

1. ወደ ቤተ መፃህፍት በመሄድ ስለ አፄ አምደ ፅዮን ታሪክ፣ በዘመናቸው ስለሰሩት ስራ፣ ስላደረጉት ጦርነት አንድ ገፅ ፃፉ። የፃፋችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።
2. በመካካለኛው ዘመን የፖርቱጋሎች እና የቱርኮች ጣልቃ ገብነት ከፍተኛ ነበር። የዚህ ጣልቃ ገብነት መሰረታዊ ምክንያት ምን ምን እንደሆነ ቤተ መፃህፍት በመሄድ መፃህፍትን በማንበብ ያገኛችሁትን አንድ ገፅ ሪፖርት ፃፉ?። ክፍል ውስጥ ለጓደኞቻችሁ አስረዱ።
3. ከ1413-1527 ድረስ በጠንካራ መሰረት የተገነባውን የደጋው ክርስቲያናዊ ግዛት እንዴት ኢማም አህመድ ሊያሸንፈው ቻለ?

## የቃላት ፍች

- ☞ አርኪኦሎጂ- በመሬት ውስጥ የተቀበሩ ቅርሶች ጥናት ወይም የእንስሳትና እፅዋት ቅሬተ አካል ቁፋሮ ጥናት ማለት ነው።
- ☞ ሙካሪብ- አለማዊ እና መንፈሳዊ የሆኑ ንጉሳን ማዕረግ ማለት ነው።
- ☞ ወደብ- ደረቅ የመሬት ክፍል ወይም በባህር ዳርቻ የሚገኝ እቃዎች የሚራገፉበት እና የሚጫኑበት ቦታ ማለት ነው።
- ☞ ርስት- የገበሬዎች መሬት ይዞታ ሲሆን ከዘር ወደ ዘር የመሚተላለፍ ነው።
- ☞ ጠረፍ- ከአንድ ሀገር ማዕከል ራቅ ያለ ቦታ ማለት ነው።
- ☞ ሽኩቻ- በስልጣን ፈላጊዎች መካከል የሚፈጠር አለመግባባትን ያመለክታል።
- ☞ ቤተ ክህነት- የኦርቶዶክስ እምነት የአስተዳደር ጉዳዮች ፈጻሚ አካል ማለት ነው።
- ☞ ባህረ ሰላጤ- በደረቅ መሬት መካከል የሚገኝ የውሀ አካል ማለት ነው።
- ☞ ቋጥኝ- ግዙፍ ድንጋይ ማለት ነው።
- ☞ አፈ ታሪክ- ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል የሚተላለፍ ታሪክ ነው።
- ☞ ሰለሞናዊያን- ከንጉስ ሰለሞን የዘር ሀረግ አለን ብሎ መንገስን ያመለክታል።
- ☞ ሂጅራ - በዚህ መፅሐፍ የነብዩ ሙሐመድ ተከታዮች ከመካ ወደ ኢትዮጵያ ያደረጉትን ጉዞ የሚገልፅ ቃል ነው።

# ምዕራፍ-5

# የአፍሪካ ታሪክ እስከ 1500

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ በአፍሪካ የሰው ልጅ ስልጣኔ ከታየበት ጀምሮ እስከ 1500 ዓ.ም ያሉትን ጊዜያት ያጠቃልላል፡፡ በዚህ ምዕራፍ በአፍሪካ የተከሰቱ ዋና ዋና ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ክስተቶችን ይዳስሳል፡፡ እነሱም የአፍሪካ ቋንቋዎች፣ የአባይ ሸለቆ ሥልጣኔዎች፣ የምዕራብ አፍሪካ ጥንታዊ መንግስታት፣ የደቡብ እና ምስራቅ አፍሪካ መንግስታት፣ የምስራቅ አፍሪካ ጠረፋማ ማህበረሰቦችን ታሪክ በአጭሩ ዳስሷል፡፡

**ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት፡**

*ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦*

- ☞ የአፍሪካ እናት ቋንቋ ቤተሰቦች የሚገኙበትን አካባቢዎች በአፍሪካ ካርታ ላይ ታሳያላችሁ፡፡
- ☞ የጥንታዊ ግብፅ ስልጣኔ አበርክቶዎች ምን ምን እንደሆኑ ታብራራላችሁ፡፡
- ☞ የምዕራብ አፍሪካ ጥንታዊ መንግስት ምስረታን ታወዳድራላችሁ፡፡
- ☞ የኩሽ ዋና ዋና ታሪካዊ መገለጫዎችን ትለያላችሁ፡፡
- ☞ በምስራቅ እና ደቡብ ምስራቅ አፍሪካ የነበሩ መንግስታትን አነሳስና ክስመት ትገመግማላችሁ፡፡
- ☞ አፍሪካዊያን ጥንታዊ መንግስታት ያላቸው መሆኑን ታደንቃላችሁ፡፡

# 5.1. የአፍሪካ ቋንቋዎች

## ተግባር-1

1. ቋንቋ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ቋንቋ ለምን ይጠቅማል? ለክፍል ጓደኞቻችሁ ጥቅሙን አስረዱ::

በአፍሪካ ብዛት ያላቸው ቋንቋዎች አሉ:: በጣም በርካታ ተናጋሪዎች ያሉት የመጀመሪያው ስዋሂሊ፣ ሁለተኛው ሀውሣ ሲሆን ሶስተኛው ደግሞ የሩባ ናቸው:: ምሁራን የአፍሪካን ቋንቋዎች በአራት ዋና ዋና የእናት ቋንቋ ምድቦች ይከፍሏቸዋል:: እነሱም አፍሮ-እስያዊ፣ ናይሎ-ሰሐራዊ፣ የኒጀር ኮንጎ እና ኮይሳን ናቸው:: በተጨማሪም የኦስትሮኔዥያ ቋንቋም በማዳጋስካር ደሴት ይነገራል::




ምስል 5.1. የአፍሪካ እናት ቋንቋዎች ስርጭት

### ሀ) አፍሮ - እስያዊ

ከኒጀር ኮንጎ በመቀጠል ከፍተኛ ተናጋሪዎች ያሉት እናት ቋንቋ ነው:: ይህ እናት ቋንቋ የሴም፣ የኩሽ፣ የበርበር፣ የቻድ እና የኦሞ ንዑስ የቋንቋ ክፍሎችን ይዟል:: ከበርበር እና ቻድ ንዑስ ቋንቋዎች ውጭ ሌሎቹ በሀገራችን ይነገራሉ:: በሰሜን አፍሪካ ማለትም ሞሮኮ፣ አልጀሪያ እና ቱኒዚያ በስፋት የሚነገር እናት ቋንቋ

ነው:: በአፍሪካ ቀንድ የሚነገሩትን አማርኛ፣ ሶማሊኛ፣ ኦሮምኛ እና ትግርኛን ያጠቃልላል:: በናይጀሪያ፣ ኒጀር፣ ካሜሩን፣ ቤኒን እና ቻድ የሚነገረው ሀውሳም በዚሁ እናት ቋንቋ ውስጥ ይገኛል::

### ለ) ናይሎ-ሰሐራዊ

ከአፍሮ እስያዊ እናት ቋንቋ በመቀጠል ከፍተኛ ተናጋሪዎች ያሉት እናት ቋንቋ ነው:: ይህ እናት ቋንቋ ሶንጋይ፣ ኮማን፣ ቻሪ ናይል እና ሌሎችም ንዑስ የቋንቋ ቤተሰቦችን ይዟል:: በርታ፣ ፈር፣ ኩናማ፣ ጉሙዝ እና ከዱ የተባሉ ቋንቋዎችን ያካትታል:: በሱዳን፣ ደቡብ ሱዳን፣ ቻድ፣ ደቡባዊ ግብፅ፣ ሰሜናዊ ታንዛኒያ፣ ናይጀሪያ፣ ኬንያ፣ ኮንጎ ደሞክራቲክ ሪፐብሊክ፣ ኢትዮጵያ እና ኒጀር ይነገራል::

### ሐ) ኒጀር - ኮንጎ

ይህ እናት ቋንቋ በአለም ላይ ከፍተኛ ተናጋሪዎች አሉት:: በምዕራብ፣ በማዕከላዊ፣ በምስራቅ እና በደቡብ የአፍሪካ ክፍሎች ይነገራል:: ኮርዶፋዊ፣ ማንዴ፣ ቮልታይካዊ እና ሌሎችንም ንዑስ የቋንቋ ቤተሰቦች ያጠቃልላል:: ኢግቦ፣ ፉላ፣ ሾና፣ ዙሉ፣ ባንቱ እና ዮሩባ በዚህ እናት ቋንቋ ውስጥ ከሚገኙት ጥቂቶቹ ናቸው::

### መ) ኮይሳን

የኮይሳን እናት ቋንቋ ስያሜውን ያገኘው ኮይኮይ እና ሳን ከሚባሉ ሁለት ንዑስ የቋንቋ ቤተሰቦች ነው:: ከአራቱ እናት ቋንቋዎች ውስጥ የጥንት እና ትንሽ ተናጋሪ ያለው ቋንቋ ነው:: በናሚቢያ እና ቦትስዋና በስፋት ይነገራል:: የኮይሳን ቋንቋዎች ልዩ የሚያደርጋቸው ተናጋሪዎቹ አየር ወደ ውስጥ በመሣብ በሚፈጥሯቸው ቀጭን ድምፆች ነው::

**ተግባር-2**

1. ቀጥሎ የተቀመጠውን ሰንጠረዥ በደብተራችሁ ካሰፈራችሁ በኂላ እናት እና ንዑስ ቋንቋ በሚለው ስር ባዶ ቦታዎችን ሞልታችሁ የሚነገሩባቸውን ቦታዎች የ √ ምልክት በማድረግ ለዩ::

| እናት ቋንቋ | ንዑስ ቋንቋ | የሚነገሩባቸው ሃገራት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አልጀሪያ | ናሚቢያ | ናይጀሪያ | ኢትዮጵያ |
| | ኩሻዊ | | | | √ |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | ቻሪ ናይል | | | | |
| | ኮማን | | | | |
| ኒጀር ኮንጎ | | | | | |
| ኮይሳን | | | | | |

## 5.2. ጥንታዊ የሰሜን አፍሪካ ስልጣኔዎች

### ሀ) የጥንታዊ ግብፅ ስልጣኔ

**ቁልፍ ቃላት:**

- ሐውልት
- ፈርኦን
- ፒራሚድ

**ተግባር-3**

1. ስለ አባይ ወንዝ የምታውቁትን ለመምህራችሁ ግለጹ፡፡

በአባይ ወንዝ ሸለቆ የሠፈሩ ጥንታዊ ግብፃዊያን ኖም በተባሉ አስተዳደራዊ ግዛቶች የተከፋፈሉ ነበሩ፡፡ በላይኛው (ደቡብ) ግብፅ 22 እና በታችኛው (ሰሜን) ግብፅ ደግሞ 20 ኖሞች ነበሩ፡፡ እያንዳንዱ ኖም የየራሱ ባህል እና ሥነ-ልሣን ነበራቸው፡፡ በ3000 ዓ.ዓ ገደማ ሜነስ የተባለው ንጉስ ሁለቱን የኖም ግዛቶች በማዋሃድ በግብፅ የመጀመሪያውን ስርወ መንግስት መሰረተ፡፡ የግብፅ ስልጣኔም በአባይ ወንዝ ላይ ተጀመረ፡፡



ምስል 5.2. የግብፃዊያን ፒራሚድ

የጥንት ግብፃዊያን ነገስታት ፈርኦን ተብለው ይጠራሉ፡፡ የአማልዕክቶቻቸው ምድራዊ ተወካይ እና መለኮታዊ ነገስታት ተደርገውም ይወሰዳሉ፡፡ የፈርኦኖች የቅርብ ረዳቶች የጦር አዛዦች፣ ግብር ሰብሳቢ መኳንንቶች እና የሃይማኖት ተግባራትን የሚያከናውኑ ቀሳውስት ነበሩ፡፡ አብዛኞቹ ግብፃዊያን አርሶ አደሮች የነበሩ ሲሆን ቀሪው የህብረተሰብ ክፍል ፀሐፊዎችን፣ ነጋዴዎችን፣ የዕደ ጥበብ ባለሙያዎችን እና ባሪያዎችን ያካተተ ነበር፡፡ በአባይ ወንዝ አማካኝነት ግብፃዊያን አርሶ አደሮች ስንዴ፣ ገብስ፣ ሽንኩርት፣ ተልባ እና የተለያዩ አትክልቶችን ያመርቱ ነበር፡፡ የቀንድ ከብት፣ ፍየል እርባታ እና ዓሣ የማስገር ተግባራትንም ያከናውኑ ነበር፡፡

ጥንታዊት ግብፅ 31 በሚሆኑ ስርወ መንግስታት ተገዝታለች፡፡ ከሀገሬው ስርወ መንግስታት ሌላ ግብፅን የወረሩ ኑቢያዎች፣ ሶሪያዊያን፣ ፋርሳዊያ እና ሮማዊያን የመሠረቷቸው ስርወ መንግስታት ግብፅን ገዝተዋል፡፡ በ1640 ዓ.ዓ አካባቢ የሄክሶስ ወረራ ምክንያት የጥንታዊ ግብፅ ስልጣኔ ከሰመ፡፡ ሄክሶሶች ለግብፃዊያን ፈረስን ለውጊያ አገልግሎት ስለመዋሉ እና ከነሐስ የተለያዩ መሣሪያዎች መስራት እንደሚቻል አስተዋውቀዋል፡፡ በመጨረሻም በ1550 ዓ.ዓ ቀደማዊ አህሞስ የተባለ የላይኛው ግብፅ ንጉስ ሄክሶሶችን አሸነፋቸው፡፡

## የግብፅ የሥልጣኔ አበርክቶዎች

| አበርክቶ ዘርፎች | ዝርዝር ተግባራት | ስራዎቹ ያላቸው ጥቅምና መገለጫዎች |
|---|---|---|
| ስነ ፅሑፍ | ሄሮግሊፊክስ | • የሄሮግሊፊክስ ፅሁፎች ይፃፉ የነበረው በፓፒረስ ላይ ነበር። የሂሮግሊፊክስ አፃፃፍ ስልት ጠቀሜታ<br>• ዓመታዊ የሰብል ምርትንና ግብርን ለመመዝገብ<br>• ለሣይንስና ባህል ዕድገት<br>• ስለአስተዳደርና<br>• ዲኘሎማሲያዊ ግንኙነታቸውን ለማጠናከር |
| ሳይንስ | ህክምና<br>መድሐኒት<br>ኬሚካል | • ሆስፒታል ተኝቶ ህክምና ማግኘት<br>• ሰውነታችን 360 አጥንት መኖሩን ደርሰውበታል<br>• ሬሳ ማድረቂያ መሚን ፈልስፈዋል። |
| ሒሳብ | ጂኦሜትሪ እና አርቲሜቲክ | • ግድቦችን እና ቦዮችን ይሰሩ በነበረበት ጊዜ ሂሳባዊ ቀመሮችን መፍጠር ቻሉ። |
| ዕደ ጥበብ | ሸክላ፣ ጌጣጌጦችን እና ቅርፃ ቅርፅ | • ጥበብ በተሞላበት ሁኔታ ጌጣጌጦችን ከብረታብረት እና ከእንጨት ይሰሩ ነበር።<br>• በሀውልቶቻቸውም ላይ አምልኳዊ ቅርፃ ቅርፆችን ይሰሩ ነበር። |
| ሥነ ህንፃ | ፒራሚዶችን፣ ቤተ-ፀሎቶችን፣ ቦዮችን ና ግድቦችን ያካትታል | • ለንጉሶቻቸው መቀበሪያ፣ ስርዓተ ፀሎት ማድረጊያ ይጠቀሙባቸው ነበር። ምሳሌ፡ የካርናክ ህንፃ እና ታላቁ የጊዛ ፒራሚድ |
| የጊዜ መቁጠሪያ | • 12 ወራት ወይም 365 ቀናት መሆኑን ግብፆች ለአለም አስተዋውቀዋል። | |

### ተግባር-4

1. የግብፆች ስልጣኔ ለአፍሪካ ያለውን አበርክቶ መፅሀፍትን በማንበብ ሪፖርት አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ገለፃ አድርጉላቸው።

## ለ) ጥንታዊ ኩሽ/ኑቢያ

**ተግባር-5**

1. ኩሽ ማለት ምን ማለት ነው? በጥንድ ተወያይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁላቸው::



ምስል 5.3. በጥንታዊያን ሜሮይ የተሰራ ሕንፃ

ኩሽ ወይም ኑቢያ የሚለው ስም ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው ከጥንታዊ ግብፅ መዛግብት በ2000 ዓ.ዓ ገደማ ነው:: ግብፃዊያን ኩሽ የሚለውን መጠሪያ የሰጡት ለአሁኑ የሱዳን አካባቢ ነው:: ጥንታዊ ግብፅ ከኩሽ ጋር የጠበቀ የንግድ ግንኙነት ነበራት:: በዚህም የኩሽ ህዝብም የግብፃዊያንን ባህል ወርሰው ነበር:: የግብፃዊያን አማልዕክትም በኩሽ ይመለኩ ነበር:: ጥንታዊ ኩሽ ጠንካራ እና የበለፀገች መንግስት ሆና እስከ 750 ዓ.ዓ ድረስ ቆይታለች:: የመንግስቱ ማዕከል ናፓታ ትባል ነበር:: በ8ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ኩሽ ግብፅን በወረራ ይዛለች:: አምስት የሚሆኑ የኩሽ ነገስታትም በተከታታይ ግብፅን ገዝተዋል:: ጥንታዊ ኩሻዊያን ከ200 በላይ ፒራሚዶችን፣ ሀውልቶችን፣ ቤተ መቅደሶችን፣ ቤተ መንግስቶችን እና የነገስታት መዋኛ ገንዳዎችን ሰርተው ነበር:: በንግድ ዘርፍ ደግሞ ከሮማ እና አረቢያ ጋር ይነግዱ ነበር:: ወደ ውጭ ከሚልኳቸው ሸቀጦች ውስጥ ወርቅ፣ የዝሆን ጥርስ እና ጥቁር እንጨት ይጠቀሳሉ:: የሚያስገቧቸው ደግሞ የወይራ ዘይት፣ እጣን፣ ጣውላ እና የነሀስ ብረት ይገኙበታል::

አሶርያ ግብፅን በወረረች ጊዜ የኩሽ ገዥዎች ከግብፅ ተባረሩ:: ወደ ሀገራቸው ከሸሹ በኋላም አዲስ መንግስት አቋቋሙ:: ይህ አዲስ መንግስት የሜሮይ መንግስት በመባል ይጠራል:: ምክንያቱም የመንግስቱ ማዕከል ሜሮይ የምትባል ከካርቱም

በስተደቡብ የምትገኝ ከተማ ስለሆነች ነው:: የጥንታዊ ግብፅ ሥልጣኔ አሻራ እንደ ኩሽ ሁሉ በሜሮይም ተንፀባርቋል:: ለምሣሌ፡ የሜሮይ ህዝብ ይናገር የነበረው የግብፅን ቋንቋ ሲሆን፣ ስነ-ፁሁፋቸውም ሂሮግሊፊክስ እና አማልዕክቶቻቸውም የግብፅ አማልዕክት ነበሩ:: የጥንታዊ ሜሮይ ሥልጣኔ የተዳከመው ከ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ነው:: ለዚህም መዳከም ውስጣዊ ምክንያት (የእርሻ ምርት መቀነስ፣ የከሰል ምርት ጥራት መቀነስ እና የበረሀማነት መስፋፋት) ነበሩ:: ውጫዊ ምክንያቱ ደግሞ በአክሱም መንግስት መወረሯ ነበር::

### ተግባር-6


1. የኩሽ ህዝብ የሚታወቅባቸውን ዋና ዋና ነገሮች ጥቀሱ::
2. የኩሽ መንግስት የወደቀባቸውን ምክንያቶች ዘርዝሩ::

## ሐ) ካርቴጅ

### ተግባር-7

1. ቱኒዝያ በየትኛው የአፍሪካ ክፍል ትገኛለች? ካርታ ላይ አሳዩ::

ካርቴጅ በጥንት ዘመን ከነበሩት ታላላቅ ከተማ መንግስታት መካከል አንዱ ሲሆን በጣም የበለፀገ የንግድ ማዕከል ነበረው:: የካርቴጅ ከተማ በሰሜን አፍሪካ በሜዲትራኒያን ባህር ዳርቻ ላይ የዛሬዋ ቱኒስ ከተማ አቅራቢያ ይገኝ ነበር:: ካርቴጅ ግዛት የተቆረቆረውው 814 ዓ.ዓ በፎኔሽያዊያን (ፊንቃዊያን) ነበር::




ምስል 5.4. የካርቴጅ መንግስት ግዛት

ካርቴጅ ዙሪያዋን በጠንካራ የግንብ አጥር የተከበበች ከተማ ነበረች። የግንቡ ከፍታ 12 ሜትር ውፍረቱ ደግሞ 9 ሜትር ነበር። በካርቴጅ የነበረው ስርዓተ መንግስት የሚመራበት ህዝባዊ ምክር ቤት ቢኖርም እውነተኛው የፖለቲካ ስልጣን የተያዘው በጥቂት ሃያላን ነበር። የሮማ መንግስት የሲሲሊን ደሴት ለራሱ ለማድረግ በመሻቱ ከካርቴጅ መንግስት ጋር ሶስት ጦርነቶችን ከ264 -146 ባለው ጊዜ አካሂደው በሶስተኛው የፑኒክ ጦርነት ካርቴጅ ተሸንፋ የሮማ መንግስት አካል ሆነች።

**ተግባር-8**

1. መፃህፍትን በማንበብ የካርቴጃዊያን ስልጣኔ አበርክቶዎች ውስጥ አስደናቂ የሆኑትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁላቸው።
2. የፑኒክ ጦርነቶች ያስከተሉትን ውጤት ምን ምን እንደሆኑ ከለያችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ገለፃ አድርጉ።


## 5.3. ጥንታዊ የምዕራብ አፍሪካ መንግስት ምስረታ

### ሀ) ጋና

**ተግባር-9**

1. በአፍሪካ ካርታ ሞሪታንያ እና ማሊን በመሳል አሳዩ።

ጥንታዊ ጋናን የመሠረቷት ሶነንኬ የተባሉ አርሶ አደሮች ነበሩ። ጥንታዊ ጋና ደቡብ ምስራቅ ሞሪታኒያ እና ማሊ አካባቢ ያለውን ቦታ ይይዛል። በስተደቡብ ከነበሩ ወርቅ ከሚያወጡ ህዝቦች፣ በስተሰሜን በረሃው ክልል በግመል የረጅም ርቀት ንግድ እና ንግዱን በሚያካሂዱት ህዝቦች መካከል መገኘቷ ጋና ተጠቃሚ ሆና ነበር። የጋና ገዥዎች ከዋና ከተማቸው ኩምቢ ሳለህ ላይ ሆነው ከወርቅ ንግድ በሚያገኙት ግብር ትልቅ ግዛተ አፄ መስርተው ነበር። በ1000 ዓ.ም በስተምዕራብ እስከ ሴኔጋል ወንዝ ሸለቆና በስተምስራቅ የኒጀር ወንዝ ታላቁ መጠማዘዣ /Great bend of the Niger/ ድረስ ያሉ ክልሎችን ግዛታቸው ያጠቃልል ነበር።




ምስል 5.5. ጥንታዊ ጋና ግዛተ አፄ

የሶነንኬ ነጋዴዎች በምዕራብ አፍሪካ እስልምናን በመቀበል የመጀመሪያዎቹ ነበሩ:: በ11ኛው ክፍለ ዘመን የአልሞራቪዶች መንግስት መመስረትን ተከትሎ የጋና መሪዎችም እስልምናን ተቀበሉ:: ይህ እርምጃ በረሃውን አቋርጠው ከሚመጡ ሙስሊም ነጋዴዎች ጋር ያለውን ግንኙነት እንዲሻሻል አድርጎታል:: ነገር ግን ይህ የጠነከረ የንግድ ግንኙነት ጋና በወርቅ ንግዱ ላይ የነበራት የበላይነት ላይ ባላንጣዎችን አስነስቶባታል:: የማንዲካ ህዝቦች እና ሌሎችም ያካሄዱት ፋክክር፣ የአካባቢው የተፈጥሮ ሀብት መራቆት እንዲሁም የአልሞራቪዶች ወረራ ለጋና መንግስት መውደቅ አስተዋፅኦ አበርክተዋል:: በ1235 ዓ.ም የማንዲካ የጐሣ አለቃ ዋና ከተማዋን ኩምቢሳለህን በመውረሩ የጋና መንግስት ፍፃሜ ሆኗል::

### ተግባር-10


1. ለጋና መንግስት መውደቅ ምክንያቶችን አብራሩ::

## ለ) ማሊ

### ተግባር-11

1. የኒጀር ወንዝ የት ይገኛል? ካርታ በመሳል አሳዩ::

ሶነንኬ እና ማንዲካ ተብለው የሚጠሩ ነገዶች ከጋና አገዛዝ ነፃ በመውጣት የመጀመሪያዎቹ ነበሩ። በ1235 ዓ.ም የማንዲንካው መሪ ሱንዲያታ ኬታ ለም በሆነው የላይኛው ኒጀር ወንዝ ሸለቆ የነበሩ ጉሣዎችን በማዋሃድ በዙሪያው የነበሩ ጎረቤት ህዝቦችንም በአገዛዙ ሥር ስላደረጋቸው ግዛቱ ሊጨምር ችሏል። የማሊ ገዥዎች እስልምናን የተቀበሉት መንግስታቸውን ከመመስረታቸው በፊት ነበር።




ምስል 5.6.ጥንታዊ ማሊ

ማሊ የሌላውን ዓለም ትኩረት የሣበችው ከ1324-1325 ባለው ጊዜ ማንሣ ሙሣ በካይሮ በኩል አድርጐ ወደ መካ ባደረገው ሃይማኖታዊ ጉዞ ምክንያት ነበር። ማንሣ ሙሣ ለግብፅ እና መካ መሪዎች ብዛት ያለው ወርቅ ለግሶ ነበር። በዚህ ዘመን የቲምቡክቱ ከተማ በወርቅ ንግድ እና እስላማዊ ትምህርት ማዕከልነቷ አለምአቀፋዊ ዝና አትርፋ ነበር። ኒያኒ ከምትባለዋ ክፍለ ግዛቷ የተሻለ ዝናብ ያላት በመሆኑ የእርሻ ስራ እየሰሩ ማሽላ፣ ዳጉሳ እና ሩዝ ያመርቱ ነበር። የማንሳ ሙሳ ወታደሮችም በመንግስት እርሻዎች ላይ ባሪያዎችን እያሳረሱ ጥራጥሬ ያስመርቱ ነበር። ሌላው የመንግስት የገቢ ምንጭ ደግሞ የወርቅ ንግድ ነበር። የማሊን ሰፊ ግዛት ለማስተዳደር ጠንካራ እና ሀይለኛ አመራር ያስፈልግ ነበር። የእርስ በርስ የሥልጣን ሽኩቻ በ14ኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ የማንሣዎችን አገዛዝ ሲያዳክመው የማሊ ገባር ግዛቶች ነፃነታቸውን አወጁ። ከኒጀር ወንዝ መጠማዘዣ በስተደቡብ የሚገኙት የሞሲ ጠንካራ መንግስታት የማሊን እምብርት ሲወሩ የቱዓሪግ አርብቶ አደሮች ከበረሃው በመምጣት ቲምቡክቱን ተቆጣጠሩ።

**ተግባር-12**

1. የጥንቷን ማሊ እና የአሁኗን ማሊ በካርታ ላይ አሳዩ::
2. ማሊ የውጭውን አለም ትኩረት የሳበችበት ምክንያቶች ምን ምን ነበሩ::
3. ማሊ እንድትወድቅ ያደረጉ ምክንያቶችን በመለየት አብራሩ::

### ሐ) ሶንጋይ


**ቁልፍ ቃላት:**

☞ ሽሪዓ ☞ ግብር ☞ ገባር

**ተግባር-13**

1. ስለ ናይጀሪያ የምታውቁትን ለመምህራችሁ አብራሩ::

የማሊ መንግስት ሲዳከም ከኒጀር ወንዝ ታላቁ መጠማዘዣ በስተምስራቅ ይኖሩ የነበሩት የሶንጋይ ህዝቦች ናቸው:: ሶንጋይ ትልቅ ግዛተ አፄ የሆነችው በ15ኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ላይ በታላቁ ሱኒ ዓሊ (1464-1492) ዘመን ነበር:: ሱኒ ዓሊ ግዛቱን በወታደራዊ ዘመቻ በማስፋፋት ቱዓረጎችን ከቲምቡክቱ እና የሞሲ ጉሣዎችን ከኒጀር ወንዝ መጠማዘዣ ማባረር ችሏል:: በ1492 ዓ.ም ሱኒ ዓሊ ሲሞት ግዛቱ ማሊን ሙሉ በሙሉ ያጠቃለለ ሆኖ ነበር::




ምስል 5.7.ጥንታዊ ሶንጋይ ግዛተ አፄ

ዓሊን የተካው አስክያ ሙሐመድ ሲሆን እሱም የአስኪያ ስርወ መንግስት መስራች ሆነ:: ጠንካራ ሙስሊም የነበረው አስኪያ ሙሐመድ የሶንጋይን ግዛት በማስፋፋት ጠንካራ አስተዳደራዊ መዋቅር ዘርግቷል:: ግዛቱን ወጥ አድርጎ ለማስተዳደር እና ለማዋሃድ እስልምናን ተጠቅሞበታል:: በሸሪዓ ህግጋት የሚመሩ ሀይማኖታዊ ዳኞች በመላው ግዛቱ በመሾም የግዛቱን ሠላም ማስጠበቅ ችሏል:: በተጨማሪም ሙስሊም ቱዓረጐችን ማስገበር ችሏል:: ቲምቡክቱ እና ጀኒ ከተሞች ላይ ግዙፍ የትምህርት ማዕከላትን መስርቷል::

በ16ኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ የስልጣን ሽኩቻ ማዕከላዊ መንግስቱን አዳከመው:: አዲስ የተመሠረቱ ከሶንጋይ በስተምስራቅ የሚገኙት የቦርኑ፣ የሐውሳ ከተማ መንግስታት እና የቱዓረግ ሱልጣኔት የንግድ ተፎካካሪ መሆን በመቻላቸው ሶንጋይን የበለጠ አዳከማት:: በዚሁ ጊዜ በምዕራብ የአፍሪካ ጠረፍ የአውሮፓዊያን መምጣት የወርቅ ንግዱን አቅጣጫ እንዲቀየር ምክንያት ሆነዋል:: በመጨረሻም በ1591 ዓ.ም የሞሮኮ መንግስት ወረራ ለሶንጋይ መንግስት ፍፃሜ ምክንያት ሆኗል::

**ተግባር-14**

1. ሶንጋይ በአሁኑ ጊዜ የትኞቹን የምዕራብ አፍሪካ አገሮችን ያካትታል?
2. የሸሪዓ ህግን አስክያ መሀመድ ለምን መጠቀም ፈለገ?
3. ሶንጋይ ግዛተ አፄ እንዴት ሊወድቅ ቻለ?

## 5.4. የመካከለኛውና ደቡብ ምስራቅ አፍሪካ መንግስታት

### ሀ) ጥንታዊ የኮንጎ መንግስት

**ተግባር-15**

1. የኮንጎ ወንዝ በየትኛው የአፍሪካ ክፍል ይገኛል? በካርታ ላይ አመልክቱ::

የኮንጎ መንግስት የተመሰረተው በታችኛው የዛየር ወንዝ አካባቢ ነበር:: አካባቢው ምርታማ፣ የተለያዩ የእጅ ስራ ውጤቶች የተስፋፉበት እና የንግድ ስራ የተጠናከረበት አካባቢ ነበር:: ይህም በአካባቢው የሚኖረው ህዝብ እያደገ እንዲሄድና በመስፋፋት ብዙ ቦታዎችን እንዲይዙ አደረገ:: በ1300 አካባቢ የባኮንጎ መንደሮች እየተስፋፉ ወደታችኛው ዛየር ወንዝ አካባቢ ደረሱ::



ምስል 5.8 የባኮንጎ ኅሳዎች መኖሪያ ቤት

የባኮንጎ ኅሳዎች ኑሯቸው በእርሻ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ እምነታቸውም የመሬት መንፈስ የሚባል ነበር:: የዚህ ሀይማኖት ጠባቂ ካህናቶች ደግሞ ማኔካቡንጋ በመባል ይታወቃሉ:: በ1400 ዓ.ም አካባቢ የባኮንጎ መንደሮች በመሰባሰብ ባልጠነከረ አንድነት ምባንዛኮንጎ ላይ ማዕከላቸውን መሰረቱ:: ምባንዛኮንጎ የኮንጎ ግዛተ አፄ የፖለቲካ እና የባህል ማዕከል ነበረች:: የንጉሱ የማዕረግ ስምም ማኒኮንጎ ተባለ:: የኮንጎ መንግስትም በመስፋፋት በ1580 ዓ.ም አካባቢ በምዕራብ አትላንቲክ ውቅያኖስ በስተምስራቅ እስከ ክዋንጎ ወንዝ የተዘረጋ ሰፊ ክልል ነበረው::


### ተግባር-16

1. በተናጠል መፃህፍትን በማንበብ የጥንታዊ ኮንጎ ግዛተ አፄን የገቢ ምንጮችን ከለያችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ሪፖርት አቅርቡላቸው::

### ለ) የታላቋ ዚምባብዌ ጥንታዊ መንግስት

### ተግባር-17

1. በምትኖሩበት አካባቢ የመኖሪያ ቤቶች አጥራቸው በምን እንደተሰራ አብራሩ?




ምስል 5.9. የታላቋ ዚምባብዌ መገኛ

በሾና ቋንቋ ዚምባብዌ ማለት የድንጋይ ግንብ ማለት ነው:: የታላቋ ዚምባብዌ መንግስት ተመስርቶ የነበረው በአሁኗ ዚምባብዌ ግዛት ውስጥ ነበር:: የአካባቢው ህብረተሰብ የድንጋይ ካብ ወይም ግንብ ለከብቶች በረት እና የሀብታሞችን ቤት ለማጠር ይገነባ ነበር:: በጣም ድንቅ የሚባል እስከ አስር ሜትር ከፍታ የነበረው የድንጋይ ግንብ ከ1200-1450 ዓ.ም ባለው ጊዜ ገንብተው ነበር::



ምስል 5.10.የሾና ታላቅ ግንብ

ግንቡም የዚምባብዌ መንግስት የስልጣን እና የክብር መገለጫ ነበር:: ግንቡና ፍርስራሹ ግን የዚምባብዌ ታላቅ የባህል እና የማንነት ቅርስ ሆኖ እስካሁን ድረስ ያገለግላል:: ዚምባብዌ ምውኔ ሙታፓ (Mwene mutapa) በሚባል መንግስት ተተካ:: ምውኔ ደግሞ የገዥው ሰው የንግስና ስሙ/ማዕረጉ ነበር:: ዚምባብዌ ከ11-15ኛው ክፍለ ዘመን የምወኔሞታፓ ስርወ መንግስት ከተማ ሆና ብትቆይም በ1629 ዓ.ም በፖርቱጋል አስተዳደር ስር ወድቃለች::

### ተግባር-18

1. የዚምባብዌ ስልጣኔ አበርክቶዎች በመለየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ገለጻ አቅርቡ፡፡
2. የሾና ጎሳዎች የድንጋይ ቤት መስራታቸው ለአሁኑ ስልጣኔ ያለውን ጠቀሜታ በመገምገም ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ፡፡

## 5.5. የምስራቅ አፍሪካ ጠረፍ ንግድ ማህበረሰቦች

### ሀ) አዛኒያ

### ተግባር-19

1. ስለ ታንጋኒካ የምታውቁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ?

አዛኒያ የተባለው ግዛት አዬ ትክክለኛ መገኛ ቦታውን ለማመልከት አስቸጋሪ ነው፡፡ አዛኒያ የምስራቅ አፍሪካ ጠረፋማ ቦታ ያካትታል ተብሎ ይገመታል፡፡ የአዛኒያ ማህበረሰቦች ከተማን፣ ወደቦችን እና የገበያ ቦታዎችን ይቆጣጠሩ ነበር፡፡ በተጨማሪም ሂማሪያት የተባሉ የደቡብ አረቢያ ህዝብ ጋር በዝሆን ጥርስ የንግድ ልውውጥ ያደርጉ ነበር፡፡ ሂማራይቶች ከብረት የተሰሩ ቁሳቁሶችን እና የጦር መሳሪያዎችን ወደ አዛኒያዊያን ቦታ ይዘው ይመጡ ነበር፡፡

### ተግባር-20

1. የአዛኒያ የጠረፍ ንግድ ማህበረሰቦች የሰሯቸውን ስራዎች በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ ከሰራችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ሪፖርት አቅርቡ፡፡

### ለ) ዘንጅ (ዛንጅ)

### ተግባር-21

1. የምስራቅ አፍሪካ ጠረፍ ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? በካርታ ላይ አመልክቱ፡፡

ዛንጅ ከምስራቅ አፍሪካ ቀንድ እስከ ሞዛምቢክ ያለውን ጠረፍ ያካትታል ተብሎ ይገመታል፡፡ ዘንጅ የገበያ ማዕከሎችን የሚመሩ ነገስታት እንዲሁም ሌሎች ህዝብ

የሚመሩ ነገስታት (ዋክሊሚ) ነበሯት፡፡ የዚህ አካባቢ ህዝብ በአብዛኛው የባንቱ ቋንቋ ተናጋሪ የነበሩ ሲሆን የአረቢያ እና የፐርሺያ ዝርያ ነበራቸው፡፡ የጋማ እና የቀንድ ከብቶችን ያረቡ ነበር፡፡ እምነትን በተመለከተ ማክላንጃሉ የተባለ ባህላዊ እምነት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም የፕላኔት፣ የእንስሳት እና የማዕድናትም አማልክት ነበሯቸው፡፡

## ተግባር-22


1. የዛንጅ ማህበረሰቦችን አጠቃላይ ስራዎች ከለያችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ሪፖርት አቅርቡ፡፡

### ሐ) የስዋሂሊ የከተማ መንግስታት

## ተግባር-23

1. የስዋሂሊ ቋንቋ የት ሀገር የሚነገር ይመስላችኋል? መልሱን ለመምህራችሁ ግለፁ፡፡

የአረብ እና የባንቱ ቅልቅል የሆኑት አፍሪካዊ ህዝቦች ስዋሂሊ ይባላሉ፡፡ ከአሁኑ ሶማሊያ እስከ ሞዛምቢክ ያለውን ቦታ ይዘውት ነበር፡፡ ስዋሂሊ ማለት የጠረፍ ህዝብ ማለት ነው፡፡ በመቀጠልም ስዋሂሊ የምስራቅ አፍሪካ የስራ ቋንቋ ሆነ፡፡ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ የታንዛኒያ ብሄራዊ ቋንቋ ነው፡፡ አረቦች በዚህ አካባቢ መስፈር የጀመሩት ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምሮ ሲሆን ከእስልምና ሀይማኖት መስፋፋት ጋር ተያይዞ የቋንቋው ተናጋሪዎች ቁጥር ሊጨምር ችሏል፡፡




ምስል 5.11. የስዋሂሊ ጠረፋማ ቦታዎች

የስዋሂሊ ከተሞች ከ1200-1500 ድረስ የነበሩት ኪልዋ፣ ላሙ፣ ማሊንዲ፣ ሞምባሳ እና ዛንዚባር ናቸው:: የውጭ ንግድም ከፐርሽያ፣ ቻይና እና ኢንዶኔዥያ ጋር በወርቅ፣ በዝሆን ጥርስ እና በባሪያ ይነግዱ ነበር:: ነገር ግን ከ1500-1600 ባለው ጊዜ አካባቢውን ፖርቱጋሎች በመያዝ የንግድ መስመሩን ብሎም ስልጣኔውን አጠፉት::

## ተግባር-24

1. ጥንድ ጥንድ በመሆን የስዋሂሊ የንግድ ማህበረሰቦች በዘመናቸው የሰሯቸውን ስራዎች ምን ምን እንደሆኑ ከለያችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ገለፃ አድርጉ::
2. የምስራቅ አፍሪካ ጥንታዊ ማህበረሰቦችን አንድ የሚያደርጓቸውን ሁነቶች በመለየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ሪፖርት አቅርቡ::

## ማጠቃለያ

- በአፍሪካ የሚገኙት 55 ሀገሮች የሚናገሯቸው ቋንቋዎች በአራት እናት ቋንቋዎች ይከፈላሉ:: እነሱም አፍሮ እስያዊ፣ ናይሎ ሰሀራዊ፣ ኒጀር ኮንጎ እና ኮይሳን ናቸው:: በተጨማሪም በማዳጋስካር ኦስትሮኔዥያ የሚባል ቋንቋ ይነገራል::
- በአባይ ወንዝ ሸለቆ የተመሰረተው የግብፃዊያን ጥንታዊ ስልጣኔ የአፃፃፍ ስልት፣ የሞተን አካል መድረቂያ መሚ፣ ሆስፒታል ገብቶ መታከምን ወዘተ አበርክቷል::
- በፊንቃዊያን የተመሰረተችው ካርቴጅ ሶስት ጦርነቶችን ከሮማ ጋር ብትዋጋም በሰሜን አፍሪካ እና በሮም የነበራትን ግዛቷን እንድታጣ ሆናለች::
- የኩሽ መንግስት በሰሜን ሱዳን በአባይ ወንዝ ዳርቻ የሚገኝ አካባቢ መሆኑን ብዙዎች ይስማማሉ:: ይህ መንግስት ሲዳከም የሜሮይ መንግስት ተመስርቶ ነበር:: ይህ መንግስት ብረት በማቅለጥ ይታወቅ ነበር::

- በምዕራብ አፍሪካ ተከስተው ከነበሩት ጥንታዊ ገናና መንግስታት መካከል ጥንታዊት ጋና፣ ማሊ እና ሶንጋይ ይጠቀሳሉ፡፡ ጥንታዊ ጋና ዋላታ፣ ኩመቢሳለህ እና ኒያኒ የተባሉ አካባቢዎችን ያማከለ ግዛተ አፄ መስርቶ ነበር፡፡ ጥንታዊ ማሊ ደግሞ ጥንታዊ ጋና የተመሰረተበትን አካባቢ ቲምቡክቱ እና ጋኦን ጨምሮ አስተዳድሮ ነበር፡፡ ጥንታዊ ሶንጋይ የጥንታዊ ማሊ ግዛተ አፄ ይዞት የነበረውን ጀኔ የምትባል ግዛት በመጨመር አስተዳድሮ ነበር፡፡
- የኮንጎ ጥንታዊ ግዛተ አፄ በማእከላዊ አፍሪካ የሚገኝ ነበር፡፡ የአሁኗ ኮንጎ ጋር ፈፅሞ አይገናኝም፡፡
- ታላቋ ዚምባብዌ በመካከለኛው እና በደቡባዊ የአፍሪካ ክፍል ከተመሰረቱት ታላላቅ ጥንታዊ መንግስታት አንዷ ነበረች፡፡ ስልጣኔው የተመሰረተበት ቦታ ከአሁኗ ዚምባበዌ ጋር ይቀራረባል፡፡
- የምስራቅ አፍሪካ ጠረፋማ መንግስታት ከሆኑት አዛኒያ እና ዛንጂ (ከአሁኗ ደቡብ ሶማሊያ እስከ ሞዛምቢክ ያለው ቦታ) ይጠቀሳሉ፡፡ የስዋሂሊ ማህበረሰቦች ደግሞ (ከአሁኗ ደቡብ ሶማሊያ እስከ ሞዛምቢክ ያለውን ጠረፋማ አካባቢ) አካሎ የተመሰረቱ የከተማ መንግስታት ነበሩ፡፡
- የምስራቅ አፍሪካ ጠረፋማ ማህበረሰቦች ወይም ግዛተ አፄ የሐብትና የንግድ እንቅስቃሴ በፖርቱጋሎች መምጣት ሊጠፋ ቻለ፡፡

# የክለሳ ጥያቄዎች

**ክፍል አንድ፡-** ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በትክክል ካነበባችሁ በኋላ ትክክል ከሆኑ እውነት ካልሆኑ ደግሞ ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

1. አማርኛ ቋንቋ ከአፍሮ እስያዊ እናት ቋንቋ ውስጥ ይመደባል፡፡
2. ሱንዲያታ ኬይታ ማሊን ከፍተኛ የምጣኔ ሀብት እድገት ላይ አድርሷት ነበር፡፡
3. የአረብና የባንቱ ቅልቅል የሆኑት አፍሪካዊ ህዝቦች ዘንጅ ይባላሉ፡፡
4. ኑቢያ በአሁኑ ሰዓት ሱዳን ውስጥ የሚገኝ በረሀማ ቦታ ነው፡፡
5. ታላቋን ዚምባብዌ የመሰረቷት ህዝቦች የማንዲካ ህዝቦች ነበሩ፡፡

**ክፍል ሁለት፡-** ቀጥሎ በ ሀ አምድ ለቀረቡት ጥንታዊ ስልጣኔዎች ከ ለ አምድ ከቀረቡት መስራች ጎሳዎች ጋር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ዚምባብዌን የመሰረቱ | ሀ)ሶነንኬ |
| 2. ማሊን የመሰረቱ | ለ) ሾና |
| 3. ካርቴጅን የመሰረቱ | ሐ) ማንዲካ |
| 4. ጋናን የመሰረቱ | መ) ፎኔሽያ |
| 5. ሶንጋይን የመሰረቱ | ሠ)ኢንካ |
| | ረ) ማሊንኬ |

**ክፍል ሶስት፡-** ቀጥሎ የቀረበውን ሰንጠረዥ በደብተራችሁ ካሰፈራችሁ በኋላ በተጠየቀው መሰረት መልሶችን በመስራት ለመምህራችሁ አሳዩ/አሳርሙ፡፡

| ጥንታዊ መንግስታት | የመሰረቷቸው ህዝቦች | የተመሰረቱበት ጊዜ | የወደቁበት ጊዜ እና ምክንያቶች | የጋራ የሚያደርጓቸው ሁነቶች |
|---|---|---|---|---|
| ጋና | | | | |
| ማሊ | | | | |
| ዚምባብዌ | | | | |
| ሶንጋይ | | | | |
| ካርቴጅ | | | | |

# ቁልፍ ቃላት ፍቺ

- **ሐውልት-** ጥንታዊ ሰዎች ንጉሶቻቸው ሲሞቱባቸው ለመዘከሪያ የሚያሰሩት ምስል ሲሆን በአሁኑ ዘመን ታዋቂ ለሆኑ ሰዎች በህይወት እያሉም ምስላቸው ተቀርጾ በአደባባይ ማቆምን ያመለክታል፡፡
- **ፈርኦን** -የጥንታዊ ግብፃዊያን ንጉሶችን ማዕረግ ያመለክታል፡፡
- **ፒራሚድ-** ግብፆች ለፈርኦኖቻቸው መቀበሪያ የሚሰሩት ግንብ ነው፡፡
- **ሸሪዓ-** የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ መሪዎች የሚያስተዳድሩበት፣ የሚዳኙበት ህግ እና መመሪያ ማለት ነው፡፡
- **ግብር-** ጎሳዎች በአሁኑ አሰያየም ዜጎች ለመሪዎቻቸው የሚከፍሉት የአይነት ወይም የገንዘብ ክፍያ ማለት ነው፡፡
- **ገባር-** ሰዎች ለንጉሶች በአይነት እና በጉልበት ግብር የሚከፍሉትን ያመለክታል፡፡

# ምዕራፍ-6 የዓለም ጥንታዊ ስልጣኔዎችና የመካከለኛው ዘመን ታሪክ

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ የሚከተሉትን ይዘቶች መሰረት ተደርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡ ጥንታዊ የዓለም ስልጣኔ የሆኑትን ሜሶፖታሚያ፣ ህንድ፣ ቻይና፣ ግሪክ እና ሮማ ይዟል፡፡ የመካከለኛው ዘመን የአለም ታሪክ ደግሞ የባዛንታይን ግዛተ አፄ እና የኦቶማን ግዛተ አፄን አካቷል፡፡ በተጨማሪም የአለም ዋና ዋና ሃይማኖቶች ተዳስሰውበታል፡፡

**ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት፡**

*ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-*

- ☞ *የጥንታዊውን ዓለም ዋና ዋና ስልጣኔ ቦታዎችን በካርታ ላይ በማመልከት ታብራራላችሁ፡፡*
- ☞ *የባዛንታይን ግዛተ አፄ እና የኦቶማን ግዛተ አፄን አነሳስ እና መስፋፋት ታወዳድራላችሁ፡፡*
- ☞ *የመካከለኛው ዘመን የዓለም ታሪክ ዋና ዋና መገለጫዎችን ትተነትናላችሁ፡፡*
- ☞ *ጥንታዊ የዓለም ስልጣኔ አበርክቶዎችን ትገመግማላችሁ፡፡*

## 6.1. የጥንታዊ ዓለም ስልጣኔዎች

### 6.1.1. የጥንታዊ ሜሶፖታሚያ ስልጣኔ

*ተግባር- 1*

1. ስልጣኔ በወንዝ ዳር/ሸለቆ ለምን ሊጀመር ቻለ?
2. የሀገራችን የጥንት ሰዎች መረጃን እንዴት/በምን መዝግበው ይይዙ ነበር?
3. የንጉሳዊ እና የፍፁማዊ አስተዳደሮች ምን አይነት መገለጫዎች አሏቸው? አብራሩ፡፡


ጥንታዊ ሥልጣኔ በእስያ አህጉር ከተመሰረተባቸው ሥፍራዎች መካከል ቀደምቱ የጥንታዊ ሜሶፖታሚያ ሥልጣኔ ነው:: ሜሶፖታሚያ የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም በሁለት ወንዞች መካከል የሚገኝ ሀገር ማለት ነው:: የሜሶፖታሚያ ሥልጣኔ የተጀመረው በ3500 ዓ.ዓ. ገደማ በኤፍራጥስ እና በጤግሮስ ወንዝ ሸለቆዎች መካከል የግማሽ ጨረቃ ቅርፅ ባለው ለም ቦታ ላይ ነበር:: በጥንታዊት ሜሶፖታሚያ ይኖሩ የነበሩ ከማዕከላዊ እስያ በመምጣት በደቡብ ምስራቅ ሜሶፖታሚያ የሠፈሩት ሱመርያን ተብለው ይጠራሉ:: ከእነርሱ ከፍ ብሎ በሰሜን ምዕራብ እና በማዕከላዊ ሜሶፖታሚያ የሰፈሩት ደግሞ የአካድያ ሕዝቦች ናቸው:: እነዚህ የሱመርያ እና የአካድያ ሕዝብ የሠፈሩበት ቦታ በኋላ ባቢሎንያ በመባል ይታወቃል:: በሰሜን የሜሶፖታሚያ ክፍል የሰፈሩት ሕዝብ ደግሞ አሶራዊያን ይባላሉ::




ምስል 6.1. የሜሶፖታሚያ ስልጣኔ

እነዚህ የጥንታዊ ሜሶፖታሚያ ሕዝቦች በተለያየ ጊዜ በየተራ እየተፈራረቁ የተለያዩ ስልጣኔዎችን መስርተዋል:: እነርሱም የሱመርያ፣ የአካድያ፣ የባቢሎንያ እና የአሶርያ ስልጣኔዎች ነበሩ:: ጥንታዊ ሜሶፖታሚያ አንድ ጠንካራ መንግስት እና ሕዝብ የነበራት ሳትሆን ከላይ የተጠቀሱትን መንግስታት እና ሕዝብ የያዘች ነበረች:: እነዚህ የሜሶፖታሚያ ስልጣኔዎች አስተዳደራዊ ተግባራቸው ሲቃኝ ንጉሳዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ፍፁማዊ ነበር::

የመንግስቱ የገቢ ምንጭ በእርሻ እና በንግድ የተመሰረተ ነበር:: ህዝቡም አርሶ አደር፣ ቀሳውስት፣ ወታደር፣ የእደጥበብ ባለሙያ፣ ነጋዴ፣ ተቀጣሪዎች እና ባሪያዎችን የያዘ ነበር:: ነሀስን ለጦር መሳሪያ በማዋል በታሪክ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ነበሩ:: ማረሻን ለመጀመሪያ ጊዜ በመስራትና በመጠቀም፣ በነፋስ የሚንቀሳቀሱ ጀልባዎችን፣ በስነ-ከዋክብት ጥናት፣ ሒሳብን (ለአስተዳደር ሥራ በስፋት በመጠቀም፣ አንድ ስዓት ስድሳ ደቂቃ እንደሆነ፣ አንድ ክብ ደግሞ 360 ዲግሪ መሆኑን) እና ኩኒፎርም የተባለ የአፃፃፍ ስልትን ለአለም አበርክተዋል::



ምስል 6.2. ኩኒፎርም አፃፃፍ

ኩኒፎርም የላቲን ቃል ሲሆን ትርጉሙም ሽብልቅ ማለት ነው:: ስለዚህ የኩኒፎርም አፃፃፍ ስልት እንደ ሽብልቅ ቅርፅ ያላቸው የተለያዩ ምስሎችና ምልክቶችን ይጠቀም ነበር ማለት ነው:: የሚፃፈውም በፀሐይ በደረቀ የሸክላ ጡብ ላይ ነበር::

### ተግባር-2


1. ስለ ሜሶፖታሚያ ስልጣኔ በመማራችሁ ያገኛችሁትን ጥቅም አብራሩ::
2. የጥንት ሜሶፖታሚያ ስልጣኔ ተመስርቶ የነበረው በዛሬው የት አካባቢ ነበር? በካርታ ላይ አመልክቱ::

## 6.1.2. የህንድ ጥንታዊ ስልጣኔ

### ተግባር-3

1. የአሁኗን ህንድ መገኛ በካርታ ላይ አሳዩ::

በ2500 ዓ.ዓ የህንድ ሥልጣኔ በኢንደስና ጋንጀስ ወንዝ ሸለቆዎች ተጀመረ። የጥንታዊ ህንድ ሥልጣኔ መስራች የድራቪድያን ሕዝቦች ነበሩ። የህንድን ሥልጣኔ ጥንታዊነት የሚያመለክቱ የሃራፓ እና ሞሔንጆ-ዳሮ የተባሉ ከተሞች ፍርስራሽ፣ የጡብ ቤቶች፣ ከሸክላ የተሠሩ ማሰሮዎች እና የተለያዩ የቤት ዕቃዎች አርኪኦሎጂስቶች ባደረጉት ቁፋሮ ተገኝተዋል። የእነዚህ ከተሞች ሥልጣኔ በ1500 ዓ.ዓ. አከተመ። ምክንያቱ ደግሞ የአየር ንብረት ለውጥ አደጋ በማስከተሉ እና ከጥንታዊ የኢንደስ ወንዝ ሸለቆ ሥልጣኔ መውደቅ በኋላ የአርያን ነገዶች ሰሜን ህንድን ወረው በመያዛቸው የድራቪድያን ሕዝቦች ቦታውን ለቀው ወደ ደቡብ ህንድ ተሰደዱ። አርያኖች ባደረጉት ተከታታይ ወረራም በህንድ ትንንሽ መንግስታትን አቋቋሙ።




ምስል 6.3. የህንድ ስልጣኔ

የጥንታዊ ህንድ ሕዝብ በዘርና በቆዳ ቀለም ልዩነት (Caste system) የተከፋፈለ ነበር።

**ብርሐማን አንደኛ መደብ**
- የበላይ ገዥዎች የሆኑ ቀሳውስትና መኳንንቱን ያካትታል።
- ነጭ የቆዳ ቀለም አላቸው።
- ክብር እና ዝና ያላች ናቸው።

**ሻትሪያ ሁለተኛ መደብ**
- የወታደሩን ክፍል ይይዛል።
- ቀይ የቆዳ ቀለም አላቸው።
- ወታደራዊ አገልግሎት ይሰጣሉ።

**ቫይሽያ ሶስተኛ መደብ**
- ገበሬዎች፣ የዕደ ጥበብ ባለ ሙያዎችን ይይዛል።
- ቢጫ የቆዳ ቀለም አላቸው።
- ግብር ይከፍላሉ።

**ሱድራ አራተኛ መደብ**
- ባሮች እና ቀጥረኞች
- ጥቁር የቆዳ ቀለም ያላቸው የታችኛው የህንድ ዜጎች ናቸው።
- ምንም አይነት መብት የላቸውም

በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ገደማ የሰሜን ምዕራብ ህንድ ክፍል በታላቁ እስክንድር ተወሮ በግሪኮች አገዛዝ ስር ወደቀ። ከጊዜ በኋላም ህንድን ከግሪኮች አገዛዝ ነፃ ለማውጣት የነፃነት እንቅስቃሴ ተጀመረ። የዚህ የነፃነት እንቅስቃሴ አደራጅ እና መሪ ቻንድራጉፕታ መውሪያ (324-297) ይባላል። ይህ መሪ ግሪኮችን በማሸነፍ ህንድን ነፃ አውጥቷል። ሰሜን ህንድን አንድ አድርጎ በመግዛትም የመጀመሪያውን የህንድ ስርወ መንግስት (321 ዓ.ዓ. - 185 ዓ.ም) መሥርቷል።

የጥንታዊ ህንድ ሥልጣኔ አበርክቶዎች በርካታ ናቸው። በተለይም ልብስን የማቅለም ዘዴ፣ የቆዳ ሥራ፣ የሣሙና፣ መስታዎት ማምረት፣ ብረት ማቅለጥ፣ በሸክላ ሥራ፣ በስነ ሕንፃ እና ቅርፃ ቅርፅ ለየት ያሉ ነበሩ። በስነዕሁፉ ረገድም

በሳንስክሪት ቋንቋ የተፃፉ የተለያዩ ፅሁፎችን ትተው አልፈዋል:: በህክምና በኩልም ከተክሎች መድሃኒት መቀመም የተለመደ ተግባራቸው ነበር:: በሂሳብ ውስጥ ዜሮ የተገኘው በህንዳውያን ነው:: አልጀብራን እና የዴሲማል አጠቃቀምን ለዓለም ያስተዋወቁ ህንዶች ናቸው::

### ተግባር-4

1. የጥንታዊ ህንድ ስልጣኔ አበርክቶዎችን በተመለከተ በክፍል ውስጥ ተወያዩበት::
2. ወደ ቤተ መፃህፍት በመሄድ የህንድ ስልጣኔ ያከተመበትን ምክንያቶች ጥንድ ጥንድ በመሆን ከለያችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ገለፃ አድርጉ::

## 6.1.3. የጥንታዊ ቻይና ስልጣኔ

### ተግባር-5

1. ስለ ሐረር ጀጎል ግንብ የምታውቁትን ለመምህራችሁ ግለፁ::

የጥንታዊ ቻይና ሥልጣኔ የተጀመረው በየሎው ወንዝ እና በያንግቲዝ ወንዝ ሸለቆዎች ነበር:: በጥንታዊ ቻይና ብዙ ቁጥር ያላቸው ስርወ መንግስታት በስልጣን ላይ ተፈራርቀዋል:: የመጀመሪያው ስርወ መንግስት የሻንግ ስርወ መንግስት(1600-1050) ነበር:: የዚህ ስርወ መንግስት ማዕከል ህዋንግሆ ሸለቆ ነበር:: በሻንግ ስርወ መንግስት ከተሰሩ ስራዎች ተጠቃሾቹ ከነሀስ የተሰሩ ውሀ መያዣዎች፣ በፈረስ የሚጎተቱ የጦር ሰረገላዎች እና የአጻጻፍ ጥበብ ናቸው:: የሻንግን ስርወ መንግስት በማስወገድ ሥልጣን የያዘው የቹ ስርወ መንግስት (1050-256) ነበር:: ይህ ስርወ መንግስት የቻይናን ግዛት ከማስፋፋቱም በተጨማሪ የመገበያያ ገንዘብ፣ ከብረት የተሰሩ መሣሪያዎች፣ በፅሁፍ የሰፈሩ ሕጎች፣ ስነ-ፅሁፍ እና ፍልስፍና የዳበረበት ጊዜ ነበር:: ከ476-221 በቻይና እርስ በርስ ጦርነት ተካሄዶ ነበር:: ይህም በቻይና ታሪክ ውስጥ “የመንግስታት ውጊያ ዘመን“ በመባል ይታወቃል:: የተበታተነችው ቻይና መልሣ የተዋሃደችው በችን ስርወ መንግስት (221-206) ዘመን ነበር:: የዚህ መንግስት መስራች ንጉስ ሽህ ሕዋንግ-ቲ (Shih Huang- ti 256-206) ይባላል::



ምስል 6.4 ታላቁ የቻይና ግንብ

በችን ስርወ መንግስት በርካታ ጠቃሚ ሥራዎች ተሰርተው ነበር፡፡ 21,196 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ታላቁ የቻይና ግንብ የተጀመረው በዚህ ጊዜ ነበር፡፡ የተሰራበትም ምክንያት ከእስያ ከሚመጡ ወራሪዎች ቻይናን ከጥቃት ለመከላከል ታስቦ እንደነበር ይነገራል፡፡ በችን ሥርወ መንግስት ዘመን ስነ ፅሑፍ አድጓል፡፡ በመላ ቻይና ተመሳሳይ ህግ ለማስፈንና ማዕከላዊ መንግስትን ለማጠናከር ጥረት ተደርጓል፡፡ የሐን ስርወ መንግስት(206 ዓ.ዓ- 220 ዓ.ም) ለቻይና ማደግ እና መበልፀግ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ ስነ-ጥበብ እና ሳይንስ በከፍተኛ ደረጃ አድገው ነበር፡፡ የኮንፊሽየስ ፍልስፍናም በጣም የተስፋፋው በዚህ ወቅት ነበር፡፡ የጥንታዊ ቻይና ሕዝቦች በንግድ የታወቁ ነበሩ፡፡ ከኮንስታንቲኖፕል፣ ከህንድ እና ከአክሱም መንግስታት ጋርም ይነግዱ ነበር፡፡

ቻይናዊያን በተለይም በሐር ልብሳቸው እና በማራኪ የሸክላ ሥራቸው በጣም የታወቁ ነበሩ፡፡ ጥንታዊ ቻይና የራሷ የሆነ የአፃፃፍ ስልት ነበራት፡፡ ይህም ሎጎግራፊ በመባል ይጠራል፡፡ የተለያዩ ምስሎችን እና ቁሳቁሶችን በመጠቀም ቃላትን ፈጥረው በወረቀት ላይ ይፅፉ ነበር፡፡ ከጥንታዊ ቻይና ሥልጣኔ አበርክቶዎች መካከል የወረቀት ሥራ ጥበብ፣ ኮምፓስ፣ ባሩድ፣ ርዕደ መሬትን መለኪያ መሳሪያ፣ የቀን መቁጠሪያ እና ማዳበሪያ የመስራት ጥበብ፣ ስነ-ነጥበብ እና ቅርፃ ቅርፅ ይጠቀሳሉ፡፡

### ተግባር-6

1. የጥንታዊ ቻይናን ካርታ ከሰራችሁ በኋላ የህዋንግሆ እና የያንግቲዝ ወንዞችን አሳዩ::
2. የጥንታዊ ቻይና ስልጣኔ የምጣኔ ሀብት መሰረቶቹን በግላችሁ ለዩ:: በመቀጠል ከጎናችሁ ካለው/ችው ጓደኛችሁ ጋር በጋራ ስሩ:: ሀሳባችሁን በፅሁፍ ለጓደኞቻችሁ ግለፁ::
3. የጥንታዊ ቻይና የስልጣኔ በወቅቱ ከነበሩት ሌሎች የአለም ስልጣኔዎች ጋር የነበረውን ግንኙነት እንዴት ትገመግሙታላችሁ? በምን ይለያል?

## 6.1.4. የጥንታዊት ግሪክ ስልጣኔ


**ቁልፍ ቃላት:**

| | |
|---|---|
| ☞ ደሴት | ☞ አማልክት |

### ተግባር-7

1. ድራማ የሚለው ቃል ከየት መጣ? ምን ማለት ነው? መልሳችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ::

ከ3000 -1400 ዓ.ዓ በምስራቅ ሜዲትራኒያን ከግሪክ አጠገብ በምትገኝ ክሬት በተባለች ደሴት ከፍተኛ ስልጣኔ ተፈጠረ:: ይህ ስልጣኔ ወደ ኤጅያን ባህር ደሴቶች ተዛመተ:: ይህም የክሬት ስልጣኔ ወይም የሚኖን ስልጣኔ በመባል ይጠራል:: ስሙ የተወሰደው በአፈ ታሪክ የክሬት ሕዝብ ንጉስ ከነበረው ሜኖስ ነው:: በክሬት ለእርሻ አገልግሎት የሚውል በቂ መሬት ባይኖርም ለመርከብ እንቅስቃሴ የተመቻቹ ወደቦች በመኖራቸው ነዋሪዎችን በንግድ ሥራ ላይ እንዲሰማሩ አደረጋቸው::






ምስል 6.5. የግሪክ ስልጣኔ

የአቴና የከተማ መንግሥት የተቋቋመው በማዕከላዊ ምሥራቅ ግሪክ በአቲካ ባህረ ሰላጤ አካባቢ ነበር። ከ750 ዓ.ዓ በኋላ በአቴና አብዛኛው ሕዝብ በዕደጥበብ፣ በዓሣ ማስገር እና በንግድ ላይ የተሰማራ ነበር። የአቴና መንግሥት ፖለቲካዊ አደረጃጀት በዲሞክራሲ ስርዓት ላይ የተመሠረተ እና በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የቀጥታ ዲሞክራሲን በተግባር ላይ ያዋለ የከተማ መንግስት ነበር። የአቴና ሕዝብ በቀጥታ በመንግስት አስተዳደር በመሣተፍ ሕግ እና ፖሊሲ ያወጣሉ።

ክሊስቲነስ (570-508) የተለያዩ ህጎችን በማውጣት ይታወቅ ነበር። ለምሳሌ የንግግር ነፃነት፣ በሕግ ፊት እኩልነት፣ ወዘተ በመደንገግ የአቴናን ሕዝብ ዲሞክራሲ አጎናፀፋቸው። በየዓመቱ በዕጣ የሚመረጡ 500 አባላት ያሉት ሸንጎም አቋቁሞ ነበር። በአቴና መንግስት ለውጥ ያመጣው ሌላው የአቴና መሪ ፔሪክለስ (461-429) ሲሆን በእሱ የአስተዳደር ዘመን ማንኛውም ሕዝብ በመንግስት ጉዳዮች በስፋት እንዲሳተፍ ተደርጓል። በፔሪክለስ ዘመን ዲሞክራሲ በአቴና ከፍተኛ ዕድገት አሳይቷል።

የስፓርታ የከተማ መንግሥት የተቋቋመው በደቡብ ግሪክ በፔሎፓኔዥያን ባህረ ሰላጤ አጠገብ ነበር። የስፓርታ ሕዝብ የኢኮኖሚ መሠረት እርሻ ነበር። የስፓርታ ሕዝብ በሦስት ዋና ዋና መደቦች የተከፈለ ነበር። እነሱም የመሬት ባላባት የሆኑት ስፓርታውያን፣ ነፃ ወገን የሆኑት ፔሪወኪና፣ የእርሻ ሥራ የሚያከናውኑ ባሪያዎች (ሄሎት) ናቸው። በስፓርታ የመሬት ባላባቶች አምባገነናዊ መንግስት መስርተው ነበር። በመሆኑም በስፓርታ ዲሞክራሲ ቦታ አልነበረውም። በስፓርታ የማንኛውም ሰው ልጅ ሰባት ዓመት ሲሞላው ጀምሮ የውትድርና ትምህርት የመከታተል ግዴታ አለበት። የስፓርታ ሕዝብ በጦረኝነታቸው የታወቁ ነበሩ። አብዛኛውን ጊዜያቸውን ለወታደራዊ ተግባር ይጠቀሙ ነበር።



ምስል 6.6. የጥንታዊ ግሪክ ስነ ህንፃ

በአቴናዊያን እና በፐርሽያዊያን መካከል በ490 ዓ.ዓ ማራቶን በተባለው ቦታ በተደረገው ጦርነት አቴናውያን ግዙፉን የፐርሽያዊያንን ጦር ቢያሸንፉም ውድመትን አድርሶባቸዋል፡፡ በስፓርታ እና አቴና መካከል በተፈጠረው የእርስ በርስ ጦርነት (431- 404) ስፓርታ አሸናፊ ነበረች፡፡ በተጨማሪ በ338 ዓ.ዓ ግሪክ በመቄዶንያ ንጉስ ፊሊፕ ተወረረች፡፡ በኋላም ግሪክ ነፃነቷንም አጣች፡፡

**ተግባር-8**

1. የግሪክ ነገስታት የአቴናን የከተማ መንግስት ለመገንባት የወሰዱትን እርምጃዎች በመገምገም ተገቢነታቸውን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ፡፡
2. በአቴና እና በስፓርታ መካከል ስለተፈጠረው ጦርነት ምን አስተያየት አላችሁ? ሀገር ለመገንባት ተፅዕኖውን እንዴት ትገልፁታላችሁ? ለሀገራችን የሚጠቅም ብላችሁ የምትወስዱት ተሞክሮ ምን አለ?
3. በስፓርታ የከተማ መንግስት ስርዓት አንድ ልጅ ሰባት አመት ሲሞላው ወታደራዊ ግዴታ እንዲፈፅም መገደዱን ትደግፋላችሁ? በአሁኑ እድሜያችሁ ወታደር ሁኑ ብትባሉ ምን ይሰማችኋል?

## 6.1.5. የሮማ ሥልጣኔ

**ቁልፍ ቃል**

☞ ግዛተ አፄ


**ተግባር-9**

1. እኛ ኢትዮጵያዊያን በአድዋ ጦርነት ላይ ያሸነፍናት አውሮፓዊት ሀገር ማን ትባላለች?

በ1500 ዓ.ዓ ገደማ የኢንዶ-አውሮፓ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ላቲን የሚባሉ ነገዶች የአልፕስን ተራራ ወረሩ፡፡ ላቲኖች በ753 ዓ.ዓ ከታይበር ወንዝ ከፍ ብሎ በሚገኝ ኮረብታማ ስፍራ ላይ የሮማን ከተማ እና መንግስት አቋቋሙ፡፡ እንደ ላቲኖች አፈ-ታሪክ ከሆነ ጥንታዊ ሮም የተመሠረተችው ሮሚለስ እና ሬሙስ በተባሉ ሁለት መንትያ ወንድማማቾች ነበር፡፡ ጥንታዊ ሮማውያን ኑሯቸው የተመሠረተው በእርሻ ላይ ነበር፡፡ አማልክትን ወይም ጣኦቶችን ያመልኩ ነበር፡፡ ለምሣሌ ማርስ

የጦርነት አምላክ፣ ኔፕቱን የባህር አምላክ፣ ቬኑስ የፍቅር አምላክ፣ ወዘተ ናቸው በማለት ያምኑ ነበር፡፡ በ750 ዓ.ዓ ሮም ኢትሩስካን በተባሉ ሕዝብ እጅ ወደቀች፡፡ ለቀጣይ 250 ዓመታት ኢትሩስካኖች ሮምን ገዝተዋል፡፡ ኢትሩስካኖች በሥልጣኔ ረገድ ከሮማውያን የተሻሉ ነበሩ፡፡

የሮማ ሕዝብ በሦስት መደቦች የተከፈሉ ነበሩ፡፡ በሮማ ሪፐብሊክ ውስጥ ስልጣን የያዙትና የመሬት ከበርቴ የነበሩት ፓትሪሻንስ ናቸው፡፡ የሁለተኛው መደብ የኢኩቲስ ሀብት ግን የተመሠረተው በንግድ ላይ ነበር፡፡ ሦስተኛው መደብ ፕሌቢያንስ ደግሞ አነስተኛ ገበሬዎች፣ የዕደጥበብ ባለሙያዎች እና የጉልበት ሰራተኞች ነበሩ፡፡ ባሪያዎች በሮማ የግዛት መስፋፋት ዘመን በጦርነት የተማረኩ ሲሆኑ በፓትሪሻኖች ሠፋፊ መሬት ላይ ጭሰኛ እና የቤት ሠራተኛ ሆነው አገልግለዋል፡፡



ምስል 6.7. ሮማዊያን ከግሪኮች እና ከፊንቂያዊያን ያገኙትን ልምድ በመጠቀም የፈጠሩት የላቲን ቋንቋ ፊደላት

የሮማ መንግሥት ተስፋፊ ወታደራዊ መንግስት ሊሆን የቻለበት ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ጠንካራ ሠራዊት ስለገነባ ነበር፡፡ ይህም ማለት ሁሉም ሮማውያን ወታደራዊ አገልግሎት መስጠት ግዴታቸው ስለነበር፡፡ በተጨማሪም በሮማ ጦር ሠራዊት ውስጥ ጠንካራ ወታደራዊ ስነ ስርአት በመኖሩ ነበር፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ለውጊያ ስምሪት ወታደሩን በአፋጣኝ ሁኔታ ከቦታ ወደ ቦታ የማንቀሳቀስ ዘዴው ብቁ መሆኑ እና በጦርነት ያሸነፈውን ሕዝብ በአግባቡና በጥሩ ሁኔታ ማስተዳደርና መምራት መቻሉ ነበር፡፡ በሮማ ሪፐብሊክ የመንግስቱ አስተዳደር ዲሞክራሲያዊ ባህርይ ነበረው፡፡ በምርጫ የተቋቋሙ ሸንጎዎች ነበሩት፡፡ ሆኖም ግን ያለምርጫ

የተቋቋመው የበላይ ሸንጎ ሴኔት ሲባል ባለስልጣናቱ ኮንሱሎች ይባሉ ነበር፡፡

በ476 ዓ.ም ጀርመኖች (ጎትስ እና ቪጎትስ) የሮማን መንግስት በጦርነት ሙሉ በሙሉ እንዲወድቅ አደረጉ፡፡ የሮማ ግዛተ አፄ ራስን ከጠላት ለመከላከል ሲባል ለሁለት ተከፍሎ ነበር፡፡ እነሱም የምዕራቡ ሮማ ግዛት-አፄ በሮማው ንጉስ የሚገዛና ማዕከላዊ መንግስቱ መቀመጫ ሮም እና የምስራቁ ሮማ መንግስት (የባይዛንታይን ግዛተ-አፄ) መቀመጫውን ኮንስታንቲኖፕል አደረገ፡፡ የባይዛንታይን ግዛተ አፄ ማዕከል የተቆረቆረችው በንጉስ ኮንስታንቲን በ330 ዓ.ም ነበር፡፡ የምዕራቡ ግዛት የላቲን ቋንቋን ሲጠቀም የምስራቁ ግን የግሪክ ቋንቋን ይጠቀሙ ነበር፡፡ የምስራቁ የሮማ መንግስት ለቀጣዮቹ 1000 ዓመታት በመቆየት በመጨረሻም በ1453 ኦቶማን ቱርኮች ኮንስታንቲኖፕልን ሲይዙ የባይዛንታይን ግዛተ አፄ ፍፃሜው ሆነ፡፡

**ተግባር-10**

1. በጥንታዊ ግሪክ የታዩ ስልጣኔዎች ከሮማ ስልጣኔዎች ጋር ግንኙነት አላቸው ብላችሁ ታስባላችሁ? ከሁለቱ የትኛዎቹን ታደንቃላችሁ? ለምን? በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ ተከራከሩ፡፡
2. በዘመኑ የነበረው የሮማ መንግስት በ476 ዓ.ዓ የውጭ ጥቃትን ለመቅረፍ የወሰደውን እርምጃ በመለየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ሪፖርት አቅርቡ፡፡

## 6.2. የመካከለኛው ዘመን የዓለም ታሪክ

### 6.2.1. የጨለማው ዘመን ታሪክ በአውሮፓ

**ቁልፍ ቃላት፦**

- ነገድ
- ጎሳ

**ተግባር-11**

1. በአካባቢያችሁ ቀደም ብሎ የነበረ ቤት ወይም ግንብ ፈርሶ አይታችኋል? ለምን ሊፈርስ ቻለ? መልሱን ለጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡

የጨለማው ዘመን በአውሮፓ ታሪክ ውስጥ የመካከለኛው ዘመን የመጀመሪያው

ክፍል ሲሆን ጥንታዊው የግሪክ እና የሮማ ስልጣኔ የወደቀበት፣ ከተሞች የተዳከሙበት እና የሕዝብ ቁጥር የቀነሰበት ዘመን ነበር። ይህ ሊሆን የቻለው በውስጣዊ እና ውጫዊ ችግሮች በ476 ዓ.ም ነበር። በግዛተ-አፄው ውስጥ የተፈጠሩ ክፍፍሎች፣ ስልጣንን ያለአግባብ መጠቀም እና የውጭ ወረራ ነበሩ። የጨለማው ዘመን የተወሰኑ ብሩህ ገፅታዎች ነበሩት። ከነዚህም ውስጥ ጳጳሳት እና መነኮሳት ጥንታዊ ፅሁፎችን አጥንተው ለትውልድ ማስተላለፋቸው፣ የአብያተ ክርስቲያናት እና ቤተ-መንግስታት ግንባታ መቀጠሉ፣ ህግ እና ስርዓትን የሚያስከብሩ ወታደሮች(Knights) መኖር ነበሩ።

የጀርመን ወራሪዎች የሮማን ግዛት ከተቆጣጠሩ በኋላ ህጎችን እና ደንቦችን አወጡ። ግብርም ማስከፈል ጀመሩ። መሬትን መግዛት እና መሸጥ የተለመደ ሆነ። በዚያ ዘመን ይህ አይነቱ የግል የመሬት ይዞታ ሰፋፊ መሬቶችን ቀስ በቀስ በጥቂት ግለሠቦች እጅ እንዲገባ አደረገ። በዚህ በጨለማው ዘመን ራሳቸውን ከጠላት ለመከላከል ያልቻሉ የሮማ ግዛት ህዝብ ሁሉ መሬቶቻቸውን ለመሬት ከበርቴዎች በመስጠት እና ግብር በመገበር ፊውዳሎች ከጠላቶቻቸው እንዲከላከሉላቸው ያደርጉ ነበር። ይህም ድርጊት ጥቂቶች የመሬት ባለባቶች እንዲበለፅጉ እና ብዙው ህዝብ ደግሞ እንዲደኸይ እና ወደ ጭሰኛነት እንዲለወጥ አድርጓል። በአጠቃላይ ሲታይ ፊውዳሊዝም በአውሮፓ ሲከሰት የሚከተሉት ሁለት ዋና ዋና ክስተቶች ነበሩት። እነሱም ሰፋፊ የእርሻ ቦታዎች መመሥረት፣ ጥቂት የመሬት ባላባቶች መፈጠር እና የራሳቸው የሆነ መሬት የሌላቸው ጭሰኞች መፈጠር ናቸው።

*ተግባር-12*

1. ከመካከለኛው ዘመን ታሪክ ምን አዲስ እና ለእናንተ ለቀጣይ እድገታችሁ መሰረት የሆነ ነገር አገኛችሁ? ገምግሙ።

### 6.2.2. የባይዛንታይን ግዛተ አፄ

*ተግባር-13*

1. ግዛተ አፄ ምን ማለት ነው?

ባይዛንታይን የሚለው ስያሜ የተወሰደው ባይዛንቲየም ከምትባል የጥንታዊ ግሪክ ከተማ ነው። ኮንስታንትኖፕል ተብላ የተሰየመችው በመጀመሪያው የሮማው ንጉስ ኮንስታንትን ስም በ330 ዓ.ም ነው። የምዕራቡ ሮማ ግዛት አፄ በ476 ዓ.ም

ሲወድቅ የምስራቁ ሮማ ግዛት ወይም የባይዛንታይን ግዛት አፄ ግን የውጭ ወረራን ተቋቁሞ እስከ 1453 ዓ.ም ድረስ ቆይቷል።




ምስል 6.8. የባይዛንታይን ግዛተ አፄ

የምዕራቡ ሮማ መንግስት ሲወድቅ የባይዛንታይን ግዛት አፄ ለሺህ ዓመታት የቆየበት ምክንያት በመሬት አቀማመጡ (ይሄውም የባይዛንታይን ግዛት አቀማመጥ ለጠላት ወረራ አመች ባለመሆኑ)፣ የበለፀገ ሐብት ስለነበረው (ወራሪዎችን እና ወታደሮችን በገንዘቡ መመለስ እና መግዛት በመቻሉ) እና ጠንካራ የጦር ሠራዊት ማደራጀት በመቻሉ ነበሩ።

በባይዛንታይን ግዛተ አፄ ከነገሱት ነገስታት መካከል ጠንካራው ንጉስ ጁስቲንያን (527-565) ይባላል። በእሱ ዘመነ መንግስት የባይዛንታይን ግዛት በምዕራብ በኩል ተስፋፍቶ ነበር። ንጉስ ጁስቲንያን የቀድሞውን የምዕራቡን ሮማ ግዛት ከወራሪዎች እጅ ለማስመለስ ትልቅ ምኞት ነበረው። የግዛት ማስፋፋት ምኞቱን ለማሳካት ሰሜን አፍሪካን፣ ደቡብ ስፔንን እና ጣልያንን ከጀርመኖች በመውረር ይዞ ነበር። ንጉስ ጁስቲንያን ለዓለማችን ሥልጣኔ የበኩሉን አስተዋፅኦ አድርጓል። ይሄውም ቀደምት ሕጎችን በማሰባሰብ እና በመከለስ አዲስ በስሙ የሚጠራ ሕግ አውጥቷል። ይህም የሕግ ስብሰብ የጁስቲንያን ህግ በመባል ይታወቃል። የጁስቲንያን ህግ በኋላ በመላው አውሮፓ ጥቅም ላይ ውሎ ነበር። በተጨማሪም በኮንስታንቲኖፕል ከተማ ውስጥ ቅድስት ሶፊያ የተባለ ትልቅ ቤተ-ክርስቲያን ገንብቷል። ሌላው የሐር

ማምረቻ መሣሪያ ከቻይና በምስጢር አስመጥቶ በግዛቱ ማስመረት ችሎ ነበር፡፡

ከጁስቲንያን ዘመነ መንግስት በኋላ እስከ 15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የባይዛንታይን ግዛት በተለያዩ የውጭ ወራሪዎች ተከታታይ ጥቃት ደርሶበት ነበር፡፡ እነዚህ የውጭ ወራሪዎች ሎምባርዶች፣ ስላቮች እና ቱርኮች ነበሩ፡፡ በተለይም የቱርኮች ወረራ ለባይዛንታያን ግዛት አፄ መድከም አንዱ ምክንያት ነበር፡፡ ሎምባርዶች ጣልያንን ሲይዙ፣ ስላቮች የባልካንን ምድር ወረሩ፣ ቱርኮች ደግሞ ሰሜን አፍሪካን እና ሶርያን በመውረር ተቆጣጠሩ፡፡ በእነዚህ የውጭ ወራሪዎች የተነሳ የባይዛንታይን አፄ ግዛቱን ከማጣቱም በላይ በ1453 ዓ.ም በኦቶማን ቱርኮች ተገረሰሰ፡፡

**ተግባር-14**

1. የባይዛንታይን ንጉስ ጁስቲንያን ለዓለማችን ያበረከተውን አስተዋፅኦ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡
2. ለባይዛንታይን ግዛት አፄ መውደቅ ምክንያቶች የሆኑትን ምክንያቶችን በግላችሁ ከሰራችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ፡፡

### 6.2.3. የኦቶማን ግዛተ አፄ

**ቁልፍ ቃል:**

☞ ጃኒሳሪ

**ተግባር-15**

1. በ16ኛው ክፍለ ዘመን በአዳሎች እና በደጋው ክርስቲናዊ ግዛት መካከል በተደረገው ጦርነት የተሳተፉ የውጭ ሀይሎች እነማን ነበሩ?

የባይዛንታይን ግዛተ አፄ መውደቅ ተከትሎ በእስያ የተመሠረተው የኦቶማን ግዛተ አፄ ነበር፡፡ የኦቶማን ግዛት አፄ የእስያ ጠንካራ መንግስት ለመሆን ችሎ ነበር፡፡ የኦቶማን ግዛተ አፄ የተመሠረተው በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ የትንሺ እስያ ነዋሪ በነበሩት በቱርኮች መሪ በኦስማን (1300-1326) ነበር፡፡ ቀስ በቀስ ግን ኦስማን የሚለው መጠሪያ ወደ ኦቶማን በመለወጡ እስካሁን ድረስ ኦቶማን በመባል ይጠራል፡፡ ቱርኮች የእስልምና እምነትን የተቀበሉት በ10ኛው መቶ ክፍለ

ዘመን ነበር:: በወታደራዊ አደረጃጀታቸው እና በጦር መሣሪያቸው የተሻሉ ነበሩ:: በዚህም የተነሳ ቱርኮች ወታደራዊ ዘመቻዎችን እና ወረራዎችን በማድረግ ብዙ ሀገሮችን ተቆጣጥረዋል::




ምስል 6.9. የኦቶማን ቱርክ ግዛተ አፄ

ከኦስማን ሞት በኋላ የተተካው ልጁ ኦርክሃን (1326-1359) ነበር:: እርሱም የአባቱን ፈለግ በመከተል በወረራ ግዛት ማስፋፋቱን እንዲያግዘው ቋሚ የጦር ሠራዊት ጃኒሳሪዎች አቋቋመ:: በመቀጠልም ለመጀመሪያ ጊዜ የአውሮፓን ምድር በመውረር የጋሊፓሊ ልሳነምድርን ተቆጣጠረ:: በእርሱ የተተካውና ስልጣን ላይ የወጣው ቀዳማዊ ሙራድ (1359-1389) ዘመነ መንግስትም የኦቶማን ቱርኮች ባልካን ምድር ዘልቀው በመግባት ተቆጣጠሩ::

## ተግባር-16

1. የመካከለኛው ምስራቅን ካርታ በመሳል የቱርክን መገኛ አሳዩ?
2. ተማሪዎች በጥንድ በጥንድ በመሆን ከባይዛንታይን እና ኦቶማን ቱርኮች አገዛዝ መውሰድ ያለብንን ተገቢ ተግባሮችን በመለየት ተወያዩ::

## 6.3. በአለም ላይ ያሉ ዋና ዋና ሃይማኖቶች

የሃይማኖት መሰረት የተጣለው በጥንት ዘመን የሰው ልጅ ልዩ ልዩ ተፈጥሯዊ ክስተቶችን መገንዘብ ከጀመረ በኋላ እንደሆነ ይታመናል። በጥንት ዘመን ሰዎች በወንዝ፣ በዛፍ፣ በተራራ፣ በጨረቃ ወዘተ ያመልኩ ነበር። በአለም ላይ ያሉ ዋና ዋና ሃይማኖቶች የሚከተሉት ናቸው።

### ተግባር-17

1. ሃይማኖት ምንድን ነው?
2. የሃይማኖታችሁን አስተምህሮት በአጭሩ ለመምህራችሁ ግለጹ።

ሀ) **የክርስትና ሃይማኖት፦** የክርስትና ሃይማኖት አስተምህሮት በአንድ አምላክ ማመን፣ የፈጣሪን ህግጋት (አለመስረቅ፣ ዝሙትን አለመፈፀም፣ ለራስ የሚወዱትን ለሌሎች መውደድ ወዘተ) መተግበር እና በዘላለማዊ ህይወት ማመን ላይ ያተኩራል። በአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በይሁዳ ግዛት በቤተ ልሄም የተጀመረ ሲሆን በተለያየ ጊዜ ወደ ሌላው አለም ተስፋፍቷል። በአራተኛው ክፍለ ዘመን ሃይማኖቱ በመላው የሮማ ግዛት በስፋት የተስፋፋ ሲሆን ለዚህም ምክንያቱ የሮማው ንጉስ ኮንስታንትኒን የክርስትና ሃይማኖትን በመቀበሉ ነበር። በአሁኑ ዘመን በአለም ላይ ከፍተኛ አማኞች አሉት።

ለ) **የእስልምና ሃይማኖት፦** የእስልምና ሃይማኖት በ570 ዓ.ም የተወለዱት ነብዩ ሙሐመድ በአረቢያ የነበረውን የቁረይሾች ባዕድ አምልኮ በመቃወም የእስልምና ሃይማኖትን በግልጽ እና በስፋት አስተምረውታል። ነብዩ ሙሐመድ በመካ ብዙ ፈተና ቢገጥማቸውም የአረቢያ ተወላጆችን በአንድ እምነት(እስልምና) ስር ማስተሳሰር ችለው ነበር። ከነብዩ ሙሐመድ ሞት በኋላ በተከታዮቻቸው ጥረት እስልምና ወደ ግብፅ፣ ቱኒዝያ፣ አልጀሪያ፣ ሜሶፖታሚያ፣ ፓለስታይን፣ ስፔን ሞሮኮ ወዘተ ሊስፋፋ ችሏል። የእስልምና ሃይማኖት ዋና አስተምህሮት በአላህ ፈጣሪነትና በነብዩ ሙሐመድ መልዕክተኛነት ማመን፣ ፆም መፆም፣ ሶላት መስገድ፣ ለተቸገሩ ምፅዋት መስጠት እና የሀጅ ጉዞ መፈፀምን መሰረት ያደረገ ነው።

ሐ) **የአይሁድ ሃይማኖት፦** ይህ ሃይማኖት በጥንታዊ እስራኤላዊያን ከ1500 ዓ.ዓ ቀደም ብሎ ተጀመረ። የዚህ ሃይማኖት አስተምህሮ በአንድ አምላክ ማመን፣ የፈጣሪን ህግጋት መፈፀም እና ፈጣሪ ሰዎችን ወደተሻለ ህይወት የሚመራ፣ ከጥፋት የሚከላከል መሆኑን ማመን ላይ ያተኩራል። የዚህ ሃይማኖት ተከታዮች

በእስራኤል እና በተለያዩ የአለም ክፍሎች የሚኖሩ ሲሆን የሙሴን ትምህርት የተከተሉ ኦሪታዊያን ናቸው።

**መ) የሒንዱ ሃይማኖት፦** ይህ ሃይማኖት የተጀመረው በህንድ ሀገር በ1500 ዓ.ዓ አካባቢ ነበር። ይህን ሃይማኖት በመጀመሪያ የተቀበሉት ሂንዱ የሚባሉ በህንድ የሚኖሩ ጎሳዎች ነበሩ። አንዳንዴ ብርሀማኒዝም በመባል ይጠራል። ህይወት እንደ ወንዝ ሳያቋርጥ ይቀጥላል። ነፍስም እንደወንዙ ሳያቋርጥ ይቀጥላል ብለው ያምናሉ። በአንድ አምላክ አያምኑም። ብዙ አማልክት አሏቸው። ምሳሌ ቬሹ የአለም ጠባቂ፣ ሺቫ የአለም ፈጣሪ እና አጥፊ አምላካቸው ነው።

**ሠ) የቡድሐ ሃይማኖት፦** የቡዲሂዝም ሃይማኖት ሲድራታ ጉተማ በተባለ ህንዳዊ በ500 ዓ.ዓ ተጀመረ። በአንድ ፈጣሪ አያምኑም። ሰዎች ውስጣዊ ስሜታቸውን ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ተቆጣጥረው መኖር ይጠበቅባቸዋል ብለው ያምናሉ። ጫፍ የዘለቀ ወይም በጣም ዝቅ ያለ ስብዕና ተገቢ አይደለም ብለው ያምናሉ። በኮሪያ፣ ትቤት፣ ፊንላንድ፣ ቻይና እና ጃፓን ሃይማኖቱ ይመለካል።

### ተግባር-18

1. ሃይማኖት እንዴት እንደተፈጠረ የሃይማኖት አባቶችን በመጠየቅ ዘገባ አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ሪፖርት አቅርቡ።
2. ስለ ልዩ ልዩ ሃይማኖቶች መማር ምን ጥቅም አለው? ሪፖርት ካዘጋጃችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁላቸው።

## ማጠቃለያ

- በአለም ላይ የተከሰቱት ስልጣኔዎች የወንዝ ዳር እና የመሬት ላይ ስልጣኔዎች ተብለው ይከፈላሉ:: የግሪክ እና የሮማ ስልጣኔዎች የመሬት ላይ ስልጣኔዎች ይባላሉ:: የሜሶፖታሚያ፣ የህንድ እና የቻይና ስልጣኔዎች ደግሞ የወንዝ ዳር ስልጣኔ ተብለው ይመደባሉ::
- እነዚህ በአለማችን ላይ የተከሰቱት ጥንታዊ ስልጣኔዎች ለአለም ህዝብ የአጻጻፍ ስልቶችን (ኩኒፎርም፣ ሳኑስክሪት እና ሎጎግራፊ)፣ ኪነ ህንፃዎችን፣ ሳይንስ እና ሂሳብን፣ ፍልስፍናን፣ የህክምና መሳሪያዎችን እና ኬሚካሎችን አበርክተዋል::
- በ476 ዓ.ም የሮማ ግዛተ አፄ ለሁለት ተከፈለ:: እነሱም የምዕራብ ሮማ ግዛተ አፄ እና የምስራቅ ሮማ ግዛተ አፄ ነበሩ:: የምስራቁ የሮማ ግዛተ አፄ የባዘንታይን ግዛተ አፄ ተብሎ ከ476-1453 ቆይቶ በኦቶማን ግዛተ አፄ በ1453 ዓ.ም ተተካ:: የኦቶማን ግዛተ አፄ በ1300 ዓ.ም በኦስማን ቀዳማዊ ተመስርቶ ነበር::
- የጨለማው ዘመን ከሮማ ግዛተ አፄ ውድቀት እስከ ህዳሴ ዘመን (500 -1400) ያለውን ዘመን ይሸፍናል:: የጨለማው ዘመን የተባለበት ምክንያት የጥንታዊ ግሪካዊያን እና ሮማዊያን ስልጣኔዎች የተዳከሙበት ወቅት ስለነበር ነው::
- በአለማችን ከ4300 በላይ ሃይማኖቶች እንዳሉ መረጃዎች ያሳያሉ:: ሶስት አራተኛ የሚሆነው የአለማችን ህዝብ የሚያመልካቸው ሃይማኖቶች ደግሞ ክርስትና፣ ሂንዱይዝም፣ እስልምና፣ ቡዲሂዝም እና ጁዳይዝም ናቸው::
- በአለማችን ያሉ ሃይማኖቶች የራሳቸው የእምነት ተቋማት፣ መመሪያ ወይም ሃይማኖታዊ ቀኖና ያላቸው በሀገሬ መንግስቶቻቸው ህጋዊ እውቅና እና ክብር የሚሰጣቸው ለሁሉም ሰው ድብቅ ያልሆኑ ሃይማኖታዊ ስነ ስርዓት ያላቸው ናቸው::

# የክለሳ ጥያቄዎች

**ክፍል አንድ፡** የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ትክክል ከሆኑ እውነት ስህተት ከሆኑ ደግሞ ሀሰት በማለት መልሱ።

1. ሥልጣኔ በተመሳሳይ ጊዜና ሁኔታ በሁሉም የዓለም ክፍሎች አልተጀመረም።
2. የጥንታዊት ሮማ ስልጣኔ ከወንዝ ዳርቻ ስልጣኔዎች ውስጥ ይመደባል።
3. የኦሎምፒክ ስፖርትን ለአለም ህዝብ ያስተዋወቁት ጥንታዊ ስፓርታዊያን ነበሩ።

**ክፍል ሁለት፡** ቀጥሎ ለቀረቡት የምርጫ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ መልሱ።

1. በጤግሮስ እና ኤፍራጠስ ወንዞች መካከል የምትገኝ ጥንታዊ ስልጣኔ የተጀመረባት ቦታ

   ሀ) ህንድ ለ) ሜሶፖታሚያ ሐ) ግሪክ መ) ሮማ

2. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ በትክክል የተጣመረው የትኛው ነው?

   ሀ) መሳፍንት---ፕለቢያን ሐ) ተራው ህዝብ---ፓትሪሽያን

   ለ) ባለ መሬቶች----ኢኩቲስ መ) መልሱ የለም

3. ለህንድ ስልጣኔ መጀመር አስተዋጽኦ የነበራቸው ጎሳዎች

   ሀ) ስፓርታዊያን ለ) ሀራፓዊያን ሐ) አቴናዊያን መ) ኢትሩስካናዊያን

4. የጥንታዊት ቻይና ስልጣኔ በዘመኑ ከነበሩት ሌሎች ስልጣኔዎች የምትለይበትን ሁኔታ የሚገልጸው

   ሀ) ከሌላው አለም ራሷን ለይታ የኖረች መሁኗ

   ለ) ያልተቀዳ የራሷ የሆነ ስልጣኔ ማዳበሯ

   ሐ) በትንንሽ ግዛቶች የተከፈለች መሆኗ

   መ) ሁሉም መልስ ናቸው።

**ክፍል ሶስት፡** ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ።

1. የጥንታዊ ሜሶፖታሚያ ስልጣኔ መውደቅ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱን ብቻ ፃፉ።

2. የጥንታዊ ግሪክን ካርታ ከሰራችሁ በኋላ የአቴናን እና የስፓርታን ከተሞች አሳዩ::
3. ጥንታዊ ቻይናዊያን ታላቁን ግንብ የሰሩበት ምክንያት ምን ነበር?
4. በጥንታዊ ሱመርያን የተገኘው የመጀመሪያው የአፃፃፍ ስልት ምን ተብሎ ይጠራል?
5. ጥንታዊ ሮማውያን ኢትሩስካን ከሚባሉት ነገዶች የተማሯቸው ወይም የወረሷቸውን የስልጣኔ መስኮች በመለየት መልሱ::

## ፈታኝ ጥያቄዎች

1. የግብፅን ስልጣኔ ከህንድ፣ ቻይና እና ሜሶፖታሚያ ስልጣኔዎች ጋር አወዳድሩ:: የትኞቹ ስልጣኔዎች በጣም አስደነቋችሁ? ለምን?
2. የፊውዳል ሥርዓት ምን ማለት ነው? ምን አይነት ስልተምርት/የፖለቲኮ-ኢኮኖሚ ሥርዓት ነው? ከኛ ሀገር ጋር በማገናዘብ ሰርታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ሪፖርት አቅርቡ::
3. ቤተ መፃህፍት በመግባት መፃህፍትን በማንበብ አፄ ጁስቲኒያን ህጎች ምን ምን ጉዳዮች ላይ እንደሚተኩሩ ከለያችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው::

## የቃላት ፍች

- **ደሴት-** በውሐ የተከበበ ደረቅ መሬት ማለት ነው::
- **አማልክት-** እንደ አምላክ የሚመለክባቸው ግዑዝ ነገሮችን ያሣያል::
- **ግዛተ አፄ-** በአንድ ንጉስ ስር ያለ ግዛት ማለት ነው::
- **ጎሳ-** የጥንታዊ ጋርዮሽ ኅብረተሰብ አደረጃጀት አይነት ነው:: በቁጥር(ብዛት) ከነገድ ያነሱ ሆነው መላው አባሎቻቸው በደም የተሳሰሩ ናቸው:: እርስበርስ አይጋቡም::
- **ነገድ-** የጥንታዊ ጋርዮሽ ኅብረተሰብ አደረጃጀት አይነት ነው:: በብዛት ከጎሳ ይበልጣሉ:: ብዙ ጎሳዎችን ይይዛሉ:: ጋብቻን እርስበርስ ይጋባል:: ሰብል አመራረታቸው ይለያያል::
- **ጃኒሳሪ-** የቱርኮች ቋንቋ ሲሆን ወታደር ማለት ነው::

# ምዕራፍ-7

# ወቅታዊ ዓለም ዓቀፋዊ ሁኔታዎች

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ስር በአሁኑ ወቅት ለዓለም ሕዝብ ህልውና ከፍተኛ ስጋት በመፍጠር ላይ የሚገኙ አሳሳቢ ዓለም ዓቀፋዊ ክስተቶች ይዳሰሳሉ:: ይህ ምዕራፍ አምስት ዋና ዋና ርእሰ ጉዳዮችን ያካተተ ነው:: በመጀመሪያው ክፍል በተፈጥሮ አካባቢ ላይ አደጋ የጋረጡ ዋና ዋና ችግሮች ይፈተሻሉ:: በሁለተኛውና በሶስተኛው ንኡስ ርእሶች ስር ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት በተፈጥሮ ሀብቶችና በማህበረ-ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ያሳደረው አሉታዊና አዎንታዊ ተጽእኖዎች እና ዓለም ዓቀፍ ሽብርተኝነት በሰው ልጆች ደህንነት ላይ የደቀነው ስጋት ይመረመራሉ:: ንኡስ ምእራፍ አራት ዓለም ዓቀፍ ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን ሁኔታ የሚመረምር ሲሆን የመጨረሻው ንኡስ ምእራፍ ደግሞ መድሀኒት ያልተገኘለት ኤች አይ ቪ ኤድስ እያደረሰ ባለው ዘርፈ ብዙ ጉዳት ላይ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ይዘት ለጥናት የቀረበበት ክፍል ነው::

**ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት:**

*ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦*

- የአካባቢን ምንነት ትገልጻላችሁ::
- አካባቢን የሚጎዱ የሰው ልጅ ተግባራትን ትመረምራላችሁ::
- የበረሀማነት መስፋፋት መንስኤዎችንና ውጤቶቹን ትተነትናላችሁ::
- የአየርና የውሀ ብክለት መንስኤዎችንና ውጤቶቹን ታብራራላችሁ::
- ወቅታዊ አካባቢያዊ እና ዓለም አቀፋዊ ችግሮችን ትገመግማላችሁ::
- አካባቢያዊ እና ዓለም አቀፋዊ ችግሮችን የመፍቻ ዘዴዎችን ትመረምራላችሁ::

- ግለሰቦች እና ማህበረሰቡ አካባቢን ለመንከባከብ የሚያደርጉትን ተሳትፎ ትገመግማላችሁ::
- የኤች አይቪ ኤድስን የመተላለፊያና መከላከያ መንገዶችን ትለያላችሁ::

**ቁልፍ ቃላት:**

| | | |
|---|---|---|
| ኤች አይ ቪ | በረሀ | አካባቢ |
| በካይ | ኤድስ | ሽብርተኝነት |

## 7.1. ወቅታዊ አካባቢያዊ ጉዳዮች

በዓለም ላይ የሰው ልጅ ተግባራት የጋረጧቸው በርካታ ችግሮች አሉ:: ከእነዚህ መካከል የከፋ አደጋና ስጋት የፈጠሩት ክስተቶች ከዚህ በታች ለጥናት ቀርበዋል::

### ሀ) የበረሀማነት መስፋፋት

ተማሪዎች! መቼም በምትኖሩበት አካባቢ በረሀ የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ ስለሚነገር ለቃሉ እንግዳ እንደማትሆኑ በእግጠኝነት መናገር ይቻላል:: ታዲያ የበረሀን ትክክለኛ ትርጉም መናገር ትችላላችሁ? ሁላችሁም በሚባል ደረጃ በረሀ ማለት እጅግ በጣም ሞቃት የሆነ የአየር ንብረት ያለበት ስፍራ ነው ብላችሁ እንደምታስቡ ይገመታል:: በእርግጥ አንዱ የበረሀ መገለጫ እጅግ የሚያንገበግብ የፀሀይ ሙቀት መኖሩ ነው:: ነገር ግን ይህ መስፈርት ወይም መገለጫ ብቻውን የበረሀን ምንነት ይገልጻል? እስኪ ከዚህ በፊት ስለ በረሀ የነበራችሁን አስተሳሰብ ቀጥሎ ከቀረቡላችሁ ማብራሪያዎች አንጻር ገምግማችሁ ትክክለኛውን የበረሀ ትርጉምና ጽንሰ ሐሳብ ለመጨበጥ ሞክሩ::


በረሀ ማለት በዓመት ከ250 ሚ.ሜ በታች የዝናብ መጠን የሚያገኝ ስፍራ ማለት ነው:: ይህ ዓመታዊ የዝናብ መጠን እጅግ በጣም ዝቅተኛ ስለሆነ ለእጽዋት እድገት በቂ አይደለም:: በዚህ ትርጉም መሰረት የበረሀ ዋነኛው መለያ ምንድን ነው? ከፍተኛ የሙቀት መጠን ወይስ እጅግ በጣም ዝቅተኛ የዝናብ መጠን? ከዚህ በታች የቀረበው ማብራሪያ ለዚህ ምላሽ የሚሰጣችሁ ይሆናል:: በግምት 1/3 የሚሆነው የመሬት ክፍል በበረሀ የተሸፈነ ነው:: በጂኦግራፊያዊ መገኛቸው መሰረት በዓለም ላይ 4 የበረሀ ዓይነቶች አሉ:: እነርሱም፦

1. ዋልታዊ በረሀዎች (polar deserts)
2. ከፊል ገሞጅማ በረሀዎች (subtropical deserts)
2. የበጋ ቀዝቃዛ በረሀዎች ( cold winter deserts) እና
3. ቀዝቃዛ የባህር ዳርቻ በረሀዎች (cool coastal deserts)

## ተግባር-1

1. ምስል 1ን መሰረት በማድረግ ከላይ የተዘረዘሩትን የበረሀ ዓይነቶች ከመገኛ ስፍራዎቻቸው አንጻር መርምራችሁ ባህሪያቸውን ግለጹ (ለምሳሌ፡-ቀዝቃዛ፣ ሞቃት፣ ወዘተ)::

ተማሪዎች! በዓለም ላይ ከሚገኙት በረሀዎች ውስጥ በቆዳ ስፋታቸው የመጀመሪያውንና ሁለተኛውን ደረጃ የሚይዙት መገኛቸው በዋልታዎች አካባቢ ሲሆን እነርሱም የአንታርክቲክ ዋልታዊ በረሀ (The Antarctic Polar Desert) እና የአርክቲክ ዋልታዊ በረሀ (The Arctic Polar Desert) ናቸው:: በእስያ አህጉር የሚገኘው የጎቢ በረሀም ከቀዝቃዛ በረሀዎች ውስጥ የሚመደብ ነው:: እነዚህ በረሀዎች እጅግ በጣም ቀዝቃዛ የአየር ንብረት ያላቸው ናቸው::




ምስል 1 - ዋና ዋና የዓለም በረሀዎች

ሠንጠረዥ 1 - አስሩ የዓለም ታላለቅ በረሀዎች በቅደም ተከተላቸው ሲቀመጡ።

| ደረጃ | የበርሃው ስም | የቆዳ ስፋት በኪ.ሜ.$^2$ |
|---|---|---|
| 1 | አንታርክቲክ | 14,200,000 |
| 2 | አርክቲክ | 13,900,000 |
| 3 | ሳሃራ | 9,200,000 |
| 4 | ታላቁ አውስትራሊያ (ታላቁ ቪክቶሪያን ጨምሮ) | 2,700,000 |
| 5 | አረባዊ | 2,330,000 |
| 6 | ጎቢ | 1,295,000 |
| 7 | ካላሃሪ | 900,000 |
| 8 | ፓታጎኒያ | 637,000 |
| 9 | ሶሪያዊ | 500,000 |
| 10 | ታለቁ ቤስን | 492,098 |



ምስል 2 - የሚኪ ሙርዶ ደረቃማ ሸለቆዎች (አንታርክቲካ)



ምስል 3 - የሳሀራ በረሀ

## ተግባር-2

1. በምትኖሩበት ወረዳ አካባቢውን ለበረሀማነት የሚያጋልጡ የማህበረሰብ እንቅስቃሴዎችን አስተውላችኋል? እስኪ ለመዘርዘር ሞክሩ።

የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም (1991) ባወጣው ዘገባ መሰረት በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በረሀማነት በፍጥነት እየተስፋፋ ይገኛል። 35% (4.5 ቢሊየን ሄክታር) ወይም በጥቅሉ የሰሜንና ደቡብ አሜሪካን አህጉራት የቆዳ ስፋት ያህል የሚሸፍን የዓለማችን ክፍል የበረሀማነት መስፋፋት አደጋ የተጋረጠበት ሲሆን በዚህ ክልል ውስጥ የሚገኙ 850,000,000 ሰዎች ደግሞ የችግሩ ተጠቂዎች ሆነዋል። በተለይ $^{2}/3$ የሚሆነው የመሬት ክፍሉ በረሃማ የሆነበት የአፍሪካ አህጉር የችግሩ ግንባር ቀደም ተጠቂ ነው።

የበረሃማነት መስፋፋት ዋነኞቹ መንስኤዎች የግጦሽ መሬትን ከአቅሙ በላይ ማስጋጥ፣ የደን ጭፍጨፋ፣ ኋላ ቀር አስተራረስ፣ ሰው ሰራሽ ማዳበሪያና ጸረ ተባይ መድኃኒቶችን ያለ ገደብ መጠቀም፣ የከተሞች መስፋፋት፣ የአየርና የአፈር ብክለትና የተፈጥሮ ሀብት ሊሸከመው የማይችል የሕዝብ ብዛት ናቸው።

## ተግባር-3

1. በረሀማነት የሚያስከትላቸውን ችግሮች በመዘርዘር ማብራሪያ ስጡባቸው::
2. የበረሀማነት መስፋፋትን ለመግታትና የሚያስከትላቸውን ችግሮች ለመከላከል ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?




ምስል 3 - የበረሀማነት ገጽታዎች

### ለ) የአየር ብክለት

ተማሪዎች! በቅድሚያ አየር በተፈጥሮው ሽታ፣ ጣዕምና ቀለም የለሽ ቁስ መሆኑን ልትገነዘቡ ይገባል:: ነገር ግን በምትጓዙበት መንገድ ግራና ቀኝ ላይ ወይም በመኖሪያ ቤታችሁ አካባቢ ከሰዎችና ከእንስሳት የሚወገዱ ጽዳጆች (Wastes) በሚለቁት መጥፎ ሽታ ተረብሻችሁ አታውቁም? ሽንት ቤት ሲመጠጥ ያጋጠማችሁ ካላችሁ ደግሞ ምን ያህል ለመተንፈስ እንደሚያስቸግር አስተውላችኋል? ይህ የአየር ብክለት አንዱ መገለጫ ነው:: የተለያዩ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ የሆኑ መርዛማ ንጥረ ነገሮች በከባቢ አየር ውስጥ ሲቀላቀሉና አየሩ ተፈጥሯዊ ባህሪውን በመቀየር በተለይ ሕይወት ላላቸው ነገሮች ጎጂ ሆኖ ሲገኝ ክስተቱ የአየር ብክለት ይባላል:: የዓለም የጤና ድርጅት ጥናት እንደሚያመለክተው ከአስር ሰዎች መካከል ንጹህ አየር የሚተነፍሰው አንዱ ብቻ ነው::

## ተግባር-4

1. የአየር ብክለት ዋነኛ መንስኤዎች ምንድን ናቸው?
2. የአየር ብክለትን ለመከላከል ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?



ምስል 4 - የከባቢ አየር በካዮች ናሙና

### ሐ) የውሀ ብክለት

ተማሪዎች! በምትኖሩበት ቀበሌ፣ ከተማ ወይም ወረዳ የሚገኙ ወንዞች፣ ኩሬዎች፣ የጉድጓድ ውሀ ወይም ምንጮች የንጽህና ሁኔታቸው በምን ደረጃ ላይ ይገኛል? ከየቤቱ ከሚወጡ ደረቅ ወይም ፈሳሽ ቆሻሻዎች ብክለት ነጻ ናቸው? የሰፈራችሁ ነዋሪ ከቤቱ የሚያወጣውን ቆሻሻ የሚያስወግደው እንዴት ነው? እስኪ ምስል 5ን ልብ ብላችሁ ተመልከቱት። ከምስሉ ምን ትገነዘባላችሁ?

የውሀ ብክለት የተለያዩ ውሀማ አካላት (ሐይቆች፣ ወንዞች፣ ባህሮች፣ ውቅያኖሶችና የከርሰ ምድር ውሀ) በተለያዩ ሰው ሰራሽ ወይም ተፈጥሯዊ ንጥረ ነገሮች ሲመረዙ የሚፈጠር ክስተት ነው። በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሰራሽ ክስተቶች ምክንያት ውሀ በሚበከልበት ጊዜ ተፈጥሯዊ ይዘቱን ስለሚቀይር ራሱን ሊያድስ አይችልም። ስለዚህ የውሀው አካላዊ ጥራትና ስነ ሕይወታዊ ይዘት ስለሚዛባ ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታውም ይቀንሳል።




ምስል 5 - የውሀ በካዮች ናሙና



ምስል 6 - የውሀ ብክለት ውጤት ናሙና

### ተግባር-5

1. የውሀ ብክለት ዋነኛ መንስኤዎች ምንድን ናቸው?
2. የውሀ ብክለትን ለመከላከል ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?

## 7.2. ፈጣን የህዝብ ቁጥር እድገት

### ተግባር-6

1. ተማሪዎች ብዙ ልጆችን መውለድ ያለውን አዎንታዊ እና አሉታዊ ጎኖች ግለፁ::
2. የአንድ ቤተሰብ አባላት ቁጥር ቤተሰቡ ካለው ምጣኔ ሀብታዊ ደረጃ ጋር ካልተጣጣመ ምን ዓይነት ሁኔታ የሚፈጠር ይመስላችኋል?

ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት ማለት የአንድ አገር የተፈጥሮ ሀብት ሊሸከም ከሚችለው አቅም በላይ ወይም የአገሪቱ ምጣኔ ሀብታዊ እድገት ሊፈጥረው ከሚችለው የስራ እድል በላይ የሆነ የሕዝብ ብዛት መኖር ማለት ነው:: በአገራችን ለፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት መንስኤ የሆኑ በርካታ ምክንያቶች አሉ:: እነርሱም ባህላዊ አስተሳሰቦች (ለምሳሌ፦ ብዙ ልጆችን የወለደች እናት ስትከበር በአንጻሩ ደግሞ መሀን የሆነች ወይም አንድና ሁለት ልጆች ብቻ ያላት እናት ትናቃለች፣ ልጅ በእድሉ ያድጋል የሚል እምነት)፣ ምጣኔ ሀብታዊ ሁኔታዎች (ለምሳሌ፦ ልጆች የገቢ ምንጭ መሆናቸው፣ ወላጆች በእርጅና ጊዜ ልጆች ይጦሩናል ብሎ ማሰብ) እንዲሁም ፖለቲካዊ አስተሳሰብ (ለምሳሌ፦ በቁጥር ብዙ ሆኖ መገኘት ለአንድ ጎሳ ወይም ብሔረሰብ ህልውናና የበላይነት እንደ ዋስትና መቁጠር) ናቸው::

### ተግባር-7

1. በምትኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ የሕዝብ ቁጥር በፍጥነት እንዲጨምር የሚያደርጉ አስተሳሰቦችን፣ እምነቶችን ወይም ምክንያቶችን በሠንጠረዥ በተቀመጡላችሁ ምድቦች ስር በመዘርዘር አመልክቱ::

ሠንጠረዥ 2 - ፈጣን የሕዝብ ቁጥር የሚያስከትሉ ሁኔታዎች

| ማህበራዊ ምክንያቶች | ምጣኔ ሀብታዊ ምክንያቶች | ባህላዊ ምክንያቶች | ፖለቲካዊ ምክንያቶች |
|---|---|---|---|
| 1. | 1. | 1. | 1. |
| 2. | 2. | 2. | 2. |
| 3. | 3. | 3. | 3. |
| 4. | 4. | 4. | 4. |

ለዓለም የሕዝብ ቁጥር ፈጣን እድገት ዋነኞቹ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፦

- ዝቅተኛ የትምህርትና የስልጣኔ ደረጃ
- ልጆች የጉልበት ምንጭ መሆናቸው
- የሴቶች የትምህርትና የስራ እድል አለመስፋፋት
- የወሊድ መቆጣጠሪያ አገልግሎት አለመስፋፋት
- የጋብቻ እድሜ ዝቅተኛ መሆን
- የጡረታ ዋስትና አለመኖር
- ኃይማኖታዊና ባህላዊ አስተሳሰቦች
- ከፍተኛ የህጻናት ሞት መጠን

## ተግባር-8

1. እያንዳንዱ ከላይ የተጠቀሰው ምክንያት እንዴት ለፈጣን የሕዝብ ቁጥር ጭማሬ መንስኤ እንደሚሆን አብራሩ፡፡
2. ፈጣን የህዝብ ቁጥር አድገትን ለመከላከል ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?

የሕዝብ ቁጥር ጭማሬ ከማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ እድገት ጋር ካልተጣጣመ በርካታ ችግሮችን ያስከትላል፡፡ ከእነዚህ ችግሮች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፦

**ሀ) ቤተሳባዊ ችግሮች** - ከፍተኛ የውልደት መጠን መኖር ተጽእኖው በቅድሚያ የሚገለጸው በቤተሰብ ደረጃ ነው፡፡ ብዙ አባላት ባሉበት ቤተሰብ ውስጥ የምግብ እጥረት ይከሰታል፤ የፍጆታ፣ የህክምና፣ የልብስና የትምህርት ወጪ ይጨምራል፣ በወላጆች ላይ የምጣኔ ሀብትና የስነ ልቦና ችግር ይፈጠራል እንዲሁም የእናቶችና የህጻናት ሞት መጠን ይጨምራል፡፡

**ለ) ማህበራዊ ችግሮች** - የሕዝብ ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት መጨመር በተለይ በትምህርት፣ በጤና፣ በመኖሪያ ቤት፣ በውሀ፣ በመብራትና ተዛማጅ አገልግሎቶችና አቅርቦቶች ላይ ከፍተኛ ጫና ያሳድራል፡፡ የሕዝብ ቁጥር በፈጣን ሁኔታ ሲጨምር እነዚህን ማህበራዊ አገልግሎቶች ለህብረተሰቡ በበቂ ሁኔታ ማዳረስ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

*ተግባር-9*

1. በምትኖሩበት አካባቢ ከሕዝብ ቁጥር መጨመር ጋር በተያያዘ የሚታየውን የትምህርት ቤቶችና የጤና ተቋማት መጨናነቅ፤ የውሀ፣ የመጓጓዣና የመኖሪያ ቤት እጥረቶች እንዲሁም የመብራት እጦት ችግርን እንዴት ትገመግሙታላችሁ?

**ሐ) ምጣኔ ሀብታዊ ችግሮች** - የሕዝብ ብዛት በጨመረ ቁጥር በምርታማ ተግባር (ለምሳሌ፡- ፋብሪካዎችን መገንባት) ላይ ሊውል የሚገባው የአገሪቱ ካፒታል (ገንዘብ) ለተጨማሪ ማህበራዊ አገልግሎቶች ማስፋፊያ ወጪ (ለምሳሌ፡- ለጤና፣ ለትምህርት፣ ለውሀ፣ ለመኖሪያ ቤት ግንባታ፣ ወዘተ) ስለሚውል የነፍስ ወከፍ ምርትና የነፍስ ወከፍ ገቢ ይቀንሳል፡፡

**መ) አካባቢያዊ ችግሮች** - ለግንባታ ስራ፣ ለማገዶ ፍጆታና ለእርሻ ቦታ ማስፋፊያ ሲባል የደኖች በከፍተኛ ሁኔታ መጨፍጨፍና ይህን ተከትሎ የአፈር ለሸርሸራ መጋለጥ፣ የከባቢ አየር መበከልና የመሳሰሉት ችግሮች የሕዝብ ቁጥር ፈጣን እድገትን ተከትለው የሚመጡ አካባቢያዊ ችግሮች ናቸው፡፡

## 7.3. ሽብርተኝነት (Terrorism)

ተማሪዎች! የሽብር ተግባርን ምንነት በተመለከተ ግንዛቤ አላችሁ? በአካባቢያችሁ የሽብርተኝነት አዝማሚያን የሚያመላክቱ ሁኔታዎች አስተውላችኋል? በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ስለተፈጸሙ የሽብር ጥቃቶችስ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ሽብርተኝነት አንድን የተለየ የፖለቲካ ዓላማ ለማሳካት ታቅዶ ማንንም ሳይለይ በሕይወትና በንብረት ላይ ጥቃት የመፈጸምና በማህበረሰብ ውስጥ ፍርሀት የመፍጠር ተግባር ወይም እንቅስቃሴ ነው፡፡ የሚከተሉት ምስሎች ከልብ ወለድ ፊልሞች የተቀዱ አይደሉም፡፡ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በተለያዩ ጊዜያት ከተፈጸሙ የሽብር ጥቃቶች የተወሰዱ እውነተኛ ፎቶግራፎች ናቸው፡፡

*ተግባር-10*

1. ፎቶግራፎቹን በጥሞና መርምራችሁ የሽብርተኝነትን ምንነትና ውጤቱን ገምግሙ፡፡





ምስል 7 - በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የተፈጸሙ የሽብር ጥቃቶች

ሽብርተኝነት ከመደበኛም ሆነ ከሽምቅ ውጊያ የሚለይበት ዋነኛ መገለጫው ባልታጠቁ የህብረተሰብ ክፍሎችና በሲቪል ተቋማት ለምሳሌ፦ በህዝብ መጓጓዣዎች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በንግድ (ገበያ) እና በመሳሰሉት ስፍራዎች ላይ አደጋ በማድረስ በማህበረሰብ ውስጥ ፍርሀትን ለማንገስ የሚያስችለውን ጥቃት የሚፈጽም በመሆኑ ነው።

በምስል 8 ላይ የምትመለከቱት ፎቶግራፍ የሚያሳየው በዩናይትድ ስቴትስ (USA) ውስጥ መስከረም 1 ቀን 1994 ዓ.ም (September 11, 2001) የተፈጸመውን እጅግ ዘግናኝ የጥፋት ተግባር ነው። በፎቶግራፉ ላይ እንደምታዩት በዚህ የሽብር ጥቃት በኒውዮርክ ከተማ የሚገኘው የዓለም የንግድ ማእከል መንትያ ሕንጻዎች ወድመዋል። በጥቃቱ 3000 የሚደርሱ ሰዎች ሕይወታቸው አልፏል።

## ተግባር-11

1. የሽብርተኝነት መንስኤው ምንድን ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?
2. የሽብርተኝነት አስተሳሰብ እንዳያቆጠቁጥ ወይም ሽብርተኝነትን ለመከላከል ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?
3. በአገራችን የተፈጸመ የሽብር ጥቃት ስለመኖሩ በቡድን በቡድን በመሆን ተወያዩበት።



ምስል 8 - በአሜሪካ መስከረም 1, 1994 ዓ.ም (September 11,2201) የተፈጸመ የሽብር ጥቃት

## 7.4. ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር (Human Trafficking)

**ውድ ተማሪዎች!** አንዳንድ ሰራተኛና አሰሪን እናገናኛለን የሚሉ ደላሎች በተለይ ታዳጊ ወንዶችንና ሴቶችን በማባበል ከገጠር ወደ ከተማ እንዲሰደዱ በማድረግ ወጣቶቹን ለጉልበት ብዝበዛና ለከፋ ሕይወት በመዳረግ የገቢ ምንጭ እንደሚያደርጓቸው በአካባቢያችሁ ከሚኖሩ ሰዎች ወይም ከዘመዶቻችሁ ሰምታችሁ ይሆናል:: ከዚህ እጅግ በባሰ ሁኔታ ደግሞ ከአንድ አገር ወደ ሌላ አገር የሚደረገው ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር (Human Trafficking) እየተስፋፋ በመሄድ ላይ የሚገኝ ዓለም ዓቀፋዊ ችግር ሆኗል ( ይህን እውነታ በምስል 9፣ 10 እና 11 ላይ መመልከት ይቻላል)::



ምስል 9 - ዓለም ዓቀፍ ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር በሜዲትራኒያን ባህር ላይ

ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ኃይልን በመጠቀም ወይም የውሸት ተስፋ በመስጠት ሰዎችን በድብቅ አፍኖና በኃይል አስገድዶ በጀልባ የማጓጓዝ፣ በባህር ዳርቻዎች ላይ በሚገኙ ስውር መጠለያዎች የማጎርና በመጨረሻም በግዳጅ ስራ ላይ በማሰማራት ገንዘብ የማግኛ የወንጀል ድርጊት ነው:: ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር የዘመናዊ ባርነት ተምሳሌት ነው:: ምክንያቱም ታጋቾቹ በአደባባይ ለሕዝብ በሚታዩ የስራ መስኮች (ለምሳሌ፡- በሱቅ ወይም በሆቴል አስተናጋጅነት፣ በምግብ አብሳይነት፣ በተላላኪነት፣ በፋብሪካ ስራ፣ ወዘተ) ላይ እንዲሰማሩ አይፈቀድላቸውም:: ሴቶች በድብቅ በቤት ሰራተኛነት እንዲያገለግሉና ተገድደው ጋብቻ እንዲፈጽሙ፣ ህጻናቱ በልመና እንዲሰማሩና ወጣቶቹ ለጦርነት እንዲዘምቱ ይደረጋሉ:: ከዚህ በከፋ ሁኔታ ደግሞ የተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸው (ለምሳሌ፡- ኩላሊት፣ ልብ) እየወጡ ለሽያጭ ይቀርባሉ ወይም ግለሰቦቹ በሕይወት ሳሉ እንደ እንስሳ ይሸጣሉ::



ምስል 10 - ዓለም ዓቀፍ ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር በሊቢያ የባህር ጠረፍ ላይ

የህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር መንስኤዎችን ማህበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ቀውሶች በሚሉ ምድቦች ስር በጥቅሉ መፈረጅ ይቻላል:: በጥልቀት ሲፈተሹ ደግሞ በተግባር 12 በተራ ቁጥር 1 ስር የተዘረዙትን ምክንያቶች እናገኛለን::

## ተግባር-12

1. የሚከተሉትን የህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር መንስኤዎች በመተንተን ማብራሪያ ስጡባቸው::
   - ደካማ መንግስት
   - ድህነት
   - ሙስና
   - የእርስ በርስ ግጭትና አለመረጋጋት
   - የቤተሰብ መበተን
   - የሰብአዊ መብቶች አለመከበር ወይም ጥሰት
   - የትምህርትና የስራ እድል እጦት
2. ከላይ የተቀመጡትን የችግሩን መንስኤዎች መሰረት በማድረግ ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመግታት መወሰድ የሚገባቸውን እርምጃዎች ጥቀሱ::

ውድ ተማሪዎች! ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር በአገራችንም የሚስተዋል ክስተት ነው:: የችግሩ ዋነኛ ተጠቂዎችም በድህነት ውስጥ የሚኖሩና በህገ ወጥ መንገድ ለስደት የሚንቀሳቀሱ ወጣቶች ናቸው:: እነዚህ ስደተኞች ለግዳጅ ስራ እንዲሰማሩ

ይደረጋሉ፣ ደሞዛቸውን ይቀማሉ፣ እንቅልፍ እንዳይተኙ ይደረጋሉ፤ ድብደባም ይፈጸምባቸዋል። አንዳንዶቹ ስቃዩ ሲበረታባቸው ራሳቸውን ያጠፋሉ። ቀጥሎ የምትመለከቷቸው ፎቶግራፎች የሚያሳዩት ወደዚህ እጅግ አስከፊ ወደሆነው የሕይወት መዳረሻ የሚጓዙትን ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንን ነው።










ምስል 11 - የኢትዮጵያውያን ህገ ወጥ ዓለማቀፋዊ ዝውውርና ፍልሰት

## ተግባር-13

1. ከምስሎቹ ምን ትገነዘባላችሁ? ምስሎቹን ስትመለከቱ ምን ተሰማችሁ?
2. አንተ/አንቺ ወደፊት የኢትዮጵያ መሪ ብትሆን/ብትሆኚ የስደትን ችግር ለመፍታት ምን ታደርጋለህ/ሽ?
3. ከአካባቢያችሁ ስለ ስደት አስከፊነት የሚያውቅ ሰው በመጠየቅ አንድ ገጽ ዘገባ አዘጋጅታችሁ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።


## 7.5. ኤች አይ ቪ ኤድስ (Human Immunodeficiency Virus/HIV)

ተማሪዎች! በመኖሪያ አካባቢያችሁ ሰዎች ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ መንስኤና ስለሚያስከትለው ጉዳት ሲነጋገሩ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? በትምህርት ቤታችሁስ መምህራን ስለዚህ ጉዳይ አስረድተዋችሁ ያውቃሉ?

### ተግባር-14

1. የኤች አይ ቪ መተላለፊያ መንገዶች ምንድን ናቸው? የማይተላለፍባቸውስ?
2. ኤች አይ ቪ ኤድስን ለመከላከል ምን ማድረግ ይገባል ትላላችሁ?


ከታች በምስል 12 የምትመለከቱት ፎቶግራፍ ያምራል! ነገር ግን የሚያምር ነገር ሁሉ ጠቃሚ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ይህ ምስል የሚያሳየው የኤድስ በሽታ መንስኤ የሆነውን ገዳዩን ቫይረስ ኤች አይ ቪን ነው።



ምስል 12 - የኤች አይ ቪ 3 ስፍረታዊ (3-dimensional) እይታ

የኤድስ በሽታ (AIDS /Acquired Immunodeficiency Syndrome/) መድሀኒት አልተገኘለትም። በምስል 13 ላይ እንደሚታየው በኤች አይ ቪ ኤድስ የተጠቃ ሰው በእንቅልፍ ጊዜ ሰውነቱን የማላብ፣ የአፍና የጉሮሮ ቁስለት፣ የድካምና የጭንቀት ስሜት፣ የጡንቻ ህመምና የቆዳ ላይ ሽፍታዎች እንዲሁም ትኩሳትና የእጢዎች

እብጠት ምልክቶች ይታዩበታል፡፡




ምስል 13 - የኤች አይ ቪ ኤድስ ምልክቶች

## ማጠቃለያ

- በዓለም ላይ የሰው ልጅ ተግባራት የጋረጧቸው በርካታ ችግሮች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹ የበረሃማነት መስፋፋት፣ የአየር ብክለት፣ የውሀ ብክለትና ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት ናቸው፡፡ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት ማለት የአንድ አገር የተፈጥሮ ሀብት ሊሸከመው ከሚችለው አቅም በላይ የሆነ የሕዝብ ብዛት መኖር ማለት ነው፡፡ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ጭማሬ ከማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ እድገት ጋር ካልተጣጣመ ቤተሰባዊ፣ ማህበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እና አካባቢያዊ ችግሮችን ያስከትላል፡፡
- ሽብርተኝነት በማህበረሰብ ውስጥ ፍርሀት በመፍጠር አንድን የተለየ የፖለቲካ ዓላማ ለማሳካት ማንንም ሳይለይ በሕይወትና በንብረት ላይ ጥቃት የመፈጸም ተግባር ነው፡፡ ሽብርተኝነት ከመደበኛም ሆነ ከሽምቅ ውጊያ የሚለየው ባልታጠቁ የሕብረተሰብ ክፍሎችና በሲቪል ተቋማት ለምሳሌ፡- በህዝብ መጓጓዣዎች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በገበያ ስፍራዎችና በመሳሰሉት ላይ ጥቃት የመፈጸም ተግባር በመሆኑ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

- ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር የዘመናዊ ባርነት ተምሳሌት ነው:: ምክንያቱም ታጋቾቹ በአደባባይ ለሕዝብ በሚታዩ የስራ መስኮች (ለምሳሌ፦ በሱቅ ወይም በሆቴል አስተናጋጅነት፣ በምግብ አብሳይነት፣ በተላላኪነት፣ በፋብሪካ ስራ፣ ወዘተ) ላይ እንዲሰማሩ አይፈቀድላቸውም:: ሴቶች በቤት ሰራተኛነት እንዲያገለግሉና ተገድደው ጋብቻ እንዲፈጽሙ፣ ህጻናቱ በልመና እንዲሰማሩ፤ ወጣቶቹ ለጦርነት እንዲዘምቱ ይደረጋሉ:: ከዚህ በከፋ ሁኔታ ደግሞ የተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸው (ለምሳሌ፦ ኩላሊት፣ ልብ) እየወጡ ለሽያጭ ይቀርባሉ ወይም በሕይወት ሳሉ እንደ እንሰሳ ይሸጣሉ::
- ኤች አይ ቪ (Human Immunodeficiency Virus/HIV) የሰውን በሽታ የመከላከል አቅም የሚያዳክም ቫይረስ ነው:: የኤድስ በሽታ (AIDS /Acquired Immunodeficiency Syndrome/) መድሀኒት አልተገኘለትም:: በኤች አይ ቪ ኤድስ የተጠቃ ሰው በእንቅልፍ ጊዜ ሰውነቱን የማላብ፣ የአፍና የጉሮሮ ቁስለት፣ የድካምና የጭንቀት ስሜት፣ የጡንቻ ህመምና የቆዳ ላይ ሽፍታዎች እንዲሁም ትኩሳትና የእጢዎች እብጠት ምልክቶች ይታዩበታል::

## የክለሳ ጥያቄዎች

ሀ) ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ካልሆነ ሐሰት በማለት መልሱ::

1. ከዓለም የቆዳ ስፋት ውስጥ $^{2}/3$ው በበረሀ የተሸፈነ ነው::
2. በኤች አይ ቪ የተያዘ ሰው በወቅቱ ከታከመ ሊድን ይችላል::
3. ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት የልማት ውጤት ነው::
4. ከፍተኛ የህጻናት ሞት መጠን ለፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት መንስኤ ነው::
5. ኤች አይ ቪ ኤድስ በጋራ በመመገብ ሊተላለፍ ይችላል::

ለ) በ‘ሀ’ አምድ ስር የተዘረዘሩትን በ‘ለ’ ስር ከተቀመጡት ጋር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ጎቢ | ሀ) መገኛው ሰሜናዊ አፍሪካ ነው |
| 2. ሳሀራ | ለ) መገኛው እስያ አህጉር ነው |
| 3. አርክቲክ ዋልታዊ በረሀ | ሐ) ደቡባዊ ምእራብ አፍሪካ ይገኛል |
| 4. አንታርክቲክ ዋልታዊ በረሀ | መ) መገኛው ደቡባዊ ዋልታ አካባቢ ነው |
| 5. ካላሀሪ | ሠ) መገኛው ሰሜናዊ ዋልታ አካባቢ ነው |
| | ረ) ከፊል ገሞጅማ በረሀ |

ሐ) ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር መንስኤ አይደለም፦

   ሀ) ድህነት ለ) ደካማ መንግስት

   ሐ) ልማት መ) የስራ እድል እጦት

2. የዓለም ወቅታዊ ችግር ያልሆነው የትኛው ክስተት ነው?

   ሀ) የአየር ብክለት ለ) ቅኝ አገዛዝ

   ሐ) ሽብርተኝነት መ) ድህነት

3. የሽብር ጥቃት ዋነኛ ዒላማ የሚያደርገው በየትኞቹ ላይ ነው?

   ሀ) በወታደራዊ ተቋማት ለ) በንጹሀን ዜጎች

   ሐ) በደህንነት ተቋማት መ) በፖሊስ ተቋማት

4. ከሚከተሉት ውስጥ የፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት ውጤት ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ) ረሀብ ለ) ስደት ሐ) የስራ እድል መስፋፋት መ) ድህነት

5. ከሚከተሉት ውስጥ በኤች አይ ቪ የመጠቃት ምልክት ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ) የጭንቀት ስሜት ለ) የጡንቻ ህመም

   ሐ) ትኩሳት መ) የቆዳ ቀለም መቀየር

መ) ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ።

1. ዋና ዋናዎቹ የሽብርተኝነት መንስኤዎች ምንድን ናቸው?
2. የበረሀማነትን መስፋፋት ለመከላከል መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች ምን ምን ናቸው?

ሠ) ፈታኝ ጥያቄዎች

1. የአየር ብክለት የሚያስከትላቸው አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ችግሮች ምንድን ናቸው?
2. የውሀ ብክለት የሚያስከትላቸው አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ችግሮች ምንድን ናቸው?
3. ኤች አይ ቪ ኤድስ በቤተሰብ፣ በማህበራዊ፣ በምጣኔ ሀብታዊና በፖለቲካዊ ሁኔታዎች ላይ የሚያሳድራቸው አሉታዊ ተጽእኖዎች ምንድን ናቸው?

## የቁልፍ ቃላት ፍቺ

- ኤች አይ ቪ- የሰውን ልጅ በሽታ የመከላከል አቅም የሚያዳክም ቫይረስ ነው።
- ኤድስ- የኤች አይ ቪ ቫይረስ ወደ ሰው ልጅ ደም ውስጥ ከገባ በኋላ የሚያስከትለው ህመም ነው።
- አካባቢ- በዙሪያችን የሚገኝ ማንኛውም ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ነገር ወይም ክስተት ነው።
- ሽብርተኝነት- በሕዝብ ውስጥ ፍርሀትና ጭንቀት ለመፍጠር በማለም በማንኛውም ንጹህ ዜጋ ሕይወትና ንብረት ላይ የሚፈጸም ጥቃት ነው።
- በረሀ- ሕይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ ሊቋቋሙት የማይችሉት እጅግ ከፍተኛ ሙቀት ወይም ቅዝቃዜ ያለበት ስፍራ ወይም ምድረ በዳ ነው።
- በካይ- የከባቢ አየርን ተፈጥሯዊ ባህሪ የሚቀይር ከፋብሪካዎች፣ ከመኪናዎችና ከመኖሪያ ቤቶች የሚለቀቁ መርዘኛ ጭሶች፣ ጋዞች እንዲሁም ጠጣርና ፈሳሽ ንጥረ ነገሮች ናቸው።

# ማጣቀሻዎች (References)


ጎመትኮ (1996). የህብረተሰብ ትምህርት መማሪያ መጽሀፍ, 5ኛ ክፍል (ተሻሽሎ የተዘጋጀ)፣ አማራ ብሔራዊ ክልል ት/ቢሮ. አዲስ አበባ: ቦሌ ማተሚያ ድርጅት::

ጎመትኮ (1996). የህብረተሰብ ትምህርት መማሪያ መጽሀፍ, 6ኛ ክፍል (ተሻሽሎ የተዘጋጀ)፣ አማራ ብሔራዊ ክልል ት/ ቢሮ. አዲስ አበባ: ቦሌ ማተሚያ ድርጅት::

ላፒሶ ጂ. ድሌቦ, (1982). የኢትዮጵያ መንግስት እና ህዝብ የረጅም ጊዜ ታሪክ. አዲስ አባባ : ንግድ ማተሚያ ቤት::

ኑረድን አበራ (2012). የሀረሪ ታሪካዊ ፅሑፎች መድብል: በሀረሪ ክልል ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ. ሀረር: ሀረር ማተሚያ ቤት

ሸዋነሰህ ፍስሐ) (2014). ጂኦግራፊን የማስተማር ዘዴ: ለዲፕሎማ መርሀ ግብር መማሪያ የተዘጋጀ (ያልታተመ). ጎንደር: ኢትዮጵያ

ተክለ ፃድቅ መኩሪያ (1966). የግራኝ አህመድ ወረራ. አዲስ አበባ: ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት::

________ (1953). የኢትዮጵያ ታሪክ ከአጼ ልብነ ድንግል እስከ አጼ ቴዎድሮስ. አዲስ አበባ : ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት::

Bahru Zewdu, (1998). A short history of Ethiopia and the Horn. Addis Ababa: Department of History, AAU, Ethiopia.

Henok Ahmed, (2007). Survey of Ethiopian history up to 1991. Amhara National Education Bureau, Dessie College of Teachers Education, Ethiopia.

Hussien Ahmed,(2001). Islam in the ninetieth century: Ethiopia revival, reform and reaction. The Netherlands: Brill.

Ishaq, I., (2004). Siratu Resululuah: The life history of Prophet Muhammed. London: Oxford University Press.

Lewis, H.S., (March 1966). The origin of the Oromo and Somali. Journal of African history, Madison: My Publisher.

Little, M., (2009). World History: Patterns of interaction. New York: Houghton Muffin Company.

Mohammed Hassen, (1990). The Oromo of Ethiopia: A history 1570-1860. London: Cambridge University Press.

Ofcansky, T. P., (2015). Sudan, a country study: Federal Research Division. Washington Dc: Library of Congress.

Quataert, D., (2000). The Ottoman empire 1700-1922. London: Cambridge State University.

Sergaw Hable Sellassie. (1972). Ancient and medieval Ethiopian history. Addis Ababa; United Printers.

Shewaneseh Fisseha. (2013). Introduction to social studies: A Teaching module for diploma program, Gonder, Ethiopia.

Shewaneseh Fisseha, Simachew Bantigegn & Alemneh Mellese. (2016). Social studies I (Unpublished), Bahir Dar, Ethiopia

Shewaneseh Fisseha, (2011). Geography of population, A teaching module for geography majors diploma program (Unpublished), Gonder, Ethiopia.

Shewaneseh Fisseha. (2000). Survey of world geography: A teaching module for diploma program (Unpublished), Gonder, Ethiopia.

Shillington, K., (1995). History of Africa. London: St. Martin Press.

Tadesse Tamrat, (1972). Church and state (1270-1527). London: Oxford University Press.

Tekle Tsadik Mekuria, (1973). Nubia (Nepata - Meroe). Addis Ababa: Berehan ena Selam Printing Press.

UNESCO, (1981). General African history II: ancient civilization of Africa. London: Heinemann Publishers.

________ (1988). General African History III: ancient civilization of Africa. London: Heinemann Publishers